# ማክሲም ጎርኪይ

# እናት

ልብ ወለድ

«ራዱጋ» አሳታሚ ድርጅት ።
ሞስኮ ።

ተርጓሚው ፤
ግዕዛን የማነ ።

М. Горький
МАТЬ
*на амхарском языке*

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

© «ራዱጋ» አሳታሚ ድርጅት እ.ኤ.አ. 1986

© የፕሮግሬስ የመጻሕፍት ማዘጋጃና ማሳተሚያ ቤት
የአማርኛ ትርጉም እ. ኤ. አ. 1981 ዓ. ም.

በሶቪየት ኅብረት ታተመ ።

Г $\frac{4702010200-414}{031(01)-86}$ без объявления

ISBN 5-05-001622-3

## መቅድም ።

በአንድ ሀገር ቋንቋ የሥነ-ጽሁፍ ታሪክ ውስጥ እጅግ ዓይነተኛ የሆኑ ፣ እንደውም አዲስ የሥነ-ጽሁፍ ምዕራፍ የሚከፍቱ መጻሕፍት አሉ ። ምንም እንኳን ሩስያዊው ስመ-ጥር ደራሲ ማክሲም ጎርኪይ «እናት» በሚል ርእስ የጻፈው መጽሐፍ የሶቭየት ሥልጣን ከመመሥረቱ አሥር ዓመታት አስቀድሞ የተጻፈ ቢሆንም ፤ ለሩስያውያን አዲስ የሥነ-ጽሁፍ ምዕራፍን የከፈተ ነው ። ይህንን መጽሐፉን ለእኛ ለሶቭየት ሥነ-ጽሁፍ እንደመጀመርያ የመሠረት ድንጋይ አድርገን እንቆጥረዋለን ።

«እናት» የተሰኘው የጎርኪይ መጽሐፍ ሩስያ ውስጥ በመጀመርያ የታተመው በ 1907 ዓ. ም.* ነበር ። ጎርኪይ ይኸንን መጽሐፉን ሲጽፍ ታሪካዊ ተልእኮውን በሚገባ የተገነዘበ ፤ አዕምሮውም ተደላድሎ የበሰለ ደራሲ ነበር ። በዚያን ጊዜ ዕድሜው አርባ ዓመት ይጠጋው ነበር ። ጎርኪይ ለአሥራ አምስት ዓመታት እርሱነቱን ለሥነ-ጽሁፍ እና ለሕዝባዊ ተግባራት ሰጥቶ ነበር ። ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ ዓለም-አቀፍ ታዋቂነት ያስገኙለትን ልብ-ወለድ ታሪኮች (novels) ፣ አጫጭር ልብ-ወለድ ታሪኮች (stories) እና የቲያትሮች ድርሰቶች (plays) ጽፎ ነበር ። በፖለቲካዊ ተግባሮቹ እና

---

* በዚህ መጽሐፍ ላይ ዓመተ ምህረቶች የሚቀርቡት እንደአውሮጳውያን የዘመን አቆጣጠር ነው ። (ተርጓሚው ።)

ከቦልሽቪክ ፓርቲ ጋርም በነበሩት ግንኙነቶቹ ምክን
ያት በዛሩ (ንጉሣዊው) መንግሥት ተግዞ ነበር ። ከአንድ
ጊዜ በላይም ታሥሮ ነበር ። ይኸ ሁኔታ ግን ፤ ተግባሮ
ቹን ከመፈጸም ሊያግደው አልቻለም ። በ 1905 ዓ. ም.
የሩስያ ሬቮሉሺን ጊዜ ፤ ማለትም «እናት» በሩስያ ውስ
ጥ ታትሞ ከመውጣቱ ሁለት ዓመታት በፊት ፤ ለከእ
ንግዲህ ወዲሁ ታላቅ ወዳጁ ከሆነው ከቭላዲሚር
ሌኒን ጋር ለመጀመርያ ጊዜ ተዋወቀ ።

በ 1890 ዓ. ም. አካባቢ በሩስያ ውስጥ ከቦታ-ቦታ
በመመላለስ ያደረገው ጉዞ ፤ ማኅበራዊ ጉዳዮችን በሚመ
ለከት ረገድ የነበረው አትኩሮት እና ሬቮሉሺናዊ
ግንዛቤው ፤ በዚያን ጊዜ ከነበሩት ተመሳሳዮቹ መካከል
ጥቂቶቹ ብቻ ተሳክቶላቸው የነበረው ሩስያን የመመል
ከት እና የመረዳት ችሎታ እንዲኖረው ሊያደርገው
በቃ ። የትውልድ ሀገሩ እጅግ ሰፊ በመሆኗ ፤ በሐገሩ
ውበት እና ምድሯም ባቀፈቻቸው ልዩ-ልዩ ትዕይንቶ
ች ልቡ በአንክሮ የተነካ ሲሆን ፤ ከዚሁ ጋር በአንድ
ነትም ፤ በሐገሩ ሕዝቦች ላይ ይታይ በነበረው ድንቁ
ርና ፣ ድህነት እና ሥቃይ መንፈሱ በማዘን ተረብሾ
ነበር ።

መላው የጎርኪይ የድርሰት ሥራዎቹ ማኅበራዊ
ጉዳዮችን በአት ኩሮት መገንዘቡን የሚያሳዩ ናቸው ።
ይሁን እንጂ ይህ ለሩስያ ሥነ-ጽሁፍ አንድ ብቸኛ
የሆነ ጉዳይ አይደለም ። ለሩስያ ሬቮሉሺን የመጀመር
ያዎቹ ትውልዶች ናቸው በማለት ጎርኪይ ቀጽሎአ
ቸው በነበሩት በታኅሣሣውያን (ዴካብሪስት) ግጥሞች
መካከልም ታይቶ የነበረ ጉዳይ ነው ። የዘውድ አገዛ
ዝን እና ገባርነትን በመቃወም በዲሴምበር 14 ቀን
1825 ዓ. ም. በተካሄደው እንቅስቃሴ ተሳትፈው የነበሩ
ት ባለቅኔዎች ከልባቸው ሪፑብሊክን ደጋፊዎች
የነበሩ ሲሆኑ ሕዝቦችን ለማገልገል እና የሕዝቦች



የወደፊት ኑሮም የተቃና እንዲሆን በድርሰቶቻቸው
አማካይነት ይታገሉ ነበር ። የሩስያ ታላላቅ ደራስያን
እና ባለቅኔዎች እነ ፑሽኪን ፤ ሌርሞንቶቭ ፤ ሄርዘን ፤
እና ስለእነርሱም አንድ ልብ-ወለድ መጽሐፍ ሊጽፍ
አስቦ የነበረው ፤ «ጦርነት እና ሰላም» የተሰኘው መጽ
ሐፉም ሬቮሉሺናዊ መልዕክት እንዲኖረው ያደረገው
ሌቭ ቶልስቶይ እንኳን ሳይቀር በታኅሣሣውያን ተመ
ሰጦ ነበር ።

ከጎርኪይ ጋር በአስተሳሰብ የተመሳሳይነት ቅርበት
የነበራቸው «ራዝኖቺንጽዕ»* በሚል ቅጽል ይታወቁ የ
ነበሩት ሬቮሉሺናውያን በአሥራ ዘጠኝኛው ክፍለ-ዘ
መን አጋማሽ ላይ ይገኙ ነበር ። እነርሱም ፤ ስመ-ጥር
በሆኑት ደራስያን በእነ ኔክራሶቭ እና ሳልቲኮቭ-ሼ
ድሪን ይደገፉ የነበሩት እነ ቸርኒሼቭስኪይ እና ዶብ
ሮሉቦቭ ነበሩ ። የዚህ ሥነ-ጽሁፍ ትውልዶች ሰፋ ያ
ለ ማኅበራዊ አመለካከት የነበራቸው ሲሆኑ ፤ አመለካ
ከታቸውን ለመግለጽም ብርታት ነበራቸው ።

በ 19 ኛው ክፍለ-ዘመን አጋማሽ ላይ ይቀርቡ የነ
በሩት የሩስያ ልብ-ወለድ መጽሐፎች ለሩስያ ሥነ-ጽ

---

* ራዝኖቺንጽዕ (የተለያየ ማዕርግ እና መጠርያ
ያላቸው ሰዎች) ሩስያ ውስጥ በ 18 ኛው ክፍለ ዘመን
ማከተምያ እና በ 19 ኛው ክፍለ-ዘመን መባቻ ላይ
አንድ ራሱን የቻለ መደብ የማይወክሉ የኅብረተሰ
ቦች ክፋዮች የሆኑትን የካህናት ወገኖች ፤ የነጋዴ ወገ
ኖች ፤ የዝቅተኛ ቡርዧ ወገኖች ፤ የዝቅተኛ ሹማምንት
ወገኖች ያጠቃለለ መጠርያ ነው ። እነዚህ የኅብረተሰብ
ክፋዮች አብዛኛዎቹ በአዕምሮ ሥራ ተሠማርተው የ
ነበሩ ሲሆኑ ፤ የቡርዧ ዴሞክራሲያዊ እና የሬቮሉሺና
ዊ ዴሞክራሲ አይዲዮሎጂ አንቀሳቃሾችም ነበሩ ።
(ተርጓሚው)

ሁፍ ዝናን አስገኝተዋል ። ልብ-ወለድ መጽሐፎቹ የተ
ለያዩ እንደመሆናቸው ሁሉ ፣ ሁሉም መጽሐፎች ፣ መው
ጫ-መንገዱ ከጠፋበት የሩስያ ማኅበራዊ ኑሮ እንደም
ን ሊወጣ እንደሚቻል መንገድ-መንገዱን በመሻት
ያመለክቱ ነበር ። ይኸን የመሰለው ድርጊት ፣ በ 19 ኛው
ክፍለ-ዘመን ላይ የሶስዮ-ሳይኮሎጂ (ማኅበራዊ እና
ሥነ-ልቡናዊ) ልብ-ወለድ መጻሕፍትን በመጻፍ እጅግ
ስመ-ጥር የሆኑትን እንደ ሌቭ ቶልስቶይ እና እንደ
ፌኦዶር ዶስቶየቭስኪይ የመሳሰሉትን ደራስያን ይመለ
ከታል (ከዚህም በስተቀር እነ ፑሽኪን ፣ ጎጎል ፣ ሌርሞ
ንቶቭ ፣ ቱርጌኔቭ እና ጎንቻሮቭ የተሰኙትን ቀደም ባ
ለው ጊዜ የነበሩትንም ደራስያን ይመለከታል) ።

ማክሲም ጎርኪይ ክላሲካል ለሆነው ለሩስያ የሥ
ነ-ጽሁፍ ማኅበራዊ ወግ ከፍተኛ ዋጋ ይሰጥ ነበር ።
እንደውም ፣ ሥነ-ጽሁፍን በሚመለከት ረገድ አንጋፋ
ወንድሞቹ የሆኑት ፣ በተለይም ቶልስቶይ እና ቼኾቭ
ውለታ የጣሉበት መሆናቸውን በይፋ ይገልጥ ነበር ።
ከእነርሱ የቀሰመው የሥነ-ጽሁፍን ጥበብ ብቻ አል
ነበረም ። ሩስያን እና ሩስያውያንን እንዲያውቅ ፣ የሩስ
ያውያንን መንፈሳዊ (spiritual) አኗኗር እና ሥነ-ል
ቡናዊ ምኞት ለመገንዘብ እንዲችል አብቅተውታል ።

እነሆ ስለዚህም ፣ ማክሲም ጎርኪይ የሩስያ ክላሲ
ካል ሥነ-ጽሁፍ ስመ-ጥር ወጎችን ተከትሎ በማዳበር
የቀጠለ መሆኑን እንመለከታለን ። ይሁን እንጂ ፣ ከዚ
ሁ ጋር በአንድነትም አዳዲስ የድርሰት አደራረስ
ዘዴዎችን ፈጣሪ ፣ የሶቭየት ሥነ-ጽሁፍን መሥራች ነ
በር ። ጎርኪይ የክላሲካል እና የሶቭየት ሥነ-ጽሁፎችን
የሚያገናኝ «ህያው ድልድይ» ነው በማለት ከሶቭየት
ታላላቅ ደራሲዎች መካከል አንዱ የሆነው አሌክሴ
ይ ቶልስቶይ ተናግሮአል ። በአሁኑ ጊዜ ፣ ፑሽኪን የመ
ጀመርያው ሁኖ የሚገኝበትን የሩስያ ክላሲካል ደራ



ስያን የያዙትን ቦታ ለጎርኪይም ያለአንዳች ማመን
ታት ሰጥተነዋል ። ቀደም ባለ ጊዜው ባበረከታቸው
ድርሰቶቹ ውስጥ ፣ ከፑሽኪን እስከ ቼኾቭ ድረስ ይገ
ኙ የነበሩት ታላላቅ ደራሲዎቻችን ባሕርይ የሆነውን
ከመላው ብሔሮች እና ከመላው የሰው ልጆች ጋር
የወንድማማችነት መንፈስ የመመሥረት ስሜትን ይ
ሻ የነበረ መሆኑን በህሊናችን እንገነዘባለን ። የእኛን
የሩስያን ኅብረተሰብ ከሚመለከቱት ጉዳዮች ጎን-ለጎን
የመላው የሰው ልጆችን ጉዳዮች ፣ እንደዚሁም የግለሰ
ቦችን መብቶች እና ግዴታዎችን የሚመለከቱ ጉዳዮ
ችን አንስቶአል ። የሩስያ ሥነ-ጽሁፍ በውስጡ ይዞት
ይገኝ የነበረው ይህ ባሕርይ ፣ በተለይም በቶልስቶይ
እና በዶስቶየቭስኪይ የቀረቡት ድርሰቶች በውስጣቸ
ው በያዙዋቸው እነዚህን መሳይ መልዕክቶች በዓለ
ም ላይ አድናቆትን እና ተቀባይነትን እንዲያገኙ አ
ድርገዋቸው ነበር ። ምንም እንኳን የቶልስቶይን እና
የዶስቶየቭስኪይን አመለካከቶች ጎርኪይ ያሄስ ቢሆን
ም ፣ የሰዎች ማኅበራዊ አኗኗር እንደምን በመሰለ
ሁኔታ እንደገና መደራጀት እንደነበረበት እነርሱ ያቀ
ርቡት የነበረውን አስተሳሰባቸውንም በመሠረቱ ይቃ
ወመው የነበረ ቢሆንም ፣ ምንም ጊዜ ቢሆን ፣ በተሟሟ
ቀ ክርክር ላይ በሚገኝበት ጊዜ እንኳን እነርሱን
ሲጠቅሳቸው ፣ የሰውን ልቡና ጠልቀው በመግባት እ
ና የታሪክ አጋጣሚዎችንም በሚገባ በመገንዘብ ረገ
ድ አንዳችም የሚስተካከላቸው የለም በማለት ይገል
ጻቸው ነበር ።

ጎርኪይ የሩስያ ሥነ-ጽሁፍን ግሩም ወግ ይከተል
የነበረ እና የአዳዲስ ነገሮችም ፈጣሪ ነው ስንል ፣ የሩ
ስያ ሥነ-ጽሁፍ በዕድገቱ የደረሰበትን አዲስ ምዕራፍ
ሊያስገኝ የቻለ እርሱ ብቻ ነበር ማለታችን አይደለም ።
ሂደቱ ቀስ-በቀስ ይከናወን የነበረ እና ውስብስብም

የሆነ ነበር ። ይኸንን በዓይነቱ ፍጹም አዲስ የሆነ
መጽሐፍ ጎርኪይ ሊጽፍ በነበረበት ዋዜማ ላይ (እ
ዚህ ላይ የምናወሳው ስለዚህ ስለሚያነብቡት መጽሐ
ፍ ነው ።) ደራስያን አዲስ ዓይነት የአጻጻፍ ገለጻ ዘዴ
ን ይሹ ነበር ። በ 1880 ዓ. ም. መጀመሪያ ላይ ፤ ለሩስያ
ሥነ-ጽሁፍ አድናቆትን ያስገኙ ፤ ታላላቅ ከሆኑት የሶ
ሻል እና የሳይኮሎጂ-ነክ ልብ-ወለድ መጻሕፍት መካከ
ል የመጨረሻ ማብቂያ የሆነው መጽሐፍ በዶስቶየ
ቭስኪይ ተጽፎ ነበር ። ዶስቶየቭስኪይ አረፈ ። ቱርጌኔ
ቭ ፤ የመጨረሻ ድርሰቱን ከጻፈ ስድስት ዓመታት በ
ኋላ አረፈ ። ቶልስቶይ ፤ «አና ካሬኒና» በሚል ርእስ የ
ጻፈውን ልብ-ወለድ መጽሐፉን በ 1877 ዓ. ም. ላይ የ
ጨረሰ ሲሆን ፤ «ትንሳኤ» በሚል ርእስ የጻፈውን መጽ
ሀፉን ግን እስከ 19 ኛው ክፍለ-ዘመን የመጨረሻው
ዓመት ድረስ ፤ ማለትም እስከ ሃያ ዓመት ድረስ ጽፎ
አልጨረሰም ነበር ። የቲያትር እና የአጫጭር ልብ-ወ
ለድ ታሪኮች ደራሲ የሆነው አንቶን ቼኾቭ ፤ ምንም
እንኳን ልብ-ወለድ ድርሰት ለመጻፍ ብዙ ጊዜ ያስብ
የነበረ ቢሆንም ፤ አንዳችም ልብ-ወለድ ድርሰት አልጻ
ፈም ነበር ። ለመጻፍ ለሚፈልገው ልብ-ወለድ ድርሰት
በመጽሐፉ ውስጥ የሚያቀርበው ተስማሚ የሚሆን
የባሕርያት መሪ-ባሕርይ (hero) ልክ እርሱ በሚፈልገ
ው ዓይነት ለማግኘት (ለመፍጠር) ያልቻለ ሁኖ ስለአ
ገኘው ፤ ልብ-ወለድ መጽሐፍ ለመጻፍ ያልቻለ መሆኑ
ን ገልጾአል ። በእነዚያው ዓመታት ውስጥ ቶልስቶይ
«ትንሳኤ» በሚል ርእስ ያቀርበው ለነበረ መጽሐፉ
ቅር-አሰኚ የሆነውን ዲሚትሪ ኔኽሉዶቭ የተሰኘውን
መሪ-ባሕርይ ለመጽሐፉ የፈጠረ ሲሆን ፤ ይኸንን የፈ
ጠረውን ባሕርይ በመጽሐፉ ውስጥ ዋናው ተዋናይ
እያደረገ ያራምደው ጀመር ። በዚህ የቶልስቶይ የመጨ
ረሻው ልብ-ወለድ መጽሐፉ በሆነው እና እንደዚሁ



ም ለ 19 ኛው ክፍለ-ዘመንም የሩስያ የመጨረሻው ልብ-
ወለድ መጽሐፍ በሆነው በዚህ መጽሐፉ ውስጥ ሬ
ቮሉሺናዊ የሃሳብ መልዕክት ይገኝበታል ። ምንም እ
ንኳን ቶልስቶይ እስከሕይወቱ መጨረሻ ድረስ በሬቮ
ሉሺናዊ አሠራር ተግባሮች ኅብረተሰብን ማስተካከል
ን የሚቃወም ቢሆንም ፤ ብልህ በሆነ አዕምሮው ፤
ሬቮሉሺናዊ እንቅስቃሴዎች እንዲኖሩ የሚያደርጉ ኃይ
ላት ምን እንደሆኑ በጥልቀት በመመራመር ሊገነዘባ
ቸው ችሎአል ። ከዚህ በበለጠም የዚህ ሬቮሉሺናዊ
እንቅስቃሴ ዓይነተኛ አባላት የሆኑትን ፤ ስሜታቸውን
በቅን መንፈስ በመረዳት ያንጸባርቃቸው ነበር ።

በ «እናት» አማካይነት ጎርኪይ የተለመደውን የሩስ
ያ የልብ-ወለድ መጽሐፍ የአቀራረብ ዘር በአዲስ መ
ሬት ላይ ዘራ ። የሩስያ ሥነ-ጽሁፍ ሕይወት ሊታደስ
የሚችለው ይኸንን በመሰለ ሁኔታ ብቻ ነበር ። ይህ
መጽሐፍ የወዝ-አደሩን መደብ በሚመለከት ረገድ የተ
ጻፈ የመጀመርያው የሩስያ ልብ-ወለድ መጽሐፍ ነው ።
መጽሐፉም የወዝ-አደሩ መደብ የሰው ልጅ በታሪኩ
ያከማቻቸውን መላውን ቆሳቁሳዊ እና መንፈሳዊ
ሀብቶች እንደነበሩ በመጠበቅ ሕዝቦችን ነፃ ለማ
ውጣት የሚችል ኃይል አድርጎት ቀርበዋል ። ማክሲ
ም ጎርኪይ በሩስያ ሥነ-ጽሁፍ ውስጥ አዲስ ባሕር
ይን (ጀግናን) አስተዋወቀ ። አዲስ የሆነ ኪነታዊ ዘዴን
ሳይቀበሉ ፤ በመጽሐፍ ውስጥ የሚፈጠሩ የታሪክ ገባ
ርያንን (ገባርያነ-ታሪክ) በአዲስ ዘዴ የሚቀርቡበት መን
ገድ ሳይፈጠር ፤ አዳዲስ የአደራረስ ዘዴዎች ሳይፈጠሩ ፤
ይኸንን ተግባር ማከናወን የማይቻል መሆኑ ግልጽ
ነው ።

ጎርኪይ «እናት» ን ከመጻፉ ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ
በሥነ-ጽሁፍ ዓለም የወዝ-አደሩ መደብ ተወካዮች ይ
ቀርቡ ነበር ። ይኸም ሁኔታ ይታይ የነበረው በሩስያ

ሥነ-ጽሁፍ ውስጥ ብቻ አልነበረም ። ለማስረጃም ያህል ፤ ሁለት የእንግሊዝ ደራሲዎችን ለመጥቀስ ብቻ ፤ ቻርልስ ዲከንስ እና ጆርጅ ኢሊዮት ከጎርኪይ ቀደም ብለው ስለወዝ-አደሩ መደብ ጽፈው ነበር ። የሌሎች የአውሮጳ ሀገሮች ደራሲዎችም እንደዚሁ በተመሳሳይ ሁኔታ ስለወዝ-አደሩ መደብ ጽፈዋል ። ጎርኪይ ግን በደራሲነት ተግባሩ ወስዶት የነበረው እርምጃ ሠርቶ-አደሩን ሰው ፍትሕ-አልባ የሆነ ሥርዓት ባለበት ሁኔታ የሚበደል አድርጎ በማቅረብ ብቻ ሳይሆን ፤ ታሪክን ሠሪ እንደሆነ አድርጎ ፤ በጊዜው የሚታየውን ማኅበራዊ ፍትሕ-አልባነት በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚታገል ሰው አድርጎ በማቅረብ ጭምር ይጽፍ የነበረ ደራሲ ነው ። ይኸንን በሚመለከት ሁኔታ ለዓለም ሥነ-ጽሁፍ አርዐያ የተወ ሲሆን ፤ በእርግጥም አዳዲስ የድርሰት ባሕርያትን የፈጠረ ነው ሊባል ይቻላል ።

ጎርኪይ ያከናወነው የሥነ-ጽሁፍ ተግባር በዕርግጥም አስደናቂ ነው ። እንዲህ አጭር በሆነ ጊዜ ውስጥ የተዋጣላቸው ደራሲዎች የመሆን ሁኔታ የሚያጋጥማቸው ደራስያን ጥቂቶች ናቸው ። በ 20 ኛው ክፍለ-ዘመን መጀመርያ ላይ ፤ ማለትም በሥነ-ጽሁፍ መድረክ ብቅ ማለት ከጀመረ ከአሥር ዓመታት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ፤ የጎርኪይ ስም በመላው ዓለም ታውቆ-ተደንቆ ነበር ። ይበልጥ የሚያስገርመው ደግሞ ፤ ይኸ ሊሆን የቻለው እንደ ቶልስቶይ እና ቼኾቭን የመሳሰሉ ታላላቅ ደራስያን በዚያን ወቅት ይገኙ በነበረበት ጊዜ መሆኑ ነው ። አዲሱ ክፍለ-ዘመን ጎርኪይ ላይ ያተኩር ጀመር ። እንደ ሄንሪ ኢብሰን ፤ በርናርድ ሾው ፤ አናቶል ፍራንስ የመሳሰሉ ዝነኛ ደራስያን ምናልባትም አነስ ባለ ሁኔታ የተደነቁ ሳይሆን አይቀርም ። ጎርኪይ ራሱም ቢሆን የበቀለው «ከዝቅተኛው አዘቅት» ፤ ከኅብረተሰብ መረማመጃ ሥር ሲሆን ፤ በኅፃንነቱ ፤ በለጋነቱ እና



በጎልማሳነቱ ጊዜ ደርሶበት ለነበረው ሥቃይ ፤ ዕድል-ፈንታው ደርሶለት የካሰው እና ያቻቻለለት ይመስላል ። አዲሱ ክፍለ ዘመን ተተብትቦ ይገኝበት የነበረውን የህልውና እንቆቅልሽ የሚፈታው እርሱ ይመስል ፤ ከአዲሱ ክፍለ ዘመን ምርጥ ሰዎች መካከል አንዱ እነሆ እርሱ ነበር ።

ይሁን እንጂ ፤ ምንም እንኳን ተሸጋጋሪ (አላፊ) ቢሆኑም አስደናቂ የሥነ-ጽሁፍ ታሪክ ፤ የስኬት ምልክት የሚታይባቸው እጅግ ብዙ የድርሰት ማስረጃዎችን ያበረከትልናል (ለሰባ ዓመቶች ያህል ሥራዎቹ አላፊ-ጠፊ ሳይሆኑ መቆየታቸው ተጨባጭ ማስረጃዎች በመሆናቸው ።) የጎርኪይ ሥራዎች ተዋጥተውለት የነበሩት ከላይ በተጠቀሰው መንገድ አልነበረም ። የዚህም ምክንያቱ ፤ ጎርኪይ የአዲሱን ፤ የሃያኛውን ክፍለ-ዘመን ዋና መፍቻ-ቁልፍ የሆነውን የወዝ-አደሩን መደብ በመጨበጡ እና ለድርሰቶቹም ሁሉ ዋና መፍቻ-ቁልፍ አድርጎ በመጠቀሙ ነው ። በ 20 ኛው ክፍለ-ዘመን ላይ ሠርቶ-አደር ሰው ጉዳዮችን በቁጥጥሩ ሥር የሚያውል ፤ ሁኔታዎችን ለርሱ በሚያስፈልጉት አቅጣጫዎች የሚመራ ዋና ባሕርይ ሁኖ በታሪክ መድረክ ብቅ አለ ። ማክሲም ጎርኪይ የጻፈው እና አርጋጅ-አውራጅ የሆነው ለዚህ ሠርቶ-አደር ሰው ታሪክ ነው ። ይህንን ተግባሩንም እጅግ በተሟላ እና ፍጹም ኪነታዊ በሆነ ሁኔታ «እናት» በተሰኘው መጽሐፉ ላይ አቅርቦ እንዳሳየው ያህል በሌሎቹ ድርሰቶቹ ላይ አላቀረበም ።

እርግጥ ነው ፤ ይህ ተግባሩ በአንድ ጊዜ በአዕምሮው ውስጥ ሠርጾ የተገኘ ውጤት አይደለም ። በመጽሐፉ ላይ የወዝ-አደሩን መደብ ምንነት ያሳየው ቀስ-በቀስ ደረጃ-በደረጃ በመዝለቅ ነው ። ቀደም ሲል «ከኅብረተሰብ ዝቃጭ አተላዎች» ላይ አጥልሎ በጻፉ

ቸው የአጫጭር ታሪክ ጽሁፎቹ ላይ በስተኋላ ጊዜ
ያቀረባቸውን የመጻሕፍቶቹን ባሕርያት ፍንጭ እንመ
ለከታለን ። በ 1890 ዓ. ም. ማብቂያ ላይ እና በ 20 ኛው
ክፍለ-ዘመን መጀመርያ ላይ ከፈጠራቸው መሪ-ባሕር
ያት እና ዋና-ዋና ንድፈ-ሃሣቦቹ ጋር በሚገባ ተቆራ
ኝቶ እናገኘዋለን ። ይኸውም ፤ የሶሻሊስት ዝንባሌ ስላ
ላቸው ሠርቶ-አደሮች «ሦስቶቹ» በሚል ርእስ በጻፈው
አጭር ልብ-ወለድ ድርሰቱ ፤ እንደዚሁም «አልባሌዎች»
እና «ጠላቶች» በሚል ርእስ ባቀረባቸው የቴያትር ድር
ሰቱ ላይም ይህንኑ አሳይቶአል ።

የ 1905 ዓ. ም. የሩስያ ሬቮሉሺን ጎርኪይን በደራሲ
ነቱ አዲስ እርምጃ እንዲራመድ ለማድረግ ያበቃው
አዲስ የዕድገት ምዕራፉ ነበር ። በዚህ ሬቮሉሺን ላይ
በበላይነት ቁሞ የነበረው የወዝ-አደሩ መደብ ነበር ።
ሬቮሉሺኑ ድል ሁኖ ነበር ፤ ይሁን እንጂ ፤ ወዝ-አደሮች
በተሸናፊነት ከመሰቃየት ይልቅ ድልን ለመቀዳጀት
የሚችሉ መሆናቸውን ሬቮሉሺኑ መረጃ-ማረጋገጫ ሁኖ
ላቸውም ነበር ።

ጎርኪይ ካቀረባቸው ሥራዎቹ ሁሉ እጅግ ስሙ-ጥር
የሆነውን እና በአጠቃላይም ከዓለም ሥነ-ጽሁፍ
ድርሰቶች መካከል ስሙ-ጥር የሆነውን ድርሰቱን
ያቀረበው በዚህ ሬቮሉሺን ዋዜማ ላይ ፤ በ 1903
ዓ. ም. ነበር ።

ይህ የጎርኪይ ልብ-ወለድ መጽሐፍ ተመሥርቶ
የተጻፈው በዕውነተኛ ድርጊቶች ላይ ነው ። በመጽሐ
ፉ ውስጥ ፤ በ 1902 ዓ. ም. ሶርሞቮ ላይ የተካሄደው «የወ
ዝ-አደሮች ቀን» (May Day) ሰልፍ ፤ የሶርሞቮ ፓርቲ ድር
ጅት ተግባሮች ፤ ሰላማዊ ሰልፉ ከተበተነ በኋላ የፓር
ቲው አባሎች ለፍርድ መቅረብ ይገኝበታል ። ጎርኪይ
ራሱ እንደዚህ በማለት አዘክሮአል ፡ — «ስለ ሠርቶ-አ
ደሮች አንድ ልብ-ወለድ መጽሐፍ ለመጻፍ ያሰብ



ኩት ሶርሞቮ ውስጥ ከተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ በኋ
ላ ኒዥኒ-ኖቭጎሮድ በተሰኘች ከተማ ውስጥ ነው ።
መጽሐፉን ለመጻፍ የሚያስፈልጉኝን ማቴርያሎች ወዲ
ያውኑ በመሰብሰብ እና በመመዝገብም ማከማቸት
ጀመርኩኝ ።» በሌላ አባባል ለማቅረብም ፤ የጎርኪይ ል
ብ-ወለድ መጽሐፍ አንድ ታሪካዊ የሆነ ዶኩሜንት
እንደማለት ነው ። ይሁን እንጂ ፤ ድርጊቶቹ ኪነታዊ በ
ሆነ ሁኔታ ከሀሳቡ አውጠንጥኖ እና አምጦ በፈጠ
ራቸው ሃሣቦች እንደገና ተቀናብረው የቀረቡ ናቸው ።
የድርሰቱ ባሕርያት ፒዮትር ዛሎሞቭ እና እናቱ ፈጥ
ሮ ያቀረባቸው የፈጠራ አቀራረቡ ናቸው ። ፈጣሪው
እንደሚመቸው አድርጎ ያቀረባቸው የፈጠራ ተዋንያ
ን ባሕርያቶቹ ናቸው ። በዚህም ሁኔታ ፤ «እናት» የተሰኘ
ው መጽሐፉ በ 1905 ዓ. ም. ሬቮሉሺን ዋዜማ ላይ የሩ
ስያ የሠራተኛ መደብ ያካሄዳቸውን የረዥም ትግሎ
ች ጠቅላላ መልክ ሰፋ ባለ እና አጠቃላይ በሆነ
ሁኔታ የቀረበ የኪነት ውጤት ሁኖ እናገኘዋለን ።

የጎርኪይ ሠርቶ-አደር ሰው ፤ በራሱ ሀገር ውስጥ
ለሚገኘው ለራሱ የሠራተኛ መደብ ብቻ የሚያስብ
ሳይሆን ፤ ለመላው ዓለም በጎነት የሚያስብ ሠርቶ-አደ
ር ሰው ነው ። የጎርኪይ ሠርቶ-አደር ሰው ፤ ሙሉ በ
ሆነ የቃሉ ትርጉም ተመራማሪ ምሁር ማለት ነው ።
ይህም ብቻ አይደለም ። የሚያስተውል እና የሚፈላሰ
ፍ የድርጊት ሰውም ጭምር ነው ። ድርጊቶችንም ብ
ቻውን አያከናውንም ። ድርጊቶችን የሚያከናውነው የሰ
ፊው ሕዝብ ተወካይ በመሆን ነው ። ድርጊቶቹን የሚ
ያከናውነው እጅግ ክቡር እና ሰብአዊ በሆኑ አስተሳ
ሰቦች ላይ በመመርኮዝ ነው ። ይህ «እናት» የተሰኘው
ልብ-ወለድ መጽሐፍ ፤ ለሩስያ የወደፊቱ የተሻሻለ ኑሮ ፤
የወዝ-አደሩን መደብ የትግሉ መሪ አድርጎ ያቀርባል ።
ከፍተኛ የሆነ አመለካከት ያለው መሆኑን በማረጋ

ገጥ ላይ ስለሚገኘው ስለ ወዝ-አደሩ መደብ የተጻፈ ልብ-ወለድ መጽሐፍ ነው ። የወዝ-አደሩ መደብ አባሎች እርባና ያላቸው መሆናቸውን እና የፖለቲካ እና የርዕዮተ-ዓለም ብስለታቸውም ገና ጮርቃ መሆኑን እንዲገነዘቡ ለማድረግ የሚያበቃቸው ፤ ለወዝ-አደሩ መደብ አባሎች የተጻፈ መጽሐፍ ነው ። መጽሐፉ በተጻፈበት ጊዜ ለሩስያ የወዝ-አደር መደብ እና ለመላው የሩስያ ሕዝብ አስፈላጊ መጽሐፍ ነበር ። «እናት» በሚል ርእስ ስለቀረበው ስለዚህ መጽሐፍ ሌኒን በ 1907 ዓ. ም. የሚከተለውን አስተያየት ሰጥቶበት ነበር ፡ — «እጅግ ጠቀሜታ ያለው መጽሐፍ ነው ። ሬቮሉሺናዊውን እንቅስቃሴ ለምን እንደተቀላቀሉት ሳይገነዘቡ እንደዚሁ የተቀላቀሉት ብዙ ሠርቶ-አደሮች 'እናት' ን ካነበቡ በኋላ ፤ ሬቮሉሺኑን ለምን እንደተቀላቀሉ ይገነዘባሉ ።»

የኪነት ሥራ የተሳካ ኅብር (harmony) ሊኖረው የሚችለው ባሕርያቱ ኅብር ስለአላቸው ሳይሆን ፤ ወይንም ድርጊቱ ኅብር ያለው በመሆኑ ሳይሆን ፤ የደራሲው ሥነ-ልቡናዊ አቋም ኅብር ያለው ሁኖ ሲገኝ ነው በማለት ቶልስቶይ አንድ ጊዜ የኪነትን ጉዳይ አስመልክቶ ተናግሮ ነበር ። የጎርኪይ ሥነ-ልቡናዊ አቋም «እናት» በተሰኘው መጽሐፉ ላይ ዋናይቱ ተዋናይት ባሕርይ ሁና በምትገኘው ኒሎቭና በተሰኘችው አማካይነት ይገለጻል ። «እናት» የተሰኘውን የመጽሐፉን መጠርያ የያዘች ፤ ይህች አንዲት ተራ ሠርቶ-አደሪት ሴት ነች ። ኒሎቭና ፤ በመጽሐፉ መጀመርያ ላይ ፤ በፋብሪካዎች ውስጥ ከአቅማቸው በላይ ከሚሠሩት እና እቤት ውስጥም ሰካራም በሆኑ ፀበኛ ባሎቻቸውም ከሚረገጡ-ከሚደበደቡ ብዙ መቶ የወዝ-አደሩ መደብ አባላት ከሆኑት እናቶች በመጽሐፉ መጀመርያ ላይ በምንም መንገድ የተለየች አይደለችም ። ይሁን እንጂ ፤



ልጅዋ ፓቬል የሠራተኞች መኖርያ በሆነው አካባቢ የነበረውን የኑሮ ሁኔታ እርግፍ አድርጎ በመተው ሬቮሉሺናዊ ሲሆን ፤ ኒሎቭናም የእርሱን አቋም በመከተል ከእርሱ ጋር ጎን-ለጎን መራመድ ትጀምራለች ። ኒሎቭና በመጽሐፉ ላይ የምታሳየው ግሥጋሴ ፤ ሬቮሉሺኑን የተቀላቀሉ መላው ሠርቶ-አደሮች ከሚያደርጉት ግሥጋሴ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ነው ። አንባቢ የኒሎቭናን ዓለም በዐይኖቿ አማካይነት የሚቃኝ ሲሆን ፤ ድርጊቶችንም እርሷ በምታቀርባቸው መመዘኛዎቿ አማካይነት በመመልከት በአንክሮ ያደንቃቸዋል ። ኒሎቭናን የልጅዋ የፓቬል ጓዶችም እናት ብለው ይጠሯት ነበር ። እነዚህ ሬቮሉሺናዊዎች ዕውነተኛ ወንድማማችነታቸውን የተገነዘቡት በእርሷ በኩል ፤ ለእናት ባላቸው አቋም በኩል ነበር ። በእርሷ አማካይነት ስለ መላው ሰዎች ወንድማማችነት ግንዛቤ ሊኖራቸው በቃ ። የፓቬል የቅርብ ጓደኛ የሆነው አንድሬይ ናኾድካ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚከተለውን ይናገራል ፡ — «ሁላችንም የአንዲት እናት ልጆች ነን ። ሁላችንም በመላው ዓለም የሚገኙ ሠርቶ-አደሮች ወንድማማችነት የማይናወጽ የጋለ የስሜት ማዕበል ውስጥ ተውጠን እንገኛለን ።» ገበሬው ሪቢንም ቢሆን ይኸንን ይገነዘባል ፡ — «ሰዎች አንድነታቸውን እንዲገነዘቡት ማድረግ ታላቅ ቁም ነገር ነው ። ብዙ ሚሊዮን ሰዎች አንተ የምታደርገውን ለማድረግ የሚሹ መሆናቸውን ስታውቅ ደግሞ ሁኔታው ልብህን ያገራዋል ።»

ኪነት ሰዎችን አንድ የማድረጊያ ዘዴ መሆኑን ስንገነዘብ ፤ በአጠቃላይ የጎርኪይን ሥራ ፤ በተለይም «እናት» በሚል ርእስ ያቀረበውን ልብ-ወለድ መጽሐፍ ከማድነቅ አንቆጠብም ። ቀደም ሲል እንደተናገርነው

ሁሉ ፤ «እናት» ስለወዝ-አደሩ መደብ ፤ በሰዎች መካከል ያሉትን ግንኙነቶች ስለማሻሻል ጉዳይ የተጻፈ መጽሐፍ ነው ። ይህም ማለት ፤ መጽሐፉ የቀረበው ለወዝ-አደሩ መደብ ብቻ ሳይሆን ፤ በመላው ዓለም ለሚገኙ ሕዝቦችም ጭምር ነው ።

ፕሮፌሰር ቦሪስ ቡርሶቭ ።

# ክፍል አንድ

# 1

ከሠርቶ-አደሮች የመኖሪያ ሠፈር ከፍ ብሎ የሚገ
ኘው የፋብሪካ ጡሩምባ ፤ በጥቀርሻ እና በዘይት የተበ
ከለውን ቆሻሻ አየር ሰንጥቆ ው! ው! ው! በማለት በየ
ቀኑ ያጓራል ። የጡሩምባውን ጥሪ በማክበርም ፤ እንቅ
ልፋቸውን ገና ጠግበው ያልጨረሱ እና ፊታቸውንም
ያጨፋገጉ ሰዎች ግራጫማ ከሆኑት ትንንሽ ጎጆዎ
ቻቸው ውስጥ በመውጣት ልክ እንደደነገጠ በረሮ
ከው-ከው እያሉ በፍጥነት እርምጃ መንገዳቸውን ይዘ
ው ይጓዛሉ ። ብርዳማ በሆነው የማለዳ ጭለማ የእግ
ረኛ መንገዳቸውን ይዘው እና በቆሸሸ ዘይት የተበከ
ሉት ብዙ መብራቶች ብዥ-ብዥ በሚል ብርሃናቸው
መንገዱን እያበሩላቸው ቀዝቃዛ አቀባበል ወደሚያደ
ርግላቸው ወደ ፋብሪካው ትልቅ የድንጋይ ግንብ ቤ
ት ያመራሉ ። ጭቃው ከእግራቸው ሥር ጮቅ-ጮቅ
ይላል ። ገና ከእንቅልፉ የነቃ ሰው የሚያሰማውን ጎር
ናና ድምፅ በማሰማት አየሩን በባለጌ ፀያፍ ስድቦች
እንዲወረር ያደርጉታል ። ከዚሁ ጋር በአንድነትም ሌሎ
ች ድምፆች በማጀብ ይቀበሏቸዋል ፡ — እነዚህም ፤ የ
ፋብሪካው ከባድ የጩኸት ድምፅ እና ትሽ-ትሽ!
ትሽ-ትሽ! የሚል ድምፅ የሚያሰማው ተን ነው ። የቀ
ፈፋቸው እና የተኮሳተሩ የሚመስሉት ፤ ረዣዥምም የሆ
ኑት እና የጠቆሩት የፋብሪካው ጪስ-ማውጫዎች ከሠ
ርቶ-አደሮቹ መኖርያ ሠፈር ከፍ ብለው እንደ ሞላ
ላ ግንዲላ ተጀንነው ተገትረዋል ።

ምሽት ላይ ፀሀይቱ ዘቅዘቅ በማለት በየቤቶቹ

መስኮቶች ቢጫማ የብርሃን ጨረሮቿን ስታንፀባርቅ ፤
ፋብሪካው ሠራተኞቹን ከድንጋያማ ሆድ-ዕቃው ውስ
ጥ እንደብረት ዝቃጭ በመዘርገፍ ተፍቷቸው እንደ
ገና የእግር መንገዱን ይያያዙታል ። — መልካቸው ጥ
ላሸት ተለቅልቆ ጠቁሮ ፤ የተራበው ጥርሳቸው ግጥጥ
ብሎ እና ከአካላቸው የሚወጣው ሙጫማ የሞተር
ዘይት ሽታም አየሩን አውዶት ወደየጎጆዎቻቸው የሚ
ያመራውን የእግር መንገድ ይያያዙታል ። እስከሚቀጥ
ለው ቀን ድረስ ሥራው ስላበቃ እና በየጎጆአቸው
ውስጥም እራት እና ዕረፍት የሚጠብቃቸው በመሆኑ
ምክንያት ፊታቸው ፈካ ማለት ብቻ ሳይሆን ደስተ
ኛም ይሆናል ።

የፋብሪካው ማሺኖች የሠርቶ-አደሮቹን ጉልበት
የሚበቃቸውን ያህል እንደሎሚ ከመጠጡ በኋላ አ
ሁን የዕለቱ የሥራ ጊዜ አክትሞአል ። አንዳችም ቀሪ
ምልክት ሳይተው ዕለቱ ሕይወትን ትቶ ነጉዶአል ።
ሕዝበ-አዳምም ወደ መቃብሩ ጉድጓድ የሚያመራ
ውን ጎዳና አንድ ዕርምጃ በተጨማሪ ተራምዶአል ።
አሁን ግን የሚሻው አረፍ ብሎ እ-ፎ-ይ! ማለትን እ
ና በትምባሆ ጭስ የታፈነ የመሸታ ቤት ሁካታን
ሲሆን ፤ ይኸውም ያረካዋል ።

እሁድ-እሁድ እና በበዓላት ቀናት ሰዎቹ እስከቀ
ኑ አራት ሰዓት ድረስ ይተኛሉ ። ከዚያም በኋላ ጨ
ዋዎች ናቸው የሚባሉ ባለትዳር ባሎችና ሚስቶች
ሁሉ ለሃይማኖት ግድ የለሾች የሆኑ ወጣቶችን በ
መዝለፍ የክት ልብሶቻቸውን እየለበሱ ወደ ቤተክር
ስቲያን ሊያስቀድሱ ይሄዳሉ ። ከቅዳሴ በኋላም ወደ
ቤታቸው በመመለስ ፒሮጊ* ከተመገቡ በኋላ እንደ
ገና እስከምሽት ተመልሰው ይተኛሉ ።

---

* ፒሮጊ — አምባሻ ፤ ቂጣ ማለት ነው ። (ተርጓሚው ።)



ለብዙ ዓመታት በሥራ ከመናወዝ የተነሳ ድካማ
ቸው ተከማችቶ አንጀታቸውን ምግብ እንዳይሻ ያደረ
ገው በመሆኑ ምክንያት ፤ ምግብ እንዲያባላቸው በማለት
ቆሽት የሚቀቅለውን ቮድካ በብዛት ይጠጣሉ ።

ምሽት ሲሆን በጎዳናዎች ላይ ይንሸራሸራሉ ። ምድ
ሩ ደረቅ በሆነበት ጊዜ እንኳን ባለላስቲክ ቡት መ
ጫሚያ ያለው ሁሉ ይኸንኑ መጫሚያውን ይጫማል ።
የምሽቱ የአየር-ንብረት ጃንጥላ የማያስፈልገው
ቢሆንም እንኳን ፤ ጃንጥላ ያለው ሁሉ ጃንጥላውን
ይይዛል ።

እርስ-በእርስ የሚተዋወቁት እንደተገናኙ ስለፋብሪ
ካው ፤ ስለማሺኖቹ ይነጋገራሉ ። በፋብሪካዎች ውስጥ
አለቃዎቻቸው የሆኑትን ካቦዎችም ይዘልፉአቸዋል ።
ከሥራቸው ጋር ግንኙነት ስለሌላቸው ስለአንዳችም
ነገሮች አያስቡም ፤ አያወሩምም ። አሰልቺ በሆኑት ቀናቶ
ቻቸው ውስጥ አልፎ-አልፎ የተድበሰበሱ የሃሣብ ነ
ጸብራቆች ከአዕምሮአቸው ብልጭ-ድርግም ይላሉ ። ወ
ንዶቹ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ከሚስቶቻቸው ጋር
የሚነዛነዙ ሲሆኑ ፤ ብዙውን ጊዜም ሚስቶቻቸውን
ይደበድቡዋቸዋል ። ወጣቶቹ ፤ አኮርዲዮን ወደሚጫወቱበ
ት ፤ የብልግና ዘፈኖችን ወደሚዘፍኑበት ፤ ዳንስ ወደሚ
ደንሱበት አስጸያፊ የሆኑ የብልግና ንግግሮች ወደሚ
ለዋወጡበት እና በሥካር ጥንብዝብዝ ወደሚሉበት
ወደየጓደኞቻቸው ቤቶች ወይንም ወደየመሸታ ቤቶች
ይሄዳሉ ። አድካሚ በሆነ ሥራ ውልቅልቃቸው የወጣ
በመሆኑ ምክንያት መጠጡ ቶሎ ብሎ ራሳቸው
ላይ ይወጣል ፤ ከደረታቸው ውስጥ-ለውስጥ ደግሞ
ምንነቱን ሊረዱት ያልቻሉት ነገር ልውጣ-ልውጣ
እያለ ይተናነቃቸዋል ። ስለዚህም ፤ ይኸንን ከመሰለው
ደስ-የማይል ስሜት ትንሽ ፋታ ለማግኘት በመሻት
እዚህ ግባ በማይሉት በረባ-ባልረባው ነገር ሁሉ ፀብ

በማንሳት እና እንደ ዱር-አራዊት አስፈሪ በሆነ ሁ
ኔታ በመጣላት ግብ-ግብ ይገጥማሉ ። የዚህም ውጤቱ
ደም መፋሰስን የሚያስከትል ድብድብ ነው ። ድብድ
ቡ አንዳንድ ጊዜ በከባድ የአካል ጉድለት የሚያበ
ቃ ሲሆን ፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የሞት አደጋን እስከ
ትሎ ያበቃል ።
በመካከላቸው የሚታየው የእርስ-በእርስ ሰብአዊ
ግንኙነታቸው የተመሠረተው በክፉ-አሳቢነት መንፈ
ስ ሁሉም ራሱን አድፍጦ በመጠባበቅ ላይ ነው ።
ይኸንን መሳዩ ስሜታቸውም በሥራ ብዛት ተበልቶ-
ተበልቶ እንዳለቀው አካላቸው ረዥም ዕድሜ የቆየ
በመሆኑ ፤ ከቶ ምንም ፈዋሽ መድሀኒት ሊገኝለት አይች
ልም ። ሰዎቹ የተወለዱት ከየአባቶቻቸው ከወረሱአቸ
ው ከእነዚህ የልብ ልክፍቶች ጋር በመሆኑ ይኸንን
ዓላማ-ቢስ የሆነ የጭካኔ ተግባራቸውን ይኸው ልክፍ
ታቸው እንዲገፉበት እየገፋፋቸው እስከዕለተ-ሞታቸው
ድረስ እንደጥላቸው አብሮአቸው እያንዣበበ ሲከተላቸ
ው ይኖራል ።
እሁድ-እሁድ ወጣቶቹ ወደቤት የሚገቡት ከመሸ
በኋላ ዘግይተው ነው ። ልብሶቻቸውም ተቀዳድደው ፤ በ
ቆሻሻ እና በጭቃ ተለውሰው ፤ ዓይኖቻቸው ደም አግ
ተው ጠቁረው እና አፍንጫዎቻቸውም ደም-በደም
ተለውሰው ነው ። አንዳንድ ጊዜ ጓደኞቻቸውን ደህና
አድርገው በቡጢ ስላደባዩዋቸው ፤ እንዲህ ነኝ እኔ!
በሚል ጉራ ተጀንነው ወደቤት ይገባሉ ። ሌላ ጊዜ
ደግሞ በኩርፊያ ለንቦጫቸውን ጥለው ፤ ተበሳጭተው
ወይንም በደረሰባቸው ውርደት የእልህ ሲቃ ይዞአቸ
ው ወደቤታቸው ይመለሳሉ ። የሰከሩ እና የሚያሳዝኑ ፤
ገደ-ቢሶች እና አሳፋሪዎች ናቸው ። አልፎ-አልፎ ከወ
ላጆች መካከል እናትየዋ ወይንም አባትየው ልጆቻ
ቸውን ጥንብዝ ብለው ሰክረው አጥር-ለአጥር ሲላተሙ ፤



ወይንም መሸታ ቤቱ ወለል ላይ ተዘርረው ያገኙአ
ቸዋል ። ከፍ-ዝቅ አድርገው በመስደብ በቮድካ የተነ
ከረ አካላቸውን በቡጢ እየደበደቡ እቤት ከወሰዱ ቸ
ው በኋላ ፤ እንደገና የማለዳው ጡሩምባ ጨለማውን
ሰንጥቆ ከማንራቱ በፊት ትንሽ እንቅልፍ እንዲያገኙ
በማባበል እንዲተኙ ያደርጓቸዋል ።
ወላጆች ልጆቻቸውን የስድብ ናዳ ያወርዱባቸዋል ።
ያለርኅራኄም ይደበድቧቸዋል ። ይሁን እንጂ ፤ የወጣቶቹ
እርስ-በእርስ መደባደብ እና ፡ መስከር እንደ አንድ እ
ንደተለመደ የዘወትር ጉዳይ ተወስዶአል ። አባቶቻቸው
ም እንደነርሱ ወጣት በነበሩበት ጊዜ ተደባዳቢዎች
ነበሩ ። ጠጪዎችም ነበሩ ። በአባቶቻቸው እና በእናቶ
ቻቸው ይደበደቡ ነበር ። ህይወት ምንግዜም ይህንን
መሳይ ነበረች ። ይኸን መሳይዋ ሕይወት ፤ ከዓመት-ዓመ
ት በዝግታ እና ውሀ-ልኩን ሳይለቅ እንደሚጓዝ የደ
ፈረሰ ምንጭ ትፈስስ ነበር ። ማናቸውም ነገር ቢሆን
ጥልቀት ባላቸው ወጎች እና ልማዶች አስተሳሰብ ተተ
ብትቦ የተሳሰረ ከመሆኑም በስተቀር ፤ በየአንዳንዱ ቀ
ን ተመሳሳይ የሆነ ድርጊት በመደጋገም ይፈጸማል ።
አንዳንድ ጊዜ በፋብሪካው የሠፈራ መንደር አዳ
ዲስ ሰዎች ለመኖር ይመጣሉ ። አዲስ-መጤ በመሆና
ቸው ብቻ ፤ ለመጀመርያ ጊዜ በዚያ ያለውን ነዋሪ
ይማርካሉ ። ከዚያም በኋላ ቀደም ሲል ይሠሩባቸው
ስለነበሩት ቦታዎች በማውራት ስለእነርሱ አንድ የይ
ስሙላ ዝንባሌ በሌሎቹ ላይ ያድራል ። ወዲያውኑ
ግን ለእነርሱ ያለው ወረት አልቆ ነዋሪዎቹ ስለሚለ
ምዱቸው ከምንም አይቆጥሩዋቸውም ። አዲስ-መጤዎቹ
ከተናገሩት ለመረዳት እንደሚቻለው ፤ በየትም ቦታ ቢ
ሆን የሠርቶ-አደሮች ኑሮ ተመሳሳይ መሆኑ ግልጽ
ነው ። ይኸ ደግሞ እርግጥ ከሆነ ፤ ታዲያ ምን አዲስ
ነገር አለና ነው መወያየት የሚቻለው?

ነገር ግን ፤ ከአዲስ-መጤዎቹ መካከል አንዳንዶቹ
በዚህ የመኖርያ ሠፈር ተሰምቶ የማይታወቅ ወሬ
ያወራሉ ። ስለሚያወሩት ወሬ ፤ ልክ ነው-አይደለም በማ
ለት የሚከራከር የለም ። ሁሉም ፤ አሄ ፤ ይኸ እንኳን
እንዴት ሊሆን ይችላል ፤ በሚል የተጠራጣሪነት ስሜ
ት ዝም ብለው ወሬውን ያደምጣሉ ። አዲስ-መጤዎቹ
ባወሩት ወሬ አንዳንዶቹ ተበሳጭተው ፤ ሌሎቹ ደግሞ
ያልታወቀ ሥጋት ለራሳቸው በመፍጠር ነቅተው ይጠ
ባበቃሉ ። ሌሎቹ ደግሞ ቦግ-ድርግም በሚል ተስፋ
በመረበሻቸው ምክንያት ኑሮን የበለጠ ውስብስብ እ
ንዲሆን ያደረጉባቸውን እነዚህን የወሬ ማስጠንቀቂ
ያዎች ከአዕምሮአቸው ለማስወገድ የወሬው ሁኔታ ከባ
ድ ጠጪዎች እንዲሆኑ አድርጎአቸዋል ።

የሠፈሩ ነዋሪዎች በአንድ አዲስ-መጤ ላይ ከዚ
ህ ቀደም አይተውት-ለምደውት የማያውቁት ነገር ቢ
ያዩበት ይኸንን ሰው ረዘም ላለ ጊዜያት ሳይዘነጉት
ያስታውሱታል ። እነርሱን ስለማይመስል ስለማንኛውም
ሰው ምንነትም ይሠጋሉ ። ምንም እንኳን አስቸጋሪ
ቢሆንም ፤ ገና ያልተቀሰቀሰውን ቀፋፊ አኗኗራቸውን
ምስቅልቅሉን ስለሚያወጣባቸው የሚፈሩት ይመስላሉ
ዓይነቶች ናቸው ። በማንኛውም ጊዜ መጠኑ እኩል
በሆነ ሁኔታ የኑሮ ጭነትን ተሸክመው መቆየት የለ
መዱ በመሆናቸው እና ከዚሁ ሁኔታ የሚላቀቁበት
ተስፋ የሌላቸውም በመሆኑ ማናቸውም ለውጥ ሥቃ
ያቸውን የባሰ ያንርባቸው መስሎአቸው በእርግጥ ያ
ምናሉ ።

አዳዲስ ሃሣቦችን የሚያቀርብ ማንንም ሰው ሠር
ቶ-አደር ሕዝቦች በዝምታ ከእነርሱ ያርቁታል ። ስለ
ዚህም ፤ አዲስ መጤዎቹ ብዙውን ጊዜ ከዚህ ቦታ
ለቀው ይሄዳሉ ። አልፎ-አልፎ በዚህ ቦታ የሚኖሩ
ባይታጡም እንኳን አኗኗራቸውን ልክ እንደሌሎቹ



አመሳስለው ይኖራሉ ። ወይንም ደግሞ ከሌሎቹ ለብቻ
ቆፈንግጠው በገለልተኛነት ይኖራሉ ...

አንድ ሰው ይህንን የመሰለ ኑሮ ለሃምሳ ዓመታ
ት ያህል ከኖረ በኋላ ይሞታል ።

## 2

መላ ሰውነቱን ፀጉር የወረረው ፤ አመለካከቱ ጭ
ፍግግ ያለ በመሆኑ የቀፈፈው ፤ በተጠራጣሪነት የሚመ
ለከቱ ትናንሽ ዐይኖች ያሉት እና የቅንድቦቹን
ሽፋሽፍቶችም በአጓጉል አመለካከት ከፍ-ዝቅ የሚያ
ደርጋቸው ሚኻኢል ቭላሶቭ የተሰኘው ሜካኒክ ይኸ
ንን የመሰለ አኗኗር ይኖራል ። ፋብሪካው ውስጥ ከ
ሚሠሩት ሁሉ በችሎታው እጅግ የተደነቀ ሜካኒክ
ሲሆን ፤ በሚኖርበት አካባቢም እጅግ ጠንካራ የሆነ
ጉልበታማ ሰው እርሱ ነው ። ከበላይ አለቆቹ ጋር
ግን የማይስማማ በመሆኑ ምክንያት የደሞዝ ዐበሉ
ዝቅተኛ ነው ። በማንኛው የበዓል ቀን ከአንዱ ካገኘ
ው ሰው ጋር በመጣላት ያንን የተጣላውን ሰው አ
ፈር-መሬት አስግጦ ስለሚለቀው ሰው ሁሉ የጠላው
እና የፈራው ነው ። እርሱንም በተራቸው ለመደብደብ
ብዙዎች ሞክረዋል ። ነገር ግን የሚሞክርላቸው አይ
ደለም ። እርሱን ለመደብደብ የሚቃጣ ማናቸውንም
ሰው ባየ ቁጥር ፤ ቭላሶቭ አጠገቡ ያገኘውን ድንጋይ ፤
ወይንም ፍልጥ እንጨት ፤ ወይንም የብረት ቆመጥ
አፈፍ አድርጎ በመጨበጥ እና እግሮቹንም አንፈራጥ
ጦ በመከፈት ሊመታው የቃጣውን ሰው ቆሞ ይጠ
ብቀዋል ። በፀጉር የተወረሩት እጆቹ እና ፊቱ ፤ ከዐይኖ
ቹ አንስቶ እስከ አንገቱ ድረስ ተንዠርግጎ የወረደ
ው ጥቁር ጢሙ ማንንም የሚያስበረግግ ነው ። ሰዎ

ች ግን በተለይ የሚፈሩት ዐይኖቹን ነው ፡ — ዐይኖቹ ትናንሾች ናቸው ። ነገር ግን በጥልቀት አተኩረው የሚመለከቱ ስለሆኑ ፣ በሌላው ሰው አዕምሮ ውስጥ ጠልቀው የሚገቡ ይመስላሉ ። እነዚሁኑ ዐይኖቹን የተመለከተ ማንም ሰው ቢሆን ፣ በሃሣቡ የሚያስላስለው ፣ አንዳችም ፍርሀት የሌለበት እና ይቅርታ-ቢስ ከሆነ አጥቂ አውሬ ፊት የቆመ መስሎት ነው ።

«እናንት የውሾች ልጆች! ድራሻችሁ ይጥፋና ፣ አትጠፉም ከዚህ!» በማለት በጢም ከተከበቡት ከናፍሮቹ ውስጥ በልዘው ቢጫ የሆኑ ፍልጥ-ፍልጥ የሚያካክሉ ጥርሶቹን ግጥጥ በማድረግ ጎርናና በሆነ ድምፅ ይናገራል ። ከዚያም አጠገቡ የነበሩት ሰዎች ተነስተው በመሄድ ላይ ሳሉ የፈሪ ስድባቸውን ፈራ-ተባ እያሉ ይጣጥላሉ ።

«የውሾች ልጆች!» ይላቸዋል ፣ ዐይኖቹን ከጉድጓዶቹ እንደወስፌ አሹሎ በማውጣት እና በንቀት አመለካከትም በመመልከት እየተከተላቸው ። ከዚያም እነርሱን እየተከተለ እና ጭንቅላቱን ከፍ በማድረግም እንደሚከተለው ጮሆ ይናገራል ፡ —

«ታዲያስ ፣ ማነው መሞት የሚፈልግ?»

ማንም የሚፈልግ የለም ።

ቭላሶቭ ብዙ አይናገርም ። «የውሻ ልጅ» የሚለው ስድቡ ግን ተወዳጅ የሆነ አባባሉ ነው ። ፖሊሶችን ፣ ባለሥልጣኖችን ፣ የፋብሪካውን አለቆች ለመስደብ የሚጠቀምበት ቃል ይኸው ነው ። ሁልጊዜም ሚስቱን ይጠራት የነበረው ፡ — አንቺ ውሻ በማለት ነበር ።

«አንቺ ውሻ ፣ አታዩም እንዴ እዚህ ፣ ሱሪዬ እኮ ተቀድዷል!»

ልጁን ፓቬልን የአሥራ-አራት ዓመት ልጅ ሁኖ ሳለ ፣ የጭንቅላቱን ፀጉር ጨምድዶ በመያዝ አባቱ ወደላይ ሊያንጠለጥለው ፈለገ ። ፓቬል አንድ ት



ልቅ መዶሻ አፈፍ በማድረግ አነሳና በአጭሩ እንደሚከተለው ተናገረ ፡ —

«እንዳትነካኝ!»

«ምን አልክ?» አለ አባትየው ፣ ደመና ከሰማይ ሁኖ አንድን ትልቅ ነጭ ዛፍ ወደታች እያንዠበበ እንደሚንጎባለል ሁሉ ፣ ረዥሙን እና ሸንቃጣውን ልጁን ወደታች እየተመለከተ ።

«የሚበቃኝን ያህል ከዚህ በፊት ተደብድቤአለሁ ። ከእንግዲህስ ወዲህ አልደበደብም» አለ ፓቬል ። እናም መዶሻውን ከወዲያ-ወዲህ ያወዛውዝ ጀመር ።

አባትየው ልጁን ገልመጥ ብሎ እያየ በፀጉር የተወረሩ እጆቹን ወደጀርባው በማድረግ ፡ —

«እሺ ይሁን ...» አለ ፈገግ እንደማለት ብሎ ። ከዚያም በረዥሙ ተነፈሰ እና የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«ቆይ ግዴለም አንተ ፣ ውሻ ...»

ከዚያም ጥቂት ቆየት ብሎ ወደ ሚስቱ ዞር አለና የሚከተለውን ተናገራት ፡ —

«ከእንግዲህ ወዲህ ለቤት ወጪ አንዳችም ገንዘብ እንዳትጠይቂኝ ። ከአሁን በኋላ የሚቀልብሽ ፓቬል ነው ።»

«አንተ ደግሞ የምትቀበለውን ደሞዝ በሙሉ ልትጠጣበት ነዋ?» በማለት ሚስቱ ስትፈራ-ስትቸር በቀስታ መለሰችለት ።

«ይኼ አንቺን የሚያገባሽ ጉዳይ አይደለም ፣ አንቺ ውሻ! ከፈለገኝ በላይሽ ላይ ውሽማ መወሸምም እችላለሁኝ!» አላት ።

ውሽማ አልወሸመም ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከሞተ እስከ ሁለት ዓመት ጊዜ ድረስ ግን ልጁን የት ደረሰ ብሎ እንኳን ዞር ብሎም ያላየው ከመሆኑም በስተቀር ፣ ፈጽሞ አላነጋገረውምም ነበር ።

እንደርሱው ትልቅ እና ፀጉራም የሆነ ውሻ አለ

ው ። ሁልጊዜ ጧት በማለዳ እስከፋብሪካው ድረስ ተከትሎት የሚሄድ ሲሆን ፤ በምሽት ላይ ደግሞ ከፋብሪካው ደጅአፍ ላይ ቁሞ ይጠብቀዋል ። ቭላሶቭ የበዓላት ቀኖችን የሚያሳልፈው ከአንዱ መሸታ ቤት ወደ ሌላ መሸታ ቤት በመዞር ነው ። ከመሸታ ቤት መሸታ-ቤት በሚዞርበት ጊዜ አንዳችም ነገር አይናገርም ። በመንገድ ሲጓዝም አንዳች እቃ እንደጠፋው ሰው የአላፊ-አግዳሚዎቹን ሰዎች መልክ ከፍ-ዝቅ አድርጎ ይቃኛል ። ውሻውም ፀጉራማ ጭራውን እየቆላ ቀኑን ሙሉ ጌታውን በመከተል ከጌታው ሥር እንዘጭ-እንዘጭ ሲል ይውላል ። ቭላሶቭ ሰክሮ ወደ ቤቱ በመመለስ ለእራት ወደ ገበታ ሲቀርብ ውሻውንም ራሱ በሚመገብበት ሳሕን ያበላዋል ። አንድም ጊዜ ቢሆን ውሻውን ሰድቦትም ሆነ ወይንም መትቶት አያውቅም ። ይሁን እንጂ ደግሞ ፤ አንድም ጊዜ ቢሆን የጨዋታ ንግግር አሰምቶትም ሆነ አሻሽቶት አያውቅም ። ከእራት በኋላ ሚስቱ የማዕዱን ሳሕኖች ከማንሳሳት ዘግየት ካለች ፤ ሳሕኖቹን መሬት ላይ ይወረውራቸዋል ። ከዚያም ከፊት-ለፊቱ አንድ ጠርሙስ ቮድካ ያስቀምጥና ጀርባውን ለግድግዳው ሰጥቶ ዐይኖቹን በመጨፈን እና አፉን በሰፊው ከፍቶ በማዛጋት በተሳሰረ አፉ ዘፈን ለመዝፈን ያላዝናል ። ሪዙ ላይ የተንጠባጠቡትን የዳቦ ፍርፋሪዎች ለማራገፍ ሪዙን ሲነካካ አስጠሊታ የሆነ የዘፈን ዜማው ይበልጡኑ ይተሳሰርበታል ። የሚዘፍናቸው የዘፈን ግጥሞች ግልጽ ያልሆኑ እና በስካር በመንተባተቡ ምክንያትም የተሳሰሩ በመሆናቸው ዜማዎች ልክ በክረምት የሚያላዝኑ ተኩላዎችን ድምፅ ይመስላሉ ። ቮድካው እስካለቀ ድረስ ይዘፍናል ። ከዚያም ማልዶ የፋብሪካው ጡሩምባ እስኪነፋ አግዳሚው ወንበር ላይ ይንጋለላል ፤



ወይንም ጠረጴዛው ላይ ጭንቅላቱን ደፍቶ ያንቀላፋል ። ውሻውም አጠገቡ ይተኛል ።

የሞተው ፤ የደም ጋኑ በመፈንዳቱ ነበር ። ፊቱ ጥላት መስሎ ፤ ዐይኖቹ ተከድነው ጥርሶቹን እያፋጨ ለአምስት ቀናት ከአልጋው ሳይወርድ ቆየ ። አልፎ-አልፎ ሚስቱን እንዲህ በማለት ይጠይቃት ነበር ፡ —

«ሰናምፋር ስጪኝ ... መርዢኝ ...»

ዶክተሩ ሙቅ ውሃ በገላው እንዲይዝ አዝዞ ነበር ። ይሁን እንጂ ሚኻኢል ኦፔራስዮን መደረግ ስለአለበት አሁኑኑ ሆስፒታል መሄድ አለበት ብሎም አዝዞ ነበር ።

«ገደል ግባ! አንተ የውሻ ልጅ ፤ ያላንተ አጋዥነት እሞታለሁኝ!» በማለት ቭላሶቭ ለዶክተሩ መለሰለት ።

ዶክተሩ ከሄደ በኋላ ፤ ሚስቱ እያለቀሰች ኦፔራስዮን እንዲሆን ብትጠይቀው የእጅ ጣቶቹን አጣፍሮ ወደርሷ በማመልከት በስድብ መልክ እያወዛወዘ የሚከተለውን መለሰላት ፡ —

«ወዮልሽ! ከበሽታዬ ብድን ፡ — ሥቃይሽ እጥፍ-ድርብ ይሆናል!»

ጡሩምባው ሠራተኞችን ለሥራ በሚጠራበት ማለዳ ጧት ላይ ሞተ ። አፉ ተከፍቶ እና በግንባሩ ላይ አግድም ያገደሙት ሽብሽብ መሥመሮችም ደስተኛ ባለመሆን መልክ በመኰማተር ተሸብሽበው ፤ ቭላሶቭ ሬሳ-ሳጥኑ ውስጥ ተጋድሞአል ። ሚስቱ ፤ ልጁ ፤ ውሻው ፤ ዤሶቭሺኮቭ (አንድ በሌብነት የታወቀ እና ሠካራም የሆነ ከፋብሪካ የተባረረ ሽማግሌ ሰው) እና የመንደሩ ጥቂት ለማኞችም ጭምር በቀብሩ ሥርአት ላይ ተገኙለት ። ሚስቱ አንዳችም የልቅሶ ድምፅ ሳታሰማ ጥቂት እምባ አፈሰሰችለት ። ልጁ ፓቬል ግን ፤ ለቅሶም አላለቀሰም ፤ እንባም አላነባም ። እነዚህ ጥቂት ሰዎች ያጀቡት አስከሬን ሲያልፍ የተመለከቱት የመንደ

ሩ ነዋሪዎች እያማተቡ ከመካከላቸው ገሚሶቹ የሚከተለውን እርስ በርሳቸው ስለሟቹ ተነጋገሩ ፡—

«ክፉ ሰው ነበር ። እሰይ! ኧረ እንኳን የሞተ ...»

ገሚሶቹ ደግሞ ፡—

«ውሻ ነበር ፤ እንደ ውሻ ሞተ!» እያሉ ተነጋገሩ ።

አስከሬኑ ከተቀበረ በኋላ ፤ በቀብሩ ላይ የተገኙት ሰዎች ተመለሱ ። የሟቹ ውሻ ግን ትኩስ መቃብር ላይ ቁጭ ብሎ መቃብሩን በፀጥታ ሁኖ በማሽተት ያነፈንፍ ነበር ። ከጥቂት ቀናት በኋላም የሟቹን ውሻ ማንነቱ ያልታወቀ ሰው ገደለው ...

## 3

አንድ እሁድ ቀን ፤ አባቱ ከሞተ ሁለት ሳምንት በኋላ ፤ ልጅየው ፓቬል ቭላሶቭ ጥንብዝ ብሎ ሰክሮ ወደቤቱ መጣ ። ወደቤትም እየተንገዳገደ በመግባት እና ማዕድ ከሚቀርብበት ዋና ቦታ በመቀመጥ ልክ አባቱ ያደርግ እንደነበረው ሁሉ ፤ ጠረጴዛውን በጡጫ በመደብደብ ፡—

«እራት!» እያለ ጮኸ ።

እናቱም መጥታ ከልጅዋ አጠገብ በመቀመጥ እጆቿን እላዩ ላይ ፤ ጭንቅላቱን ደረቷ ላይ ጋለል አድርጋ ያዘችው ።

«እማማ! ድረሺልኝ! ...» በማለት እጆቿን መነጨቃት ።

«የማትረባ ልጅ» በማለት እናቱም ለልጅዋ ባላት የመውደድ ስሜት እየተመለከተችው እጆቿን ሰበሰበች ።

«እስኪ ትምባሆ ልጠጣ! ስጪኝ የአባባን የትምባሆ መጠጫ ፒፓ!» በማለት ፓቬል በሠከረ አንደበቱ እየተንተባተበ ተናገረ ።



ከተወለደ ጀምሮ ለመጀመርያ ጊዜ መስከሩ ነው ። ቮድካው አካሉን አዝሎታል ። ይሁን እንጂ ፤ ህሊናውን አልሳተም ። እና በአዕምሮው ውስጥም የሚከተለው ጥያቄ ይመላለስ ጀመር ፡—

«ሰክሬአለሁኝ እንዴ? ሰክሬአለሁኝ እንዴ?»

በእናቱ ርኅራኄ እና ለርሱም በማዘን ባሳየችው አመለካከቷ ተሸበረ ። ለቅሶ-ለቅሶ ከጀለው ። ይሁን እንጂ ከስካሩ የበለጠ የሰከረ በመምሰል እንባውን ለመግታት ራሱን በራሱ ታገለ ።

እናቱም የተመሳቀለ ፀጉሩን እያሻሸች በቀስታ አነጋገር ፡—

«እንዲህ ያለ ነገር ማድረግ አያስፈልግህም ነበር» አለችው ።

ማጥወልወል ጀመረው ። ክፉኛ ካስታወከው በኋላ እናቱ አልጋው ላይ አስተኛችው እና የገረጣ ግንባሩ ላይ በቀዝቃዛ ውሀ የተነከረ ጨርቅ አስቀመጠችለት ። አሁን ትንሽ ስካሩ በረድ ያለለት መሆኑ የተሰማው ቢሆንም ፤ ራሱን ያዞረዋል ። የዐይኖቹ ቆቦች ከብደውት መክፈት አቅቶታል ። አፉ ውስጥ የቀረውን መራራ ጣዕም እያጣጣመ እና በዐይኖቹ ሽፋሽፍቶች መካከልም በጭላንጭል የእናቱን ሰፋ ያለ ፊት ባሻገር እያስተዋለ እንዲህ በማለት ያስብ ጀመር ፡—

«እኔ ገና አሁንም ልጅ ነኝ መሰለኝ ። ሌሎቹ ይጠጣሉ ። ግን ምንም አይሆኑም ። እኔን ግን አጥወለወለኝ ...»

ቤቱ ውስጥ ራቅ ካለው ቦታ ፤ የእናቱ ለስላሳ ድምፅ እንደዚህ ሲል ተሰማው ፡—

«ጠጪ መሆን ከጀመርክ ታዲያ እንዴት አድርገህ ነው እኔን የምትደግፈኝ?»

ዐይኖቹን ቀስ ብሎ ዘጋና ፡—

«ሁሉም ይጠጣል» በማለት መለሰላት ።

እናቱም ቁና-ቁና ተነፈሰች ። ዕውነቱን ነው ። ሰዎ
ቹ ያችኑ ቅንጣት የምታህል ደስታቸውን አንጠፍ
ጥፈው የሚጨርሱበት ቦታ የመሸታ ቤት ብቻ እንደ
ነበር እርሷም ታውቃለች ። ያም ሁኖ ግን ፤ የሚከተለ
ውን ተናገረች ፡ —

«አንተ ግን መጠጣት የለብህም! አባትህ ለሁለታች
ሁም ከሚበቃ በላይ ጠጥቶአል ። ልጄ ፤ አባትህ የሚበ
ቃኝን ያህል አሠቃየኝ ... ደግሞ አንተም እኔ እናት
ህ እንድሰቃይብህ ነውን? ኧረ እንዴት?»

አሳዛኝ እና ለስላሳ የሆኑትን እነዚህን ከአንደበቷ
የሚወጡትን ቃላቶቿን በሚያዳምጥበት ጊዜ ፤ አባቱ
በሕይወት በነበረበት ጊዜ ፍጹም የማትናገር በመ
ሆኗ ፤ አባቱም ከአሁን-አሁን ይደበድባት እየመሰላት
በጣም ትፈራ የነበረች በመሆኗ የእናቱን በቤት ውስ
ጥ ሕልው ሁና መኖሯ እንኳን የማይታወሰው የነበረ
መሆኑን አሰላሰለ ። እርሱም ራሱ ቢሆን ፤ ከአባቱ ጋር
እንዳይገናኝ እቤት መዋልን በተቻለው ያስወግድ የነ
በረ በመሆኑ ፤ ከእናቱ ተነጥሎ አደገ ። አሁን ፤ ቀስ በቀ
ስ ስካሩ ሲበርድለት አተኩሮ እናቱን ይመለከት ጀ
መር ።

ቁመተ-ረዥም እና ከወደ ትከሻዋ ትንሽ ጎበጥ
ያለች ነች ። ከአንድ ነገር ጋር ትጋጭ መስሏት እንደ
ምትፈራ ሁሉ ፤ በከባድ ሥራ እና በባሏ ድብደባ የጎ
በረው እና የተሰባበረው የሠራ አካላቷ ቀጥ ማለቱ
ቀርቶ የጎድን የአግድሞሽ ዘመም ብሎአል ። ሰፋ
ያለ ክብ ፊቷ ሽፍሽፋቶች አበጅቶ ተጨማድዶአል ።
ዐይኖቿም የፍርሃት እና የሥጋት መልክ ያረበበባቸ
ው ሲሆኑ ፤ ሁኔታቸውም በሠፈሩ ውስጥ እንደሚኖሩት
እንደ አብዛኛዎቹ ሴቶች ዐይኖች ሁኔታዎች ነው ። በቀ
ኝ ቅንድቧ በኩል ከፍ ብሎ አንድ ጎርጎድ ያለ ቁ
ስል ጠባሳ ትቶላት አልፎአል ። ይኸ ጠባሳዋም ቅንድ



ቧን ወደላይ ትንሽ ከፍ እንዲል የሳበው በመሆኑ ፤
ከግራ ጆሮዋ ይልቅ የቀኝ ጆሮዋ ከፍ ብሎ የተሰቀለ
እንዲመስል አድርጎታል ። ይኸም ሁኔታ ፤ ሁልጊዜ በመ
ሥጋት ምክንያት በተጠንቀቅ ሁኖ የሚጠባበቅ ሰው
መልክ ያላት እንድትመስል አድርጎአታል ። ጥቅጥቅ ያ
ሉት ወፋፍራምና ጥቁር ፀጉሮቿ አልፎ-አልፎ በሽበ
ት ተወርረዋል ። ሁለንተናዋ ለስላሳ ፤ አዘንተኛ እና ት
ሁት ነው ...

ከዐይኖቿ የእንባ ዘለላዎች ኩልል እያሉ በጉንጮ
ቿ ላይ ፈሰሱ ።

«አታልቅሺ! ዝም በይ ። እምጠጣው ስጪኝ» በማለት
ልጅዋ ጠየቃት ።

«ውሀ በበረዶ አመጣልሀለሁኝ» አለችው ።

ይሁን እንጂ ውሀውን እስክታመጣ እርሱ ዱሮ
ተኝቶአል ። የውሀው ጭልፋ በእጅዋ ላይ እየተንቀጠ
ቀጠ እና በረዶውም እየሟሟ ለጥቂት ደቂቃ ቆማ
ተመለከተችው ። ከዚያም ጭልፋውን ጠረጴዛ ላይ
አስቀመጠችና እቤቷ ግድግዳ ላይ ከተሰቀሉት ከቅዱ
ሳን ስዕሎች ፊት በተመስጦ እና በፀጥታ ተንበረከ
ከች ። ውጪ ካለው መንገድ አኳያ የሠከሩ ሰዎች
ድምፅ በመስኮቱ በኩል ሲያስተጋባ ይሰማል ። ወራቱ
በልግ በመሆኑ ፤ ሰማይ-መሬቱ ላይ የተጋገረውን
ድቅድቅ ጭለማ የአኮርዲዮን የሙዚቃ ድምፅ ሰንጥ
ቆት ያልፋል ። አንዱ በመጮህ ይዘፍናል ። ሌላው
ደግሞ አስነዋሪ የሆኑ ፀያፍ ስድቦችን ያዥጎደጉዳል ።
የፈሩ እና የደከሙ ሴቶች ሲጮኹ ድምፃቸው ይሰ
ማል ።

በእነ ቭላሶቭ ትንሽ ቤት የሚታየው የሰኗኗር
ሁኔታ ከቀድሞው ይበልጥ የተረጋጋ እና
ጸጥታ የሰፈነበተ ነው ። ከሌሎቹ በአካባቢው ከሚ
ገኙት ቤቶች ውስጥ ከሚታየው የአኗኗር ሁኔታም

የተለየ ነው ። የእነርሱ መኖርያ ቤት ይገኝ የነበረው
ረግረጋማ ወደሆነው ቦታ በሚያመራው መንገድ በኩ
ል አድርጎ ሲሆን ፤ ምንም እንኳን ይኸ ቤታቸው የ
ተሠራው ጉብታማ ቦታ ላይ ባይሆንም ኩራ ብሎ
ደረቱን ከነፋ ቦታ ላይ ከሚገኘው ከሰፈሩ በስተመ
ጨረሻ አኳያ በስተራስጌ በኩል ነው ። ከቤቱ ስፋት
ሩቡን ያህል የማዕድ ቤቱ የያዘው ሲሆን ፤ እናቲቱ
የምትተኛበት ክፍልም በስተጥግ በኩል በትንሽ ክ
ፍል ተከፍሎአል ። የተቀረው የቤቱ ሁለት-ሦስተኛ
ደግሞ ሁለት መስኮቶች ያሉት እና ባለ አራት ማ
ዕዘን ሁኖ የተሠራ ነው ። አንደኛው ጥግ ላይ የፓቬ
ል አልጋ ተዘርግቶበታል ፤ ሌላው ጥግ ደግሞ ጠረጴ
ዛ እና ሁለት አግዳሚ ወንበሮች ተዘርግተውበታል ።
የተቀሩት የቤት ዕቃዎች ፡ — ጥቂት ወንበሮች ፤ ትንሽ
መስተዋት እላዩ ላይ ያለበት የልብስ ኮሞዲኖ (ቁም
ሳጥን) ፤ ልብስ ያለበት ሰንዱክ ፤ ግርግዳ ላይ የግርግዳ
ሰዓት እና በቤቱ በስተጥግ በኩል ደግሞ ሁለት የ
ሚፀለይባቸው ቅዱሳን ስዕሎች ግርግዳው ላይ ተሰ
ቅለው የሚገኙት የቤት ዕቃዎች ናቸው ። የቤታቸው
ዕቃ ይኸው ነው ።

ፓቬል ፤ አንድ ወጣት ያደርገው ዘንድ የሚገባውን
ሁሉ ያደርጋል ፡ — አኮርዲዮን ፤ ከደረቱ ላይ በአሚዶ
የሚደርቅ ሸሚዝ ፤ ብሩኅ ቀለም ያለው ክራቫት ፤ የላስቲ
ክ ቡት ጫማ እና ከዘራ ገዝቶ ነበር ። በዚህም ምክ
ንያት በእርሱ ዕድሜ የሚገኙትን ወጣቶች ይመስላል ።
የምሽት የግብዣ ቦታዎች የሚሄድ ከመሆኑም በስተቀር
ተወዳጅ የሆኑትን ካድሪል እና ፖልካ የተሰኙትን
የዳንስ ውዝዋዜዎች በሚገባ አጥንቶአል ። እሁድ-እሁ
ድ እቤቱ የሚገባው ሰክሮ ነው ። ቮድካ ሲጠጣ ግን
ሁል ጊዜም ያጥወለውለዋል ። ሰኞ-ሰኞ ጧት ከእንቅ
ልፉ ይነሳ የነበረው እራስ ምታት ይዞት እና ልቡን



ም ቃር-አቅሮት ሲሆን ፊቱም ጥውልግ በማለት ደ
ብቶት ነው ።

እናቱ አንድ ጊዜ የሚከተለውን ጠየቀችው ፡ —
«እህ ፤ ታዲያስ ፤ የትላንትናው ምሽት ጥሩ ነበርን?»
እርሱም ጨፍግጎት እና ቀፎት እንደሚከተለው
መለሰላት ፡ —

«ኧረ ተይኝ ፤ እንደው ባታነሺብኝ ይሻላል! መጠጡ
ን ትቼ አሣ ባሠግር ይሻለኛል ። ወይንም ጠመንጃ
ገዝቼ አደን ባድን ይሻለኛል ።»

አንዳችም ቀን ከሥራ ቦታው ሳይተጓጎል ፤ ወይን
ም ዘግይቶ በመሄድ የገንዘብ ቅጣት ሳይቀጣ ሥ
ራውን በትጉህነት ይሠራል ። በጠባዩ ዝምተኛ ሲሆን ፤
ሰማያዊ ቀለም ያላቸው ዐይኖቹ ደግሞ እንደ እናቱ
ዐይኖች ትላልቅ ናቸው ። አመለካከታቸውም የተጠራጣ
ሪነት አመለካከት አላቸው ። አደን የሚያድንበት ጠመ
ንጃ አልገዛም ። አሣ ለማስገርም አይሄድም ። ይሁን
እንጂ ፤ ሌሎቹ የሚዘልቁትን የአኗኗር ጎዳና እርሱ
የተወ እና ያፈነገጠ መሆኑ ግልጽ ሁኖ ይታይ ጀ
መር ። ወደ ምሽት የግብዣ ቦታዎች የሚሄደው አል
ፎ-አልፎ ሲሆን ፤ እሁድ-እሁድ ወደቤት ይመለስ የነበ
ረውም ምንግዜም ሳይሰክር ሆነ ። የልጅዋ ፊት እየመነ
መነ የሚሄድ ፤ ዐይኖቹ ይበልጥ የአስተዋይነትን አመለ
ካከት እየተመለከቱ እና ሁለቱ ከናፍሮቹም ግጥም
ብለው አንድ ቀጭን መስመር ይመስል የመጋጠም
ሁኔታ ማሳየት የጀመሩ መሆናቸውን አትኩረው አስተ
ዋይ የሆኑት የእናቱ ዐይኖች ሁኔታውን ተገነዘቡ ። አንዳ
ች ነገር አበሳጭቶት ፤ ወይንም ደግሞ በሽታ አካሉን
እየመጠመጠው በመሄድ ላይ ይመስላል ። ቀደም ባ
ለው ጊዜ ፤ ጓደኞቹ እርሱን ለማየት ብዙውን ጊዜ
እቤት ይመጡ ነበር ። አሁን ግን ፓቬል ብዙውን
ጊዜ እቤት የማይገኝ ሁኖ ስላገኙት አዘውትረው መ

ምጣታቸውን ተው ። ልጅዋ ፤ ፋብሪካውቹ ውስጥ እንደ ሚሠሩት እንደሌሎቹ ወጣቶች ባለመሆኑ እናቱ ተደ ስታለች ። ይሁን እንጂ ፤ የተለመደውን ድፍርስ የአኗኗ ር ሁኔታ ገሸሽ አድርጎ ለመተው ከባድ ጥረት በማድረግ ላይ መሆኑን በመመልከቷ ደግሞ ምክ ንያቱን ያልተገነዘበችው ባዶ ፍርሀት በልቧ ውስጥ አደረባት ።

አንዳንድ ጊዜ በሚከተለው ሁኔታ ትጠይቀዋለች ፡ —

«ፓቬል ፤ አሁን እርግጥ ጤና ነህ?»

እርሱም እንደሚከተለው ይመልስላታል ፡ —

«ፍጹም ጤና ነኝ!»

እርሷም በረዥሙ ከተነፈሰች በኋላ ፡ —

«በጣም ከስተሃል!» ትለዋለች ።

መጻሕፍቶችን ማምጣት ጀመረ ። ያመጣቸውን መጻ ሕፍትም ሳይታይበት ለማንበብ ይጥራል ። ካነበባቸ ውም በኋላ ይደብቃቸዋል ። አንዳንድ ጊዜም ከመጻሕ ፍቱ ላይ ምንባብ በወረቀት ይገለብጥና ወረቀቱን ይደብቃል ።

እናት እና ልጅ የሚተያዩት በጣም አልፎ-አልፎ ሆነ ። ጨርሶ አይነጋገሩም ሊባል እስከሚቻልበት ደ ረጃ ድረስ ዝም ይባባሉ ጀመር ። ጧት ሻዩን በፀጥ ታ ጠጥቶ በቀጥታ ወደሥራ ቦታ ከሄደ በኋላ ቀትር ላይ ለምሳው ይመጣል ። ማዕድ ላይ ብቻ የሚወያዩ ሲሆን ፤ ማዕድ ከተነሳ በኋላ ወጥቶ ሂዶ እስከምሽት ይቆያል ። ማታ ተመልሶ ሲመጣም ከተጣጠበ በኋላ እራቱን ይበላ እና የመጻሕፍት ንባቡን ይቀጥላል ። እሁድ-እሁድ ማለዳ ተነስቶ ከቤት ይወጣል ። ወደ ቤት ተመልሶ የሚገባው አምሽቶ ነው ። ወደ ከተማ መውጣቱን እና አንዳንድ ጊዜም ቲአትር ቤት የሚገባ መሆኑን እናቱ ታውቅ የነበረች ብትሆንም ፤ ከከተማ እርሱን ለማየት የሚመጣ



ግን አንዳችም ሰው አልነበረም ። ከጊዜ-ጊዜ ከመናገ ር የመቆጠብ ሁኔታው ከፍ-ከፍ እያለ ሄደ ። እርሷ ልትረዳቸው የማትችላቸውን ቃላቶች በንግግሩ ውስጥ ጣልቃ እያገባ ታገኘው ጀመር ። ቀደም ሲል ይጠቀም ባቸው የነበሩትን ተርታ የሆኑ የሃሣብ አገላለጾቹንም ከጊዜ-ጊዜ እርግፍ አድርጎ የተወ ሁኖ ተሰማት ። አዳዲስ የሆኑት የጠባዮቹ ሁኔታዎች ለእርሷ ጉልህ ሁነው ይታዩዋት ጀመሩ ፡ — በእዩኝ-እዩኝ ባይነት የመሽቀርቀር አለባበሱን ትቶ ፤ ለሰውነቱ እና ለልብሱ ጽዳት ቅድሚያ ይሰጥ ጀመር ። አካሄዱ ቄንጥ የማያ ወጣለት ነፃ የሆነ የግዴለሽ አካሄድ ሆነ ። በጠባዩም ያልተኮፈሰ እና ያልተገበዘ ሆነ ። የእነዚህ ሁኔታዎች ምክንያቶች ምን እንደሆኑ እናቲቱን ያሳስባት ጀመር ። ለእርሷ የሚያሳየው ሁኔታም ጨርሶ አዲስ ዓይነት ሁኔታ ሆነ ፡ — አንዳንድ ጊዜ የቤታቸውን ወለል ያ ጥባል ። ሁልጊዜ እሁድ-እሁድ አልጋውን የሚያዘጋጅ እርሱ ሲሆን ፤ በማናቸውም ሁኔታ እናቱን ለማገዝ ይሞ ክራል ።

አንድ ቀን ስዕል አመጣና ግድግዳው ላይ ሰቀለ ው ። በስዕሉ ላይ ተስሎ የነበረው ሦስት ሰዎች በተ መስጠ እየተነጋገሩ በጎዳና ላይ ሲጓዙ የሚያሳይ ስዕ ል ነበር ።

የስዕሉንም ምንነት ፓቬል እናቱን ሲያስረዳት ፡ —

«ከመቃብር ያረገው ክርስቶስ ወደ ኤማሁስ ሲሄድ ነው» አላት ።

ስዕሉ ለእናቱ በጣም አስደሰታት ። ነገር ግን የሚከ ተለው ሃሣብ በአዕምሮዋ ውስጥ መመላለስ ጀመረ ፡ —

«ክርስቶስን እንደዚህ በከፍተኛ ሁኔታ የሚያፈቅር ከሆነ ፤ ለምን ቤተ ክርስቲያን አይሄድም?»

የፓቬል ወዳጅ የሆነው አናጢ በሠራው የሚያም ር የመጻሕፍት መደርደርያ ላይ ያሉት መጻሕፍት ብ

ዛታቸው ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ ሄደ ። የቤታቸውም ክፍል ደስ የሚያሰኝ ይዞታ ኖረው ።

ብዙውን ጊዜ እናቱን የሚጠራት «እርስዎ» በሚል የአክብሮት አጠራር እና «እማማ»በማለት ሲሆን ፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ይበልጥ በማቆላመጥ «እናትዬ» እያለ ይጠራታል ፦

«እናትዬ ስለእኔ እንዳታስቢ ። ዛሬ ወደቤት የምመለሰው ትንሽ አምሽቼ ነው» አላት ።

ይኸ አባባሉ ደስ አሰኛት ። አንድ ጠንከር ያለ እና ቁም ነገራም የሆነ ጉዳይ እንዳለ ከአነጋገሩ ተገንዝባለች ።

ይሁን እንጂ ፤ ሥጋቷ ከጊዜ-ጊዜ እየጨመረ ሄደ ። የመሥጋቷ ምክንያቶች ይበልጥ ተጨባጭ ሁነው አይደለም ፤ ያም ሁኖ ግን ከዚህ ቀደም ተደርጎ ባልታየ አዳዲስ ሁኔታው ምክንያት ልቧ አልረጋ ይላት ጀመር ። አንዳንድ ጊዜ በልጅዋ ትከፋ እና ከዚያም የሚከተለውን ዓይነት ሃሣብ በአዕምሮዋ ውስጥ ታመላልሳለች ፦

«ለምንድነው ጠባዩ እንደሌሎቹ ሰዎች ያይደለው? ጠባዩ እንደመነኩሴ ነው ። ይኸንን ዓይነት ጠባይ ደግሞ በእርሱ እድሜ ባሉ ሰዎች የሚታይ አይደለም ።»

እንደገና ሌላ ሃሣብ በአዕምሮዋ ውስጥ ይጉላላል ፦

«ምንአልባትም እንዴት የሚወዳት የልጃገረድ ጓደኛ አግኝቶ ይሆናል ።»

የልጃገረድ ጓደኛ ለመያዝ ደግሞ ገንዘብ ያስፈልጋል ። ከደሞዙ ጥቂት ብቻ ለኪሱ አስቀርቶ ቀሪውን በሙሉ የሚሰጠው ለእናቱ ነው ።

እና ይህን በመሰለ ሁኔታ ሳምንታት እና ወራት ለሁለት ዓመት እየተፈራረቁ አለፉ ። እንዲህ ደብዛው ባልታወቀ አስተሳሰብ ፤ እንዲህ ከጊዜ ወደጊዜ እየተባ



ባሰ በሚሄድ የእናት ጭንቀት ፤ እንዲህ ከዚህ ቀደም ባልተለመደ እንግዳ በሆነ እና በፀጥታ በተመላ ኑሮ ሁለት ዓመት አለፈ ።

## 4

አንድ ምሽት ከእራት በኋላ ፓቬል የመስኮቱን መጋረጃ ዘጋና ፋኖሱን ከሚቀመጥበት ወንበር በላይ ከፍ አድርጎ ግድግዳ ላይ በምስማር በመስቀል ከወደ ጥግ በኩል ቁጭ ብሎ ማንበብ ጀመረ ። እናቱ ከማዕድ የተነሱትን ሳሕኖች ማዕድ ቤት ወስዳ ካጣጠበች በኋላ ድምጿን ሳታሰማ ቀስ ብላ ወደ እርሱ ተጠጋች ። ፓቬልም ከተቀመጠበት ቦታ ሁኖ ራሱን ቀና አደረገና በማተኮር ሁኔታ ይመለከታት ጀመር ።

«አይ ፤ ምንም አይደል ፓሻ* ፤ እንደው እንዲሁ ነው የመጣሁት» በማለት ወዲያው በፍጥነት ለአመለካከቱ መልስ ከሰጠችው በኋላ በመሸበር መንፈስ የዐይኖቿን ሽፋሎች ክፍት-ዝግት እያደረገች ወደ ማዕድ ቤቷ ተመልሳ ሄደች ። ይሁን እንጂ ፤ እዚያም ሄዳ አልቆየችም ። ለጥቂት ጊዜ ከሃሣቧ ጋር ተሟገተችና ሳህን ያጠበችባቸውን እጆቿን ተጣጥባ እንደገና ወደርሱ ዘንድ መጣች ።

«ይህ የምታነበው ነገር ምንድነው እያልኩኝ ለመጠየቅ ሁልግዜም ልቤ ይፈልጋል ። ለመሆኑ እንደዚህ የምታነበው ምንድነው?» በማለት ቀስ ብላ ጠየቀችው ።

---

* ፓሻ — ፓቬል የሚለውን ስም ማቆላመጫ ነው ። እናት ልጅዋን በማቆላመጥ እከልዬ እንደምትለው ያለ ። (ተርጓሚው ።)

ፓቬል የሚያነበውን መጽሐፍ አጠፈው ።

«ነይ ቁጭ በይ ፤ እናት...» አላት ።

እናቱም የጉዳዩን ምንነት ለማወቅ በጉጉት በመጠባበቅ ሁኔታ ከወገቧ ቀና ብላ ተቀመጠች ።

ፓቬልም ቀስ ባለ አነጋገሩ ኮስተር ብሎ እና የእርሷንም ፊት ሳይመለከት እንደሚከተለው ተናገረ ፡—

«የማነብበው የተከለከሉ መጻሕፍቶችን ነው ። እነዚህ እኔ የማነብባቸው መጽሐፍቶች የእኛን የሠርቶ-አደሮችን ሁኔታዎች ዕውነቱን አፍርጠው የሚናገሩ በመሆናቸው እንዳናነብባቸው ተከልክለዋል ። እነዚህ መጻሕፍቶች የሚታተሙት ማንም ሳያውቅ በምሥጢር ነው ። መጻሕፍቶቹን ይዤ ብገኝ እሥር-ቤት ይከትቱኛል ። ዕውነትን ለማወቅ ስለምሻ እሥር-ቤት ይከትቱኛል ማለት ነው ። ገባሽ?» አላት ።

እናት ድንገት ትንፋሿን መተንፈስ ተሳናት ። ዐይኖቿን ገለጥ አድርጋም ልጅዋን ትመለከተው ጀመር ። ሌላ ሰው እንጂ ውነትስ እርሱ ልጅዋ ነው ብላ ማመንም ተሳናት ። ሲናገር ድምፁ ከቀድሞው የተለየ ነበር ። ጥልቀት ነበረው ። ወዝ ነበረው ። አጣጣል ነበረው ። ሳይበዛ አነስ ብሎ እላይኛው ከንፈሩ ላይ የተደመደመ ሪዙን በእጣቶቹ ከወዲያ-ወዲህ እያሻሸ ከተቀመጠበት ጥግ ያለውን ቦታ በመገረም አመለካከት ያማትር ነበር ። እናት የልጅዋ ጉዳይ አሳሰባት ። አዘነችበት ።

እንዲህ በማለትም ጠየቀችው ፡—

«ፓሻ ፤ ምነው ልጄ ፤ ለምንድነው ይኼንን ማድረግህ?»

ፓቬልም ራሱን ቀና አደረገና ተመለከታት ። ከዚያም ፡—



«ዕውነትን ለማወቅ ስለምሻ ነው» በማለት በረጋ መንፈስ እና በዝግታ መለሰላት ።

ድምፁ ለስለስ ያለ ቢሆንም ጠንካራ አወራረድ ነበረው ። ዐይኖቹም ከጉድጓዶቻቸው ወጥተው በአትኩሮት ፊት ለፊት ይመለከቱ ነበር ። አንድ ምሥጢራዊ እና አሥጊ ከሆነ ጉዳይ ጋር ለምንጊዜውም የተቆራኘ መሆኑን ተገነዘበች ። ወደድኩም-ጠላሁ የሚያጋጥመኝ ነገር ሁሉ መድረሱ የማይቀር ነበር በሚል ዕምነት ነገሮችን ሳታሰላስል እንዳመጣጣቸው የምትቀበል በመሆኗ ምክንያት ፤ በከፍተኛ ሀዘን እና ጭንቀት ልቧ ተሰበረ ። የምትናገረው መላ-ቅጡ ጠፋት ። እንደው ዝም ብላ እንባዋን ማንባት ቀጠለች ።

«አታልቅሺ» በማለት በቀስታ እና በርኅራኄ የማባበል አነጋገር ፓቬል ተናገራት ። ለእርሷም ይኼ አባባሉ እንግዲህ ደህና ሰንብቺ ያላት መስሎ ተሰማት ።

«እናቴ ፤ የምንኖረው ኑሮ ምን ዓይነት እንደሆነ እስቲ ዝግ ብለሽ አስተውይው! ይኸውና ዕድሜሽ አርባ ዓመት ነው ። ለመሆኑ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ያሳለፍሺው ኑሮ ፤ ኑሮ ነው ይባላልን? አባቴ ይደበድብሽ ነበር ። አባቴ በሕይወት በነበረበት ጊዜ ለምን ይደበድብሽ እንደነበር አሁን ልገነዘበው በቅቻለሁኝ ። በኑሮው ላይ ደርሶበት የነበረውን ምሬቱን ፤ ቁጭቱን እና ብስጭቱን ሁሉ ይወጣ የነበረው በአንቺ ላይ ነበር ። ኑሮው ከባድ ስለነበረ ጭነቱ ፤ ሸክሙ ይሰማው ነበር ። ኑሮውን እንዲህ እንዲከብድ ያደረገው ምን እንደሆነ ግን ለመገንዘብ አልቻለም ነበር ። እዚህ አሁን አለንበት ሠፈራችን ሠላሳ ዓመት ሙሉ በባርነት አገለገለ ። ሥራ መሥራት የጀመረው ፋብሪካው ገና ያኔ ሁለት የመሥሪያ ክፍሎች ብቻ በነበሩት ጊዜ ነበር ። አሁን ግን ፋብሪካው ሰባት ክፍሎች አሉት!»

ሥጋት ቢያድርባትም እንኳን ንግግሩን በጥሞና አዳመጠችው ። የልጅዋ ዐይኖች ደስ በሚያሰኝ ብሩኅ አመለካከት ጎላ-ጎላ ብለው ከጉድጓዳቸው ወጥተው ነበር ። ደረቱን ጠረጴዛው ላይ አስደግፎ እና በእንባ የታጠበውን ፊቷን ቀረብ ብሎ የዕውነትን ምንነት በሚመለከት ረገድ እስካሁን የተገነዘበውን በዚህ የመጀመርያ ንግግሩ አሰማት ። ባልተቆጠበ የወጣት ጉልበቱ ፤ የማወቅ ጽኑ ፍላጎት ያደረበት ተማሪ ስለቀሰመው ዕውቀት ኮርቶ እና በቀሰመው ዕውቀትም አምኖበት ለርሱ ግልጽ ሁነው የታዩትን ጉዳዮች በንግግሩ አማካይነት እንደሚያሰማ ሁሉ ፤ ፓቬልም የመጀመርያ ንግግሩን ለእናቱ ያሰማት በዚህ ሁኔታ ነው ። እርሱነቱን ከመፈተን ይልቅ እናቱን በማረጋጋት ለማሳመን ሲል ንግግሩን ያቀረበው አጠር አድርጎ ነው ። ቃላት አጥረውት ከንግግሩ ጋብ ባለ ጊዜም ፤ ከፊት-ለፊቱ በሀዘን ተኮማትሮ የተደቀነው የእናቱ ፊት ፤ በሃዘን እና በአድናቆት የሚመለከቱት ፤ ሊፈስሱ በተዘጋጁ ድቅን እንባዎች የታጀቡት የእናቱ ዓይኖች አተኩረው ይመለከቱታል ። ለእናቱ አዝኖአል ። እንደገና ያሰማው ንግግር ስለእርሷ እና ስለኑሮዋ ነው ።

«በሕይወትሽ ተደስተሽ ታውቂያለሽ? እስከአሁን በኖርሽው ዘመንሽ ትዝ የሚልሽ እና ቀደም ሲል ያሳለፍሽው ጥሩ ጊዜ የት አለና ነው?»በማለት ጠየቃት ።

እርሷም ፤ በሀዘን የተሠበረ ልቧን ያቀፈላት የሚመስል እና ደስታም ሀዘንም የተቀላቀለው እንግዳ ስሜት ተሰምቷት እያዳመጠችው ባዘንተኛ መንፈስ ፤ ዕውነትክን ነው በሚል ሁኔታ ራሷን ነቀነቀች ። ስለርሷ ኑሮ ይኸንን በመሰለ ሁኔታ ካሁን ቀደም የተናገረ አንድም አልነበረም ። እነዚህ የልጅዋ ቃላቶችም ለረዥም ጊዜያት ተረስተው የቆዩ ስሜቶቿን ቀሰቀሱባት ። ሊሞት የተቃረበውን እና ኑሮ ጣዕም-የለሽ መሆኑን ፣ የሚያስታውሷትን እነዚያን የወጣትነት ጊዜ ስሜቶቿን እና ፍላጎቶቿን እንደገና ከልጅዋ አንደበት የተሰሙት ቃላቶች ቀሰቀሱባት ። በወጣትነቷ ጊዜ ለልጃገረድ ጓደኞቿ ስለ ኑሮ አኗኗር ታወራላቸው ነበር ። ስለማንኛውም ሁኔታ በሰፊው ታወራ ነበር ። ቢሆንም ሁሉም ጓደኞቿ እና እርሷም ጭምር ኑሮአቸውን እንዲህ ከባድ እንዲሆን ያደረገውን ምክንያት ለማወቅ ሳይሹ ፤ ከባድ በመሆኑ ብቻ ይበሳጩ ነበር ። አሁን ልጅዋ አጠገቧ ተቀምጦ የሚገኝ ሲሆን ዐይኖቹ ፤ ፊቱ እና አንደበቱ ያቀረቡት ገለጻዎች ፤ የእናቱን የኑሮ ሁኔታ ደህና አድርጎ የተገነዘበው ይኼ ልጅዋ ፤ ይኼ ስለአለባት ሥቃይ የሚያዋያት እና ያዘነላት ልጅዋ ልቧን በኩራት ስሜት እጅጉን ነካው ።

ለእናቶች አይታዘንላቸውም ።

ይኸንን ታውቃለች ። ስለሴቶች ኑሮ ልጅዋ የተናገረው መራር እና የተለመደ የሆነውን የአኗኗር ዕውነት ሲሆን ፤ ከአሁን ቀደም ሰምታው የማታውቀው የማባበል እና የማጽናናት ድርብ ስሜቶች ልቧን ነኩት ።

«ምን ለማድረግ ነው የምትሻው?» በማለት ንግግሩን አቋርጣ ጠየቀችው ።

«መጀመርያ እኔ እማራለሁ ። በኋላ ደግሞ ሌሎችን አስተምራለሁ ። እኛ ወዝ-አደሮች መማር ያስፈልገናል ። ኑሮአችንን እንዲህ ከባድ እንዲሆን ያደረገው ምን እንደሆነ ውስጠ-ምሥጢሩን ፈልገን ማግኘት እና መገንዘብ አለብን» በማለት መለሰ ።

ሁልጊዜም ጠንቃቃ እና ኮስታራ የሆኑት ሰማያዊ ዐይኖቹ አሁን ለስላሳ እና ሩኅሩኅ በሆነ አመለካከት ተመልተው በማየቷ እጅጉን ደስ አላት ። በተሸበሸቡት ጉንጮቿ ላይ አሁንም እን

ባዎቿ ኩልል እያሉ የሚፈስሱ ቢሆኑም ፤ ከናፍሮቿ በፈገግታ ተሞልተዋል ። የኑሮን መራራነት ደህና አድርጎ የቀመሰው ልጅዋ በአንድ በኩል የኩራት ስሜት ሲያሳድርባት ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ገና ወጣት ሁኖ ሳለ አነጋገሩ ግን እንደማናቸውም እንደሌሎቹ ሰዎች ባለመሆኑ ፤ እንደዚሁም ሌሎቹ ሰዎች እና እርሷም ጭምር ችለው የተቀበሉትን የኑሮ ሁኔታ እርሱ ለመቃወም በመነሳሳቱ ስሜቷ በመነካት ከሁለት ተከፈለባት ። እንደሚከተለው ልትናገረውም ቃጣት ፡ — «ታዲያ ብቻህን ምን ማድረግ እችላለሁ ብለህ ነው ፤ ልጄ ሆይ?»

ይሁን እንጂ ፤ እንዲህ በድንገት ብልህ ሁኖ ያገኘችው እና ምንነቱንም ልትረዳው ላልቻለችው ለዚህ ለልጅዋ ያላት አድናቆት ይቀነስባት መስሏት ስለሠጋች ያሰበችውን መጠየቋን ተወችው ።

ፓቬል የእናቱ ከናፍሮች በፈገግታ ተመልተው ፤ ፊቷ በአድናቆት ተውጦ ፤ ዐይኖቿ በፍቅር ዐይን ሲያዩት ተመለከተ ። የቆመለትን ዕውነት ልትገነዘብለት እንድትችል ለማድረግ የበቃ ሁኖ ገመተ ። ከአንደበቱ የሚወጡት ቃላት ተደማጭ መሆናቸው በራሱ ተማማኝ እንዲሆን በማድረግ የወጣትነት ኩራት አሳደሩበት ። አንዴ እየሳቀ ፤ አንዴም እየተኮሳተረ በስሜት ተውጦ ይናገር የነበረ ሲሆን ፤ አንዳንዴም ከአንደበቱ የሚወጡትና የጥላቻ ስሜቱን የሚገልጽባቸው ቃላቶች ስልታቸውን እየሳቱ የእንቅጥቃጤ ሁኔታ ያሳዩ ነበር ። እናት ፤ ራሷን በመነቅነቅ የሚከተለውን መለሰችለት ፡—

«ወይ ጉድ ፤ ገዳዩ እንዲህ ነው እንዴ ፤ ፓሻ?»

እርሱም ሲመልስላት ፡ —

«አዎን እንዲህ ነው!» ያላት ከመሆኑም በስተቀር ፤ በጎ ተግባር ለመፈጸም ጥረት ያደርጉ የነበሩ ሰዎች ፤ በሰፊ ሕዝቦች መካከል የዕውነትን ዘር የሚዘሩ ሰዎች ፤ ሕይወትን እና ኑሮን ተቀናቃኝ በሆኑ ጠላቶች እንደ, አውሬ እየታደኑ ወደእሥር ቤት የሚወረወሩ እና በባርነትም ወደ ግዞት ቦታ የሚጋዙት ብዙ ብዙ ሰዎች መሆናቸውን ነገራት ።

«እነዚህን የመሳሰሉ ታጋዮችን አይቻለሁኝ! የዓለምን ምሬት የሚያጣፍጡ ጨው ናቸው!» በማለት በጋለ ስሜት ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ ።

እነዚህን የመሳሰሉት ሰዎች ሁኔታቸው በሃሣቧ መጥቶ አስፈራራት ። አሁንም ሁኔታቸውን «ወይ ጉድ ፤ ለካ እንዲህ ያሉ ሰዎች ናቸው?» በማለት ልጅዋን ለመጠየቅ ፈለገች ። ይሁን እንጂ አላደረገችውም ። ልክ ነው ብላ ባለመወሰን እና በተጠራጣሪነት ስሜት እየተነፈሰች ማንነታቸውን ልትገነዘባቸው ስለማትችለው ፤ ይሁን እንጂ እንዲህ አደገኛ የሆኑ ነገሮችን እንዲናገር እና እንዲያስብ ልጅዋን ያስተማሩ እነርሱ መሆናቸውን ስላወቀቻቸው ስለእነዚህ ሰዎች ምንነት ሲያወራላት በዝምታ ታዳምጠው ጀመር ። በመጨረሻም የሚከተለውን ተናገረችው ፡ —

«ሊነጋ ምንም አልቀረውም ። ወደአልጋህ ሂድና ትንሽም ቢሆን ተኛ ።»

«እሺ እተኛለሁ» በማለት መለሰ ። ከዚያም ፤ ወደርሷ ራሱን ደፋ አድርጎ ፡ — «የነገርኩሽን ተረድተሽዋልን?» አላት ።

«አዎን!» አለችው በረዥሙ ተነፈሰችና ። እንደገና እንባዎቿ ይፈስሱ ጀመር ። ድንገትም ተንሰቅስቃ አለቀሰች ። ከዚያም ፡ — «መጥፊያህ ነው ፤ ልጄ!» በማለት ተናገረች ።

ከተቀመጠበት ብድግ አለና በክፍሉ ውስጥ ተንጎራደደ ። እንደሚከተለውም መለሰላት ፡ —

«ይኸው እንግዲህ ምን እንደማደርግ እና የት እንደምሄድ ታውቂያለሽ ። ሁሉንም ነገር ነግሬሻለሁኝ ።

እናት ፤ እኔን የምትወጂኝ ከሆነ ፤ ይህን አርግ ፤ ይህን አታርግ እያልሽ እንዳታስቸግሪኝ እለምንሻለሁኝ!»
እርሷም ለቅሶዋን በመቀጠል ፡ —
«ምነው የኔ ልጅ ፤ የኔ ሸጋ ። ምንአልባት ... ምንአልባትም እኮ ይኸንን ሁሉ ነገር ባትነግረኝ ኖሮ ይሻለኝ ነበር!» አለችው ።
እጅዋን በእጆቹ ጨብጦ ያሻሽ ጀመር ።
«እናት» የሚለውን ቃል በተናገረበት ጊዜ ባሳየው ሞቃት ስሜት እና ካሁን ቀደም አድርጎት በማያውቀው እጅዋን በማባበስ የማሻሸት ሁኔታ እጅጉን አድርጎ ልቧ ተነካ ።
«ይህን አርግ ይህን አታርግ በማለት አላስቸግርህም!» አለችው በእንባ ሲቃ በተመላ ንግግር ። «ብቻ ተጠንቀቅ ። ልብ አድርግ ብያለሁኝ ተጠንቀቅ!» አለችው ።
ከምን መጠንቀቅ እንዳለበት የማታውቅ በመሆኗ በሀዘን ሁኔታ ዐይን-ዐይኖቹን እየተመለከተችው ዳግመኛም የሚከተለውን ተናገረች ፡ —
«ክሳትህ ከጊዜ-ጊዜ እየጨመረ ይሄዳል ...»
ጠንካራ እና ረዥም አካሉን አጥብቃ አቀፈችውና በእናትነት የርኅራኄ ፍቅር እየተመለከተችው እንደገና የሚከተለውን ወዲያውኑ በቀስታ ተናገረችው ፡ —
«ላንተ ትክክል መስሎ እንደታየህ ኑር ። እኔ በዚህ በኩል ምንም አላስቸግርህም ። አንድ ነገር ብቻ እጠይቅሀለሁኝ ፡ — ከምትገናኛቸው እና ከምታወራቸው ሰዎች ተጠንቀቅ ። ሰዎች ክፉ ስለሆኑ መፍራት አለብህ ። እርስ-በእርሳቸው ይጠላላሉ ። እርስ-በእርሳቸው የሚመቀኙ እና የሚቀናኑ ከመሆናቸውም በስተቀር ፤ ለመጎዳዳትም ይሻሉ ። አንድ ጊዜ እጣትህን በነርሱ ላይ አመልክተህ ከወቀስካቸው ይጠሉሃል! ያጠፉሃልም!» አለችው ።
እነዚህ በጭንቀት የተመሉ ቃላቶች ከአንደበቷ



እየወጡ ሲነገሩ ልጅዋ ከክፍሉ በራፍ መዳረሻ ላይ ሁኖ ያዳምጣል ። ንግግሯን እንደጨረሰችም ፈገግ በማለት የሚከተለውን ተናገረ ፡ —
«ልክ ነሽ ። ሰዎች መጥፎዎች ናቸው ። ይሁን እንጂ ፤ በዓለም ላይ ዕውነት መኖሯን ስገነዘብ ፤ የሰዎች መጥፎነትም ከዚሁ ጋር በአንድነት ተሻሽሎ ታየኝ ።»
ከዚያም እንደገና ፈገግ አለና ንግግሩን እንዲህ በማለት ቀጠለ ፡ —
«እንዴት እንደዚህ ሊሆን እንደቻለ ግን አላውቅም ። ገና ሕፃን ልጅ በነበርኩበት ጊዜ ሁሉንም ሰው እፈራ ነበር ። ከዚያም በዕድሜ ከፍ ካልኩኝ በኋላ ሁሉንም ሰው እጠላ ጀመር ። አንዳንዶቹን መጥላት የጀመርኩት የአውሬነት ባሕርይ ስለነበራቸው ሲሆን ፤ ሌሎቹን ደግሞ ለምን እጠላቸው እንደነበረ አላውቅም ። አሁን ግን ሁሉም ነገር ተለውጦ ይታየኛል ። ምናልባትም በዚህ ምክንያት ይሆናል ለሰዎች የማዝነው ። ሆነም-አልሆነም ፤ ሰዎች የአውሬነት ባሕርይ ያላቸው ስለሆኑ ፤ ወቀሳው ሁልግዜም በእነርሱ ላይ መዥጎድጎድ እንደሌለበት በተገነዘብኩኝ ጊዜ ግን ልቤ ይራራላቸው ጀመረ ...» በገዛ ራሱ ውስጥ አንዳች ድምፅን የሚያዳምጥ ይመስል መናገሩን አቋረጠ ። ከዚያም ረጋ ብሎ እና በሃሣብ ባሕር ጠልቆ የሚከተለውን ተናገረ ፡ —
«ይኸውልሽ ፤ የዕውነት እስትንፋስ ይህ ነው!» አላት ።
«እግዚአ መሀረነ ክርስቶስ! ልጄ ፤ አስጊ በሆነ ሁኔታ ተቀያይረሃል!» አለችው ።
ልጅዋ እንቅልፍ ይዞት በተኛ ጊዜ ፤ እናቱ ከአልጋዋ ላይ ቀስ ብላ ተነሳችና ወደርሱ ድምፅ ሳታሰማ ሄደች ። ቀይማ የሆነው ፤ ግትር እና ቁጡ ፊቱ በነጭ የትራሱ ልብስ ላይ ተጋድሞ በጀርባው ተኝቷል ። እንዳችም ድምፅ ባለማሰማት ከንፈሮቿ ብቻ እየተነቃ

ነቁ እና በጉንጮቿ መሃከል እንባዎቿ እንደምንጭ ውሀ ሳያቋርጡ እየፈሰሱ የማታ ልብሷን ለብሳ እና ባዶ እግሯን ሁና አልጋው አጠገብ ቆማ እናት ልጅዋን ትመለከት ጀመር ።

## 5

ምንም እንኳን ግንኙነታቸው የቀረበ ቢሆንም አሁንም እንደቀድሞው ፀጥታ የሰፈነበትን እና የመራራቅ ሁኔታ የሚታይበትን ኑሮ ይኖራሉ ።

በሳምንቱ አጋማሽ ላይ በዋለ በአንድ የበዓል ቀን ፓቬል ከቤት ሊወጣ ሲል ፊቱን ወደ እናቱ ዘንድ መለስ አደረገና የሚከተለውን ተናገረ ፦ —

«ቅዳሜ እኔን ለመጎብኘት ከከተማ ሰዎች ይመጣሉ ።»

«ከየት? ከከተማ?» በማለት እናት ከጠየቀች በኋላ ወዲያውኑ እንደማጉረምረም አለች ።

«ምነው ፤ ምን አለበት እናትዬ?» ብሎ ቅር በተሰኘ መንፈስ ፓቬል ጠየቃት ።

ባሸረጠችው የምግብ መሥሪያ ሽርጥ ፊቷን ጠራረገችና በረዥሙ በመተንፈስ ፦ —

«አይ ፤ ምንም አይደል ። እንደው ነው» አለችው ።

«ፈራሽ እንዴ?» አላት ።

«አዎን!» ብላ ዕውነቱን ነገረችው ።

ወደ እርሷ ጎንበስ ብሎ እና ልክ እንደአባቱ ቆጣ ብሎ የሚከተለውን ነገራት ፦ —

«የእኛ የሁላችንም መጥፊያችን ይሄ ፍርሃት ነው ። የእኛ የበላይ አለቆች የሆኑትም በዚህ በፈሪነታችን በመጠቀም ይበልጥ ያስፈራሩናል» አላት ።

እናቱም ደስታ በተለየው ሁኔታ የሚከተለውን ተናገረች ፦ —



«እኮ አትበሳጭ ። ልጄ ፤ ለምን አልፈራም? መላ ሕይወቴን ስፈራ ነው የኖርኩት ። ነፍሴ ያደገችው ከፍርሀት ጋር ነው!» አለችው ።

ፓቬልም በቀስታ ድምፅ አለሳልሶ የሚከተለውን ተናገረ ፦ —

«ይቅርታ አድርጊልኝ ። ምንም ማድረግ አልችልም ። እንግዶቹ ይመጣሉ!» አላት ።

ከዚያም ወጣና ሄደ ።

ለሦስት ቀናት ስትፈራ እና ስትርበተበት ቆየች ። ነግቶ ስትነሳ እነዚያ አይታቸው የማታውቃቸው እና አስፈሪ መስለው የሚታዩዋት ሰዎች እቤቷ የሚመጡ መሆኑ ትዝ ይላታል ። በአሁኑ ጊዜ ልጅዋ የሚከተለውን የሕይወት ጎዳና ያመለከቱት እነርሱ ናቸው ...

ቅዳሜ ማታ ፓቬል ከፋብሪካ ሥራ በኋላ ተመልሶ ወደቤቱ መጣ ። ተጣጥቦ ልብሱን ለወጠና እንደገና ተመልሶ ሊወጣ ሲል እናቱን ቀና ብሎ ሳይመለከት የሚከተለውን ተናገረ ፦ —

«እኔን የሚፈልጉ ሰዎች ቢመጡ ቶሎ ተመልሶ ይመጣል በይልኝ ። እና ደግሞ ፤ እባክሽን ይኸንን መፍራትሺንም ተወት አድርጊው...» አላት ።

ድክምክም ባለ መንፈስ አግዳሚው ወንበር ላይ ኩርምትምት ብላ ሰውነቷ ሁለት ላይ እጥፍ ብሎ ተቀመጠች ። ፓቬልም ኮስተር ባለ አመለካከት ተመለከታትና የሚከተለውን ተናገረ ፦ —

«ምናልባት አንቺ ... ዛሬ ወደ አንዱ ቦታ ወጣ ማለት ትፈልጊ ይሆን እንዴ?» የሚል ሃሣብ አቀረበላት ።

አነጋገሩ ቅር አሰኛት ። የሚከተለውንም መለሰችለት ፦ —

«አልፈልግም ። ለምን እሄዳለሁ?»

የኖቬምበር ወር ማብቂያ ነው ። ረፋዱ ላይ በቀዘቀዘው መሬት ደረቅ በረዶ ደህና አድርጎ የወረደበት ሲሆን ፤ ፓቬል ከውጪ ሲራመድ ከመጫሚያው በታች የሚረግጠው በረዶ ሲጥ-ሲጥ ሲል ይሰማታል ። ቤቱ ውስጥ ሁኖ በመስኮቱ መስተዋት ውጪው ሲታይ ድቅድቅ ጭለማ ተጋግሮበታል ። በሁለት እጆቿ አግዳሚ ወንበሩን ጨብጣ እና ኩርምት ብላ በርበሩን በመመልከት ተቀምጣለች ...

እንግዳ የሆነ አለባበስ የለበሱ የሚመስሏት እነዚያ መጥፎ ሰዎች ከውጪው ጭለማ ውስጥ ወደቤት በመምጣት ላይ ያሉ መስሎ ታያት ። አሁን ሰው ከበስተውጪ በኩል መጥቶ በእጁ በሩን ሲነካካው ተሰማት ።

ሌላው ከውጭ ሲያፏጭ ሰማች ። ይኸ የፉጨት ድምፅ በጭለማው እና በፀጥታው ውስጥ በቀጭኑ ተሽሎክልኮ በመምጣት የሚሰማ ሲሆን ፤ የዜማው ወዘናም አንድ ሰው የሚፈልግ ሌላ ያዘነ ሰው የሚዘፍነውን ዓይነት ጥሩ ጣዕም የነበረው ሲሆን ድምፁም ቀስ-ቀስ እያለ በቅርበት ይሰማ ጀመር ። ድንገትም ፉጨቱ ከግርግዳ ላይ ተለጥፎ የቆየ ድምፅ ይመስል በመስኮቱ በኩል በጉልህ ተሰማ ።

ደጃፉ ላይ በረዶ ከመጫምያ ሲራገፍ ይሰማል ። እናትም ዐይኖቿን በመክፈት እና የግንባሯን ቆዳ ወደላይ ሰብስባ በማሸብሸብ በድንጋጤ ተነሳች ።

በሩ ተከፈተ ። መጀመርያ ትልቅ ፀጉራማ ቆብ ያደረገ አንገት ከውጭ ወደውስጥ ሾከክ ብሎ ብቅ አለ ። ከዚያም አንድ ቁመተ ረዥም አካል አጭር ከሆነው ከበሩ ደፍ ሥር ጎንበስ ብሎ በመምጣት በሩን ገብቶ እንደጨረሰ ቀጥ ብሎ ቆመ ። ድምፅ



አሰምቶ ከተነፈሰ በኋላ ቀኝ እጁን ለመጨበጥ ዘርግቶ ፡—

«ጤና ይስጥልኝ ፤ እንደምን አመሹ!» አለ ።

እናትም መልስ ሳትመልስለት ጨበጠችውና እጅ ነሳች ።

«ፓቬል እቤት የለም እንዴ?» አለ ።

ከዚያም እንግዳው ሰው ቀስ ብሎ ፀጉራማ ካፖርቱን አወለቀ ። አንደኛውን እግሩን ከፍ አድርጎ ቡትመጫሚያው ላይ የነበረውን በረዶ በቆቡ አራግፎ ካበቃ በኋላ ፤ ሌላኛው እግሩንም ከፍ አድርጎ በረዶውን አራገፈ ። ከዚያም ቆቡን ወደጥግ መሬት ላይ ጣል አደረገና ቤቱን መሀል ለመሀል እያቋረጠ ጎርደድ-ጎርደድ አለ ። ቢቀመጥበት ይችለው አይችለው እንደሆነም የአንዱን ወንበር ጥንካሬ በእጁ ሞክር አድርጎ ቁጭ በማለት አፉን በእጁ ሸፍኖ አዛጋ ። ጥሩ ሞላላ ጭንቅላት ያለው ሲሆን ፤ ፀጉሩም በሚገባ ተበጥሮአል ። ጉንጮቹን ልቅም አድርጎ ተላጭቶአል ። ከላይኛው ከንፈሩ ላይ የሚገኘው ሪዙ ጎንና ጎኑን በዛ ያለ ፀጉር አሉት ። ትልልቅ በሆኑ እና ጎላ-ጎላ በማለት ከጉድጓዳቸው ወጣ ወጣ ባሉ ግራጫ ዐይኖቹ የቤቱን ግራና ቀኝ ደህና አድርጎ ቃኘ ።

አንደኛውን እግሩን ሌላኛው እግሩ ላይ ደርቦ እና ወንበሩ ላይ ተቀምጦ ከፊት ወደኋላ መለስ-ቀና እያለ የሚከተለውን ጥያቄ ለፓቬል እናት አቀረበ ፡—

«ይህ ጎጆ የእናንተ ነው ወይንስ ተከራይታችሁት ነው?»

ከፊት ለፊቱ ተቀምጣ የነበረችይቱ እናትም የሚከተለውን መለሰችለት ፡—

«ተከራይተነው ነው ።»

«ይኸን ያህልም ጥሩ ቤት አይደለም!» በማለት አስተያየቱን አቀረበ ።

«ፓሻ አሁን ይመጣል ። ይጠብቁት!» አለችው ።

«አዎን እርሱኑ እየጠበቅሁኝ ነው!» በማለት ግዙፍ አካል ያለው ይህ እንግዳ ሰው መለሰ ።

የረጋ እና ለስላሳ ድምፅ ያለው በመሆኑ እንደዚሁም መልኩ እንደማንኛውም ተራ መልክ በመሆኑ ተጽናናች ። አመለካከቱ ግልጽ እና የወዳጅነት መንፈስ ያልተለየው ነው ። ግልጽ ከሆኑት ዐይኖቹ ውስጥም ደስ የሚያሰኙ ነጸብራቆች እስክስታ ይወርዱ ይመስላሉ ። መላ ቁመናው ደስ ያሰኛል ። የአካሉ ቅርጽ በማዕዘን የተስተካከለ ፤ እግሮቹም ረዣዥም ዠርጋዶች ነበሩ ። ሰማያዊ ሸሚዝና እስከ መጫምያው ድረስ ተንዠርግጎ የወረደ ጥቁር ቦላሌ ሱሪ ታጥቆአል ። ማን እንደሆነ ፤ ከየት እንደመጣና ካሁን ቀደምም የእርሷን ልጅ አይቶት ያውቅ እንደሆነ ልትጠይቀው ከጀለች ። ድንገት ከወንበሩ ላይ ወደፊት ወዘወዝ እንደማለት አለና ንግግር ለመጀመር እርሱ ቀዳሚ ሁኖ ተገኘ ። የሚከተለውንም ጥያቄ አቀረበላት ፡—

«እምዬ ፤ ለመሆኑ እንዲህ ራስዎን የፈነከተው ማነው?»

ጥያቄውን ሲያቀርብ ዝግ ባለ ድምፅ ነው ፤ ዐይኖቹም ይስቁ ነበሩ ። ይሁን እንጂ እርሷ ግን ይኸን ጥያቄ በማቅረቡ ቅሬታ ተሰማት ።

ለስለስ ባለ ትህትና እና ዝግ ባለ ሁኔታ በመናገርም የሚከተለውን መልሳ ጠየቀችው ፡—

«የኔ ወጣት ፤ ይኸንን ለመጠየቅ ለመሆኑ እርስዎን ምን ያገባዎታል እባክዎ?» አለች ።

መላ ሰውነቱን ወደ እርሷ አስጠግቶ ከአንገቱ ጎንበስ በማለት

«ምነው ፤ አይቆጡ እንጂ ፤ እኔ የጠየቅሁዎት የእኔ የጡት እናትም ልክ እንደርስዎው ተመሳሳይ ዓይነት ጠባሳ ያለባት ስለሆነ ነው ። አብራው የምትኖረው ሰው በድብደባ ያበረከተላት ምልክት ነው ። መጫሚያ ሰፊ ነው ። የእግር ቅርጽ በሚያወጣበት እንጨት ፈነከታት ። እርሷ ልብስ አጣቢ እርሱ ጫማ ሰፊ ናቸው ። እኔን የጡት ልጅዋ ካደረገችኝ በኋላ ፤ የሀዘኗ መጽናኛ ቢሆን ብላ መረጠችው ። ሰካራም ነው ። አቤት ፤ እንዲህ እንዳይመስልዎ ፤ እንዴት መሰለዎ ይደበድባት የነበረው! እኔ ከፍርሃቴ የተነሳ ሲደበድባት ዐይኖቼ ተጉረጥርጠው ከጉድጓዳቸው ይወጡ ነበር!»

የፓቬል እናት በእንግዳው ሰው ግልጽነት ተረጋጋች ። በማይገባ ሁኔታ ቀደም ሲል መልስ ስለሰጠችውም ፓቬል ሲመጣ ይቆጣ ይሆናል ብላ ማሰብ ጀመረች ።

ከዚያም የጥፋተኛ አሳሳቅ እየሳቀች ፡—

«ቅድም እኮ አልተቆጣሁኝም ነበር ። ድንገት ሳላስበው እርስዎ ጥያቄ ስለጠየቁኝ ነው ። ነፍሱን ይማረውና ፤ እኔንም እንዲህ ያደረገኝ የኔው ሰውዬ ነበር ። ለመሆኑ እርስዎ ታታር * ነዎትን?» አለችው ።

እንግዳው ሰው እግሩን ጎነጥ አደረገ ፤ ከዚያም ጆሮዎቹ እስኪነቃነቁ ድረስ ብዙ ፈገግ አለ ። ከዚያም ከልቡ በሆነ የቀልድ አነጋገር ፡—

«እስከአሁን አይደለሁም» በማለት መለሰ ።

ይህ እንግዳ ሰው ባቀረበው የቀልድ መልስ ሳቅ ብላ የሚከተለውን እንደገና ተናገረች ፡—

«አነጋገርዎ ግን የሩስያዊ አነጋገር አይመስልም» አለች ።

እንግዳው ሰውም ጭንቅላቱን በፈገግታ እያነቃነቀ ፡—

---

* ታታር ፡— በሩሲያ ውስጥ የሚገኙ ሩስያዊ ያይደሉ የቱርክ ቋንቋ ቤተሰብ ተናጋሪ ከሆኑት መካከል የአንዱ ብሔር ስም ነው ። (ተርጓሚው ።)

«ከሩስያዊ የተሻለ ነው ። እኔ ከካኔቭ የመጣሁኝ ኾኾል* ነኝ» በማለት መለሰ ።

«እዚህ ከመጡ ብዙ ጊዜ ሆነዎትን?» አለችው ።

እንግዳው ሰውም ሪዙን እያሻሸ የሚከተለውን መለሰ ፡ —

«ከተማው ውስጥ አንድ ዓመት ያህል ኖሬአለሁኝ ። ወደዚህ ወደፋብሪካው ከመጣሁኝ ግን አንድ ወር ያህል ቢሆነኝ ነው ። እዚህ ልጅዎን ፓቬልን እና ሌሎችም እርሱን የመሳሰሉ አንዳንድ ጥሩ ሰዎች አሉ ። ስለዚህም ፣ እንደሚመስለኝ የምኖረው እዚህ ሳይሆን አይቀርም ።»

በጣም ደስ አሰኛት ። ስለልጅዋ የሙገሳ ጥሩ ቃላት ከአንደበቱ በመውጣቱም ልትክሰው ፈለገች ። እንደዚህ በማለትም ጠየቀችው ፡ —

«ሻይ ላምጣልዎትን?» አለችው ።

እርሱም ትከሻውን በመወዝወዝ ፡ —

«እኔን ብቻዬን ሊጋብዙኝ! ሌሎቹ እስኪመጡ ድረስ ይቆዩ ። ሁሉም ሲመጡ ሁላችንንም ይጋብዙናል…» አላት ።

ይኸ «ሌሎቹ እስኪመጡ» የተሰኘ አነጋገሩ ፍርሃቷን አስታወሳት ።

«ምነው ሌሎቹን የሚመጡትንም እንደዚህ እንግዳ ሰው ቀና ሰዎች ባደረገልኝ!» በማለት ታስብ ጀመር ።

አሁንም እንደገና ከበሩ መግቢያ ላይ የፓቬል እናት ድምፅ ሰማች ። በሩም በችኩላ ተከፈተ ።

---

* ኾኾል ፡ — ሩስያውያን ፣ ኡክራይናውያንን በቅጽል ስም ሲጠሯቸው ኾኾል ይሏቸዋል ። ትርጓሜውም ራሱን ተላጭቶ ጋሜ የቀረው ማለት ነው ። (ተርጓሚው ።)



እንደገና እናት ከተቀመጠችበት ተነሳች ። መቸስ እንዴ ፣ ይግረምሽ ብሏት የለ ፣ አሁን ደግሞ የመጣችው አንዲት ወጣት ልጃገረድ ነች ። እርሷም ወደ ማዕድ ቤቱ አልፋ ገባች ። ልጃገረዲቱ ቁመተ-አጭር ፣ መልከ-ተራ ስትሆን ረዥም ፀጉሯን በልሙጡ ወደኋላ አስተኝታዋለች ። በቀስታ አነጋገር እንዲህ በማለት ልጃገረዲቱ ጠየቀች ፡ —

«ዘገየሁ እንዴ?»

ኾኾል ከበስተበራፉ በኩል እየተመለከተ ፡ —

«የለም አልዘገየሽም ። በእግርሽ ነው እንዴ የመጣሽው?» አላት ።

«ታዲያስ በእግሬ ነው እንጂ ። እርስዎ የፓቬል ሚኻይሎቪች እናት ነዎትን? ጤና ይስጥልኝ እንደምን አመሹ ፣ ናታሻ እባላለሁኝ» በማለት ልጃገረዲቱ ከፓቬል እናት ጋር ተዋወቀች ።

«በአባትዎ ስምስ ማን ይባላሉ?» በማለት እናት ጠየቀች ።

«ቫሲሌቭና እባላለሁኝ ። እርስዎስ?» በማለት ልጃገረዲቱ መልሳ ጠየቀች ።

«ፔላጌያ ኒሎቭና እባላለሁኝ» በማለት እናት መለሰች ።

«ይኸው እንግዲህ ተዋወቅን …» አለች ልጃገረዲቱ ።

«አዎን» አለች እናትም ፣ በትንሹ እየተነፈሰች እና ልጃገረዲቱንም በፈገግታ እየተመለከተቻት ።

ልጃገረዲቱ ካፖርቷን ስታወልቅ ኾኾል ለመቀበል እያገዛት የሚከተለውን ጠየቃት ፡ —

«ይበርዳልን?»

«አዎ ፣ ሜዳው ላይ በጣም ይበርዳል ። ነፋሱ ኃይለኛ ነው …» አለች ።

ድምጿ ጉልህ እና ግልጽ ነው ። አፏ ጠባብ ሁኖ ከናፍሮቿ ዳጎስ ያሉ ናቸው ። እንደው በጠቅላላ

ው ድቡልቡል ያለች ለጋ ፍሬ ማለት ነች ። ካፖርቷን ካወለቀች በኋላ ሮዝማ የሆኑ ጉንጮቿን በብርድ በቀዘቀዙት እጣቶቿ እያሻሸች እና ወለሉንም በኮፍ መጫምያዋ ቋ-ቋ እያደረገች በመርገጥ ወደክፍሉ ገባች ።

«እንዴት ያለቡት ጫማ ትሄዳለች!» የሚል ሃሣብ በእናት አዕምሮ ተመላለሰ ።

«ኢ-ት-ት-ት-ት! ቅዝቃዜው በረዶ አድርጎኛል!» አለች ልጃገረዲቱ ።

«ቆይ ፤ አሁኑኑ ሳሞቫሩን* እጥዶዋለሁኝ» በማለት እናት በፍጥነት ተቻኩላ ወደማዕድ ማዘጋጃ ክፍል እየሄደች ፡ — «አሁን ነው የሚደርስ» አለች ።

ይህችን ልጃገረድ ረዘም ካለ ጊዜ ጀምሮ የምታውቃት ያህል ሁኖ ተሰማት ። በእናትነት የርኅራኄ ፍቅርም ወደደቻት ። እሌላኛው ክፍል የሚወራውን ወሬ እናት ከማዕዱ ማዘጋጃ ክፍል ሁና በማዳመጥ ከናፍሮቿ በፈገግታ ተመሉ ።

«ናሆድካ ፤ ምነው እንዲህ ፍዝዝ አልክ!» በማለት ልጃገረዲቱ ጠየቀችው ።

«አይ ፤ እረ እንደው ነው» በማለት ኮኮል በዝግታ ድምፅ መለሰ ።

«እኚህ የሚች ሚስት ዐይናቸው የደስ-ደስ አለው ። ምንአልባት የእናቴ ዐይኖችም የእሳቸውን ዐይኖች ይመስሉ ይሆናል ብዬ ነበር በመተከዝ የማስበው ። ስለእናቴ ብዙ አስባለሁኝ ። በሕይወት አለች የሚል ስሜት ይሰማኛል» አለ ።

«ሞተዋል ብለህ ነበርኮ» አለችው ።

«የሞተችው የጡት እናቴ ነች ። አሁን የምናገረው ስለወላጅ እናቴ ነው ። ምናልባት ኪየቭ ከተማ ውስጥ

---

* ሳሞቫር ፡ — ማለት የሻይ ማፍያ ነው ።



በሚገኙት መንገዶች ትለምን ይሆናል ። ቮድካም ትጠጣ ይሆናል ። በሰከረች ቁጥርም ፖሊሶች እያዳፉ በጥፊ ይመቷት ይሆናል ...»

«ውይ ምስኪን ልጅ!» በማለት አሰበች እና እናት ማዕድ ክፍል ሁና በረዥሙ ተነፈሰች ።

ናታሻ አንድ እናት ልትሰማው ያልቻለችውን ነገር በፍጥነት ፤ በለስላሳነት እና በስሜት ተናገረች ። አሁንም እንደገና የኮኮል ድምፅ በጉልህ ተሰማ ።

«አይ ፤ ጓዲት ፤ አንቺ ገና ትንሽ ኅፃን ነሽ ። ገና በልቶሽም አልጠገብሽም ። መውለድ ከባድ ነገር ነው ። ሰውን በጎ ምግባር ያለው አድርጎ ማሳደግ ደግሞ እጅግ አስቸጋሪ የሆነ ጉዳይ ነው ...»

«አይ አንተ!» ካለች በኋላ ኮኮልን በማጽናናት ለመናገር እናት ማዕድ ክፍል ሁና ትጠባበቅ ነበር ። ይሁን እንጂ ድንገት የውጪው በር ቀስ ብሎ ተከፈተና የሌባው ሽማግሌ የዳኒሎ ልጅ ኒኮላይ ቬሶቭሺኮቭ የተሰኘው ሰው ወደቤት ገባ ። ኒኮላይ ከሰው የማይስማማ ለመሆኑ ድፍን የመንደሩ ሰው የሚያውቀው ነው ። ሰውን ሲቀርብ በአኩራፊነት በመሆኑ ምክንያት የሠፈሩ ሰው ብዙም አያቀርበውም ። እናት በመደነቅ መልክ የሚከተለውን ጠየቀችው ፡ —

«ምነው ፤ ምን ነበር ፤ ኒኮላይ?» አለችው ።

ፈንጣጣ የጠቀጠቀው ሰፊ ፊቱን በመዳፉ እየጠራረገና እንደምን አመሹ ሳይልም ፡ —

«ፓቬል የለም እንዴ?» በማለት ቀስ ብሎ ጠየቀ ።

«የለም» አለችው ።

ወደውስጥ ቃኘት-ቃኘት አደረገና ገባ ። ከዚያም ፡ —

«ጓዶች ፤ እንደምን አመሻችሁ!» አለ ።

«እሱም ደሞ?» በማለት እና ባለማመን እናት ወይ ጉድ እያለች ከራሷ ጋር ስትወያይ ፤ ናታሻ ደስ ብሏ

ትና እንኳን ደህና መጣህ በሚል መንፈስ ስትጨብጠው ተመለከተች ።

ከዚያም ገና ሎጋ የሆኑ ሁለት ትንንሽ ወጣቶች መጡ ። ከሁለቱ መካከል አንደኛውን እናት የምታውቀው ሲሆን ፤ እርሱም የፋብሪካ ሠራተኛ ሲዞቭ የተሰኘው ሽማግሌ ዘመድ የሆነው ፌዶር ሲሆን ፊተ-ኮስታራ በረድፍ-በረድፉ ጥቅልል-ጥቅልል እያለ የሚቀመጥ የራስ ፀጉር ያለው እና ግንባረ-ሰፊ የሆነ ነበር ። ሌላኛው ደግሞ ዐይን-አፋር ሲሆን ፤ ፀጉሩንም ወደፊት በልሙጡ አስተኝቶታል ። ከዚህ ቀደም አይታ አታውቀውም ። ቢሆንም ደግሞ አስፈሪ የሆነም አልነበረም ። በመጨረሻም ከሁለት ከምታውቃቸው የፋብሪካ ሠራተኞች ጋር ሁኖ ፓቬል መጣ ። ከዚያም እናቱን በማቆላመጥ እንደሚከተለው ተናገረ ፡ —

«ሳሞቫር ጥዶሻላ? ጎሽ እናመሰግናለን!»

«ወጥቼ ቮድካ ብጤ ልግዛላችሁ?» አለች እናት ፤ አንድ ልትገልጸው ላልቻለችው ጉዳይ ምሥጋናዋን እንዴት እንደምታቀርብ ግራ ባጋባት መንፈስ ።

«የለም ፤ የለም ፤ ቮድካ አንጠጣም!» በማለት በፍቅር ፈገግታ መለሰላት ።

በርሷ ለመሳቅ ብሎ ልጅዋ የነርሱን ስብሰባ አደገኛነት አጋንኖ ያወራላት መስሎ ድንገት ታሰባት ።

«እነዚህ መሆናቸው ነው እንዴ ፤ ሕገ-ወጦቹ ሰዎች?» በማለት ቀስ ብላ ጠየቀችው ።

«እኚሁልሽ እነዚህ ናቸው!» በማለት ፓቬል ወደ ሌላኛው ክፍል አመራ ።

«እሱን ተወው» በማለት በፍቅር አነጋገር እየተከተለችው በመግባት በርኅራኄ አስተሳሰብ በመንፈሷ «አሁንም ገና ልጅ እኮ ነው!» ብላ አሰበች ።





ሳሞቫሩ እንደፈላ እናት ወደ ቤቱ ክፍል ወሰደችው ። እንግዶቹ ጠረጴዛውን ከበው ተቀምጠዋል ። ናታሻም ፋኖሱ ከተሰቀለበት ግድግዳ ሥር ከበስተጥግ በኩል መጽሐፍ በእጅዋ ይዛ ተቀምጣለች ።

«ሰዎች በምን ምክንያት እንደዚህ ዓይነት መጥፎ አኗኗር እንደሚኖሩ ለመረዳት ...» ብላ ናታሻ ገና ንግግሯን ሳትጨርስ ፡ —

«እና ደግሞ ሰዎች ራሳቸውም ለምን እንዲህ መጥፎዎች እንደሆኑ ለመረዳት ...» በማለት ኾኾል በንግግሯ ላይ ጣልቃ ገባ ።

«ማኅበራዊ የሆነውን የአመጣጣቸውን መሠረት መመራመር አለብን» አለች ።

«ተመራመሩ ፤ የኔ ውዶች ፤ ደህና አርጋችሁ ተመራመሩ!» አለች እናት ሻይ እየቀዳች ።

በክፍሉ ውስጥ ያሉት ሁሉ መናገራቸውን አቆሙ ።

«እንዴ ፤ ምነው እናት?» በማለት ፓቬል ኮስተር ብሎ ተናገረ ።

«ምነው?» አለች ። ቀና ብላ ብትመለከት ሁሉም እርሷን እርሷን ይመለከታሉ ። እርሷም በማፈር መልክ የሚከተለውን በማጉረምረም ተናገረች ፡ — «እረ እንደው ነው ። ከራሴው ጋር እያወራሁ ነበር ። መመራመር ከፈለጉ ለምን አይመራመሩም? በማለት ባሳቤ ሳስብ ነው ድንገት የተናገርኩት!» አለች ።

ናታሻ ሳቀች ። ፓቬልም ፈገግ አለ ። ኾኾልም ፡ —

«እምዬ ፤ ላቀረቡልኝ ሻይ አመሰግናለሁኝ» አለ ።

«መቼ ጠጡትና ፤ ጠጥተውት ነው እንጂ ማመሥገን!» አለች ። ከዚያም ወደልጅዋ ተመለከተችና ፡ — «አስቸገርኩኝ መሰለኝ?» በማለት ጠየቀች ።

ናታሻም የሚከተለውን መለሰች ፡—

«እረ ባክዎ እንዲህ አይበሉ ። ምን ማለትዎ ነው ፤ እርስዎ አስተናጋጅ ሁነው እንግዶችን ያስቸግራሉ ማለት ነው እንዴ?»

ከዚያም እንደ ኅፃን ልጅ አጠያየቅም የሚከተለውን ጥያቄ ናታሻ ለእናት አቀረበች ፡—

«የኔ እምወድዎ! ሻይ ቶሎ ይስጡኝ! ብርዱ መላ ሰውነቴ ውስጥ ገብቶ ያንቀጠቅጠኛል ። አካላቴ እንደ በረዶ ቀዝቅዟል!» አለች ።

«አሁን ነው የማመጣው ፤ አሁኑኑ!» በማለት እናት በፍጥነት መለሰች ።

ናታሻ ሻይዋን ከጠጣች በኋላ ጎላ አድርጋ በረዥሙ በመተንፈስ በስተደረቷ በኩል ዘንፈል ብሎ ወርዶ የነበረውን ፀጉሯን ወደጀርባዋ መለስ አደረገችውና በቢጫ ገበታ ተለብጦ ስዕሎች ያሉበትን መጽሐፍ ማንበብ ጀመረች ። እናት ሻይ በምትቀዳበት ጊዜ አንዳችም ድምፅ ሳታሰማ ረጋ ብሎ የሚወርደውን የናታሻን ንባብ ታዳምጣለች ። የናታሻ ወዝ ያልተለየው ድምጿ ሻዩ ከሳሞቫሩ ውስጥ ሲቀዳ በረቂቁ ከሚሰጠው የሙዚቃ ድምፅ ጋር ቅኝቱን አስማምቶ ይንቆረቆራል ። አስደሳች የሆነው ይህ የንባብ መጋረጃ የተገለጠውም ፤ ከረዥም ዘመናት በፊት በዋሻዎች ውስጥ ይኖሩ ስለነበሩና አውሬዎችንም በድንጋይ በመደብደብ ያድኑ ስለነበሩ ጥንታውያን ሰዎች ሁኔታ ነበር ። የእነዚህን ጥንታውያን ሰዎች ታሪክ ሲሰሙት ተረት ይመስላል ። እናቲቱም መላልሳ ልጅዋን በመመልከት እነዚህን የመሳሰሉት ታሪኮች እንዳይሰሙ ሕገ-ወጥ በመሆን የሚከለከሉበት ምክንያት ለምንድነው? ብላ ለመጠየቅ ፈልጋ ነበር ። ይሁን እንጂ ፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ታሪኩን በማዳመጥ መከታተል ስለሰለቻት ልጅዋም ሆነ ሌሎቹ ሳያስተውሏት በክፍሉ ውስጥ ያሉትን እንግዶች ሁኔታ ዝግ ብላ ማስተዋል ጀመረች ።



ፓቬል ከናታሻ ቀጥሎ ተቀምጦአል ። በክፍሉ ውስጥ ከነበሩት ሁሉ መልከ-መልካሙ እርሱ ነው ። ናታሻ መጽሐፏን በማንበብ ከአንገቷ ደፋ ስትል የራሷ ፀጉር ከራሷ ጎን እና ጎን ቅንጦቿ ላይ ዘፍ ብሎ ስለሚወርድ ከራሷ ቀና እያለች ወደ ጀርባዋ ትመልሰዋለች ። ራሷን ነቅነቅ እያደረገችና ድምጿንም ዝቅ በማድረግ አዳማጮቿን በፍቅር ዓይን እየተመለከተች የራሷን አስተያየት በማከል ትጨምራለች ። ኾኾል ከጠረጴዛው አንድ ጥግ በኩል ሰፊ ደረቱን በመዘረር ተቀምጦ ዐይኖቹ በአፍንጫው አኳያ ወደ ታች ቁልቁል እያማተሩ በማድረግ የገዛ ሪዙን የግራና ቀኝ ጫፎች እያሻሸ ለመመልከት ይጥራል ። ቬሶቭሺኮቭ ጉልበቶቹን በመዳፎቹ እያሻሸ እና ፈንጣጣ የጠቀጠቀው ሽፋል-የለሽ ፊቱን ወዲያ-ወዲህ ሳያነቃንቅ ይሁነኝ ብለው እንደተከሉት ምሶሶ እዚያው አለበት ቦታ በመርጋት ቀጥ ብሎ ተቀምጦአል ። ጥልቅ በሆኑት ዐይኖቹ ወደ ሳሞቫሩ አማትሮ ይመለከታል ። ወዲያ-ወዲሁን ሳይቃኝ እና በሳሞቫሩ የብርሃን ነጸብራቅም ዐይኖቹ ቦግ-ድርግም ሳይሉ ቁልጭ ብለው ይመለከታሉ ። እኳኋኑ ትንፋሽ የሚተነፍስም ሰው አይመስልም ። ትንሹ ፌዎዶር መጽሐፉ በሚነበብበት ጊዜ ያንኑ የተነበበውን መልሶ ድምፅ ሳያሰማ የሚያነበንብ ይመስል በተነበበ ቁጥር ከናፍሮቹን ያነቃንቃል ። ሌላኛው ጓደኛው ደግሞ ከወገቡ በላይ ያለ አካሉን ጎንበስ በማድረግ ክርኖቹን ጉልበቶቹ ላይ ፤ ጉንጮቹንም በመዳፎቹ አስደግፎ በማስተዋል ፈገግታ ፈገግ እያለ ተቀምጦአል ። ከፓቬል ጋር የመጣው ከርደድ ያለ ቀይ ፀጉር ያለው ሲሆን አንድ ለመናገር የሚፈልገው ነገር ያለ ይመስል ይቁነጠነጣል ። ሌላኛ

ው ነጭ ፀጉር ያለው እና ፀጉሩንም በአጭሩ የተቀ መቀመው እጁን አዘውትሮ ራሱ ላይ በማሳረፍ ፀጉሩን የሚያሻሽ ሲሆን ፤ መሬት መሬቱን ስለሚ መለከት እናት ፊቱን አታይም ። ክፍሉ በሚያስደንቅ አኳኋን የደስ-ደስ ያለው ሁኖአል ። ከዚህ ቀደም ታይ ቶ በማይታወቅ ሁኔታ የታጀበ ሲሆን ፤ ናታሻ መጽሐ ፉን በምታነብበት ጊዜም ወጣት ሁና ሳለ ጫጫታ የተመላበት የግብዣ ፓርቲ እንደምን የመሰለ እንደ ነበር ፤ ትንፋሻቸው ሁል ጊዜም ቮድካ-ቮድካ ይል ከ ነበሩት ልጆች አንደበት ይሰሙ ስለነበሩት አጸያፊ የሆኑ ንግግሮች እና የባለጌ ቀልዶች ሁኔታ አስ ታወሰች ። ሁኔታዎቹን በማስታወስና ራሷን በራሷም ስላለፈው ጊዜ በመውቀስ ልቧ ታውኮ ድው-ድው አለ ።

ባሏ እንዴት እንዳጫት አስታወሰች ። ከነዚያ ካሳለ ፈቻቸው የግብዣ ፓርቲዎች መካከል በአንዱ ላይ ጨለም ካለው መተላለፊያ ውስጥ አፈፍ አድርጎ ይዞአት ነበር ። ከግድግዳ ጋር ያጣበቃት ። ከዚያም በ ተበሳጨ ድምፅ የሚከተለውን የጠየቃት ፡ —

«ታገቢኛለሽ?»

ከግድግዳው ጋር መላ ሰውነቷን አጣብቆ ስለያዛ ት አሟት የነበረ ከመሆኑም በስተቀር በድርጊቱ ተ ቀይማም ነበር ። እርሱ ግን በሚያሳምም ሁኔታ ጡ ቶቿን እያሻሸ ትኩስ እና ርጥበት ያለው ትንፋሹን ፊቷ ላይ ይተነፍግባት ነበር ። አጣብቆ ከያዛት ቦታ በመገፍተር ተመንጭቃ ለመላቀቅ ሞከረች ።

እርሱም በቁጣ የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«የትነው የምትሄጅው? ስሚ እንጂ! መልሱን አትነ ግሪኝም እንዴ?» አለ ።

በማፈሯ እና እንዲህ በመደፈሯ ትንፋሽ አጥሯት መልስ ለመመለስ አልቻለችም ነበር ።



ከዚያም አንዱ በሩን ከፈት ሲያደርግ ቀስ ብሎ ለቀቃት ።

«እሁድ አማጭ እልካለሁኝ...» አለ ።

ብሎም አልቀረ ፤ ላከ ።

እናት ዐይኖቿን ዘግታ በረዥሙ ተነፈሰች ...

«እኔ ለማወቅ የምሻው ሰዎች ወደፊት እንዴት መኖር እንዳለባቸው ነው እንጂ ፤ ያለፈውን ጊዜያቸውን እንዴት እንደኖሩት አይደለም!» በማለት በመቃወም ዓይነት ድምፅ ቬሶቭሺኮቭ ተናገረ ።

«ልክ ነው!» አለ ቀይ ፀጉር ያለውም ብድግ እያ ለ በመናገር ።

«እኔ በፍጹም አልስማማም!» በማለት ፌዎዶር ጮኸ ።

በሚከራከሩበት ጊዜ ቃላቶች ከአንደበታቸው ዱብ-ዱብ እያሉ እንደ ነበልባል ይንበለበሉ ነበር ። እናት በምን ጉዳይ ላይ እንደሚከራከሩ አልገባትም ። የሁሉ ም መልክ በስሜት ተውጦ የነበረ ሲሆን ፤ በግልፍተ ኛነት የቁጣ መልክ ያሳየ ወይንም ብዙ ጊዜ እርሷ እንደምትሰማው ያለ የብልግና አነጋገር ያሰማ ሰው ግን ከመካከላቸው አንድም አልነበረም ።

«ልጃገረዷቱ ፊት ስለሆኑ የብልግናውን ቃል እር ሱብርሳቸው ለመለዋወጥ አፍረው ይሆናል!» በማለት እናት ገመተች ።

እነዚህን ወጣቶች ገና ሕፃናት እንደሆኑ ዓይነት አድርጋ ሁሉንም በአትኩሮት ስትመለከት በናታሻ ፊት ላይ ያረበበው ኮስታራ ገጽታ እጅጉን አስደሰታት ።

«አንድ ጊዜ ፤ ጓዶች!» በማለት ናታሻ ድንገት ተና ገረች ። ከዚያም ሁሉም ንግግራቸውን አቆሙና እርሷ ን ይመለከቱ ጀመር ።

«ሁሉንም ነገር ማወቅ አለብን በማለት ከእኛ መሃል የተናገራችሁት ጓዶች ልክ ናችሁ ። በዳፍንት

ጭለማ ትግሉን የሚያካሂዱት እኛን ለማየት እንዲች
ሉ የምርምርን ብሩኅ ፋና በእኛ ውስጥ ማብራት አ
ለብን ። ለማንኛውም ነገር ቢሆን ዕውነተኛ እና ትክ
ክለኛ የሆነ መልስ መስጠት አለብን ። ማናቸውንም
ዕውነት እና ማናቸውንም ሀሠት አንጥሮ ማወቅ ያስ
ፈልጋል ...»

ናታሻ ቃላቶቿን ስትጥል ፤ ኾኾልም ከምትሠነዝ
ራቸው ቃላቶች ጋር አስተካክሎ ጭንቅላቱን ይወዘ
ውዛል ። ቬሶቮሺኮቮ እና ባለቀይ ፀጉሩ ፤ እንደ
ዚሁም ከፓቬል ጋር አብሮ የመጣው የፋብሪካ ሠራ
ተኛ በአንድ በኩል ተሰባሰቡ ። ለምን እንደሆነ ባታው
ቀውም ለእናት እነዚህ ሰዎች ደስ አላሰኟትም ።

ናታሻ ንግግሯን ስትጨርስ ፤ ፓቬል ከመቀመጫው
ተነስቶ ቆመ ። ከዚያም በአንድ ወገን የተከማቹትን
ሦስቱን በመመልከት የሚከተለውን በዝግታ ጠየቀ ፡ —

«ለመሆኑ ከርሳችንን መሙላት ብቻ ነው እንዴ
የምንሻው? አይደለም! ከጀርባችን ላይ የታዘሉትን እና
በዐይኖቻችን እንዳናይ አድርገው የሸፈኑንን ሁሉ ፤ ማና
ቸውንም ነገር የምናይ መሆናችንን ማሳየት አለብን ።
እኛ እንከፎች አይደለንም ። ከርሳችንን ከመሙላት በስ
ተቀር ሌላ አንዳችም ነገር የማንሻ አውሬዎችም አይ
ደለንም ። ሰብአውያን ፍጡሮች ሊኖሩ የሚገባቸውን
ዓይነት አኗኗር መኖር እንሻለን ። በባርነት ቀንበር
ጠምደው ቢይዙንም ፤ በተመራማሪነት እኛም ከእነር
ሱ እኩል ልንሆን እንደምንችል ፤ እንደውም ከእነ
ርሱም ልንበልጥ እንደምንችል ለጠላቶቻችን በተጨባ
ጭ ማረጋገጥ አለብን!...»

የልጅዋን ንግግር በምታዳምጥበት ጊዜ እናት ል
ቧ ተነካ ። ኤዲያ ፤ አሳምሮ መናገርንስ ልጄ ይወቅበት!
በማለት አሰበች ።

«ከርሳቸው እንደነጋሪት እስኪቆዘር የሚበሉ አያ



ሌ ሲሆኑ ፤ ዕውነተኞች ግን ጥቂት ናቸው! በዚህ ረግ
ረጋማ በሆነው የአውሬነት አኗኗር ላይ ለወደፊቱ
የሰው ልጆች የወንድማማችነት መንግሥት መሸጋገ
ሪያ የሚሆነውን ድልድይ መመሥረት አለብን ።
ጓዶች ፤ ከፊት-ለፊታችን ተደቅኖ የሚጠብቀን ተግባር
ይህ ነው!» በማለት ኾኾል ተናገረ ።

«የመታገያችን ጊዜ አሁን ከሆነ ፤ እጆቻችንን አ
ጣጥፈን የምንቀመጥበት ምክንያት ምንድነው?» በማለት
ቬሶቮሺኮቮ በተቃውሞ መልክ በማጉረምረም ተናገረ ።

ስብሰባቸው ያበቃው ዕኩለ-ሌሊት አልፎ ውድቅቱ
ላይ ነበር ። መጀመርያ ቀድመው ከቤት የሄዱት ቬሶ
ቮሺኮቮ እና ባለቀዩ ፀጉር ሲሆኑ ፤ ይኽ ሁኔታም
እናትን አላስደሰታትም ነበር ።

«ምነው ተቻኮሉ!» በማለት እና ከሙሉ ልብ ባል
ሆነ ሰላምታ አሰጣጥ እናት ተሰናበተቻቸው ።

«ናሆድካ ፤ ትሸኘኛ የለም እንዴ?» በማለት ናታሻ
ኾኾልን ጠየቀችው ። ኾኾልም ፡ —

«እንዴታ ፤ እሸኝሻለሁኝ» በማለት መለሰ ።

ናታሻ ካፖርቷን ማዕድ ቤት ሁና ስትለብስ ፤ እና
ት የሚከተለውን ተናገረች ፡ —

«የእግር ሹራቦችዎ ለእንደዚህ ዓይነቱ ክረምት
አይሆኑም ። ስሶች ናቸው ። ሱፍ እግር ሹራቦች ልሥ
ራልዎትን?» አለቻት ።

«አመሰግናለሁኝ ፤ ፔላጌያ ኒሎቭና! ሱፍ እግር ሹ
ራቦች የሰው እግር ይቧጥጣሉ!» በማለት ናታሻ ፈገ
ግ ብላ መለሰች ።

«እኔ የምሠራልዎት የማይቧጥጥ ዓይነት ነው»
በማለት እናት ተናገረች ።

ናታሻ የዐይኖቿን ሽፋሽፍቶች የመጨፈን ያህል
አቀራርባ በማጋጠም እናትን ተኩራ ትመለከታት ጀ
መር ። ይኽ አመለካከቷም እናትን ግራ አጋባት ።

«ቂላ-ቂል በመሆኔ ይቅርታ ያድርጉልኝ ። እኔ የጠየቅሁዎት ከልቤ ነው!» በማለት እናት በቀስታ ተናገረች ።

«እርስዎ በጣም ተወዳጅ ነዎት!» በማለት ናታሻም እናትን በእጆቿ አጥብቃ በመጨበጥ ቀስ ብላ ተናገረች ።

«እምዬ ፤ ደህና ይደሩ!» በማለት ኾኾል ናታሻን ለመድረስ በሩን ሲወጣ እናትን ዐይን-ዐይኗን እየተመለከተ ተናገረ ።

እናት ልጅዋን ተመለከተች ። ፈገግ ብሎ በራፉ ላይ ቆሞ ነበር ።

«ምን ያስቅሃል?» በማለት ግራ ገብቷት እናት ልጅዋን ጠየቀችው ።

«ምንም የሚያስቀኝ አዲስ ነገር የለም ። እንደው ደስ ስላለኝ ነው!» በማለት መለሰ ።

«እርግጥ ነው ፤ እኔ አሮጊትም ሞኝም ነኝ ። ነገር ግን ደግሞ ፤ ክፉና በጎውን እለያለሁኝ» አለች ትንሽ የተከፋች በመምሰል ።

«ጎሽ ፤ ይኼ ጥሩ ነው! አሁን ጊዜው ብዙ መሽቷልና ብትተኚ ጥሩ ነው!» አላት ።

«አሁን እተኛለሁ!» አለች ።

በጣም ተደስታና ጠረጴዛውን ጉድ-ጉድ በማለት እየዞረች ሻይ ቀርቦባቸው የነበሩትን ዕቃዎች ማነሳሳት ጀመረች ። ደስታዋ ከልኩ አልፎ የነበረ ከመሆኑ የተነሳ ላቧ ይንቆረቆር ነበር ። ሁሉም ነገር ደስ የሚያሰኝ ስለነበረ እና በሰላም ስላበቃም ተደስታ ነበር ።

«ፓቨሉሻ ፤ እንዲህ ያለ ነገር ለማድረግ ማሰብህ ጥሩ ነው ። ኾኾል በጣም ጥሩ ሰው ነው ። ልጃገረዲቷም ጭምር — ኡ-ይ ፤ እንዴት ያለች ብልህ ልጅ ነች እባክህ! ለመሆኑ ምንድነች?» በማለት እናት ጠየቀች ።



«አስተማሪ ነች!» በማለት ክፍሉ ውስጥ እየተንጎራደደ በቀስታ መለሰላት ።

«በጣም ድሀ መሆን አለባት ። ልብሷ ሁሉ ለክረምት የሚሆን ልብስ አይደለም ። በዚህ አለባበሷ ጉንፋን ወዲያው ነው የሚይዛት ። ለመሆኑ ቤተሰቦቿ የት ናቸው?» አለችው ።

«ሞስኮ ናቸው» በማለት ፓቬል መለሰላት ። ከዚያም ኮስተር ብሎና በቀስታ አነጋገርም የሚከተለውን ነገራት ፡ —

«ይኸውልሽ እንግዲህ ፡ አባቷ ሃብታም ነው ። ብረታብረቶች ይነግዳል ። የሚያከራያቸው አያሌ ቤቶችም አሉት ። አሁን የምትጓዘውን የህይወቷን አቅጣጫ ለኑሮዋ መመርያ አድርጋ በመምረጧ አባትየው ከዳት ። አስተዳደጓ በሞቀ በደመቀ ፤ ሲሳዩ በተትረፈረፈ ቤት ውስጥ ነበር ። ሁሉም በእጅዋ ሁሉም በደጅዋ ተርፎ ይገኝ ነበር ። አሁን ግን ይኸው እንዲህ ብቻዋን በጭለማ ሰባት ቬርስታ* ርቀት በእግሯ ትጓዛለች...»

ይኸንን በመስማቷ እናቱ በድንጋጤ ተዋጠች ። ዐይኖቿን በልጥጣ በመክፈት የግንባሯን ቆዳ ሸብሽባና ልጅዋንም ዐይን ዐይኑን እየተመለከተችው ከቆመችበት መሀል ቦታ ላይ ተገትራ ቀረች ። ከዚያም ዝግ ባለ አነጋገር የሚከተለውን ጠየቀችው ፡ —

«አሁን ወደከተማ ነው የሄደችው?»

«አዎን» አላት ።

«ውይ! ውይ! አትፈራም እንዴ?»

«አንቺ ራስሽም አይተሻት የለም እንዴ? አትፈራም» አላት ፓቬል እየሳቀ ።

«ግን ለምን ሄደች? እዚሁ ቀርታ ከኔ ጋር ታድር ነበርኮ?» በማለት እናት ተናገረች ።

---

* ቬርስታ ፡ — የርቀት መለኪያ ነው ። 1 ቬርስታ ከ 1 ኪሎ ሜትር ትንሽ በለጥ ይላል ። (ተርጓሚው)

«ይኸ ሊሆን አይችልም ነበር ። ጢት ሰዎች ሊያዩዋት ይችላሉ ። ይኸ እንዲሆን ደግሞ አንፈልግም» አላት ።

እናት በሃሣብ ተውጣ ውጪ ውጪውን በመስኮት በኩል ታስተውል ጀመር ። ከዚያም ፡ —

«ፓቬል ፣ አደጋው የቱ ላይ እንደሆነና ፣ ክልክልነቱስ የቱ እንደሆነ እኔ ሊገባኝ አይችልም ። የምትፈጽሙት ስሕተተኛ ተግባር የለም ። ለመሆኑ ስሕተት ትፈጽማላችሁ እንዴ?» በማለት ጠየቀችው ።

የሚያሳስባት ጉዳይ ይኸ ነበር ። ስለዚህም ትክክለኛውን ማረጋገጫ ልጅዋ እንዲነግራት ፈለገች ። እርሱም በተረጋጋ መንፈስ እና ዐይን-ዐይኖቿንም እየተመለከተ የሚከተለውን መለሰላት ፡ —

«የለም ፣ ስህተት አንፈጽምም ። ያም ሁኖ ግን ፣ አንዱን ቀን ሁላችንም እሥር ቤት እንገባለን ። ይኸንን ማወቅ አለብሽ ...» አላት ።

እጆቿ ተንቀጠቀጡ ። ዝግ ባለ አነጋገርም የሚከተለውን ጠየቀችው ፡ —

«ምናልባትም ደግሞ — የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ታክሎበት እሥር-ቤት ከመግባት ትድኑ ይሆናል?» አለችው ።

«የለም ። እኔ በውሸት አንቺን ልሸነግልሽ አልሻም ። እሥር-ቤት ከመግባት አናመልጥም!» አላት ።

ፈገግ አለ ።

«ሂጂና ተኚ ። ደክሞሻል ። ደህና እደሪ!» አላት ።

ብቻዋን ሁና ሳለ ፣ ወደመስኮቱ አጠገብ ሂዳ ውጪ-ውጪውን ትመለከት ጀመር ። ውጪው ብርዳማና ጭጋጋማ ነው ። ዘመም ብለው ከቆሙት ትንንሽ ጎጆዎች ላይ የተከመሩትን በረዶዎች ነፋሱ ከግድግዳ-ግድግዳ እያጋጨና መሬት ሲደርሱም የፉጨት ድምፅ



እያሰማ እንደገና እየጠራረገ በመውሰድ በመንገዱ አኳያ ያንከወክዋቸዋል ።

«ፈጣሪዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! ይቅር በለን!» በማለት ቀስ ብላ ተናገረች ።

ልቧ በሀዘን ተሰበረ ። ቢራ-ቢሮ በምሽት ሰተት ብላ ወደቤት ድንገት እንደምትገባ ሁሉ ፣ ልጅዋ ፓቬል በተረጋጋ ሙሉ ልብ ወደፊት ይጠብቀናል ብሎ የነገራት የመከራ ጊዜም ድንገት ሰተት ብሎ ከሠራ አከላቷ በመግባት አሸበራት ። ከፊት-ለፊቷ በረዶ የተጋገረበት ጉብታ ያለ መስሎ ታያት ። አንድ ነጭ አውሎ ነፋስ በጉብታው በኩል እየነፈሰ በረዶውን በመበታተን ወደላይ በቀጭኑ አሞልሙሎ ሲያወጣው የታያት መሰላት ። ከጉብታማው ቦታ መሀከሉ ላይ ጥቁር ልብስ የለበሰች አንዲት ትንሽ ልጃገረድን ነፋሱ ከወዲያ-ወዲህ ያንገላታታል ። ነፋሱ ጥቅልል ብሎ እግሯ ሥር እየነፈሰ ከገባ በኋላ የለበሰችውን ቀሚስ በመገላለብ በቅዝቃዜው ተናዳፊ የሆነውን በረዶ ፊቷ ላይ ያርከፈክፈው ጀመር ። የልጅ እግሯ በበረዶው ክምር ውስጥ ጥልቅ-ጥልቅ እያለ መራመድ ስለተሳናት የምትጓዘው በችግር ነው ። ቀዝቃዛ እና አሥፈሪ ውድቅት ነበር ። በዚህ አበላሽና አጥፊ በሆነው የበልግ ነፋስ ውስጥ አንድ ብቻዋን ሁናና አዘንብላ እንደቆመች አክርማ ፤ ከሰውነቷ ጎበጥ ብላ ዊን-ዊን በማለት ትራመድ ነበር ። በስተቀኟ በኩል ከረግረጋማው ቦታ አንስቶ ተንጣልሏል ። ክረምት በመሆኑ ምክንያት ቅጠሎቻቸው ከላያቸው ላይ የረገፉባቸው ቤርዮዝካ የተሰኙትን ዛፎች ፣ እና አሲና የተሰኙትን ዛፎች ደግሞ ነፋሱ በላያቸው ሽው እያለባቸው ያፏጫሉ ። ከሩቅ ባሻገር የከተማው ብርሃን ብዥ-ብዥ ሲል ይታያል ።

«ቸሩ መድሃኔ ዓለም ፣ ምህረትህን አውርድልን!»

በማለት በፍርሃት እየተንቀጠቀጠች እናት ቀስ ብላ ተናገረች ።

7

ቀናቱ ሳምንታትን እየወለዱ ፣ ሳምንታትም ወራትን እየወለዱ ልክ አንገት ላይ እንደሚታሠሩ የጌጥ ዶቃ ዎች አንዱ ቀን በሌላው ቀን ላይ እየተደራረበ ይገ ሠግሥ ጀመር ። ሁልጊዜ ቅዳሜ-ቅዳሜ የፓቬል ጓደኞ ች እርሱ ቤት ይሰበሰቡ የነበረ ሲሆን ፣ እየአንዳንዱ ስብሰባም ፤ አንድ በሩቅ ከታቀደ ዓላማ ላይ ለመድረስ ከፍተኛ ርዝማኔ ባለው የመወጣጫ ደረጃ በኩል ሰዎች ዝግ ብለው ደረጃውን አንድ-በአንድ እያሉ እንደሚወጣጡት ዓይነት ነበር ።

ቀድሞ ይሰበሰቡ በነበሩት ሰዎች ላይ ሌሎች አዳዲስ ሰዎችም ታከሉባቸው ። ቭላሶቭ ቤት ውስጥ የምትገኘው ትንሽ ክፍል ጢቅ ብላ በሰዎች ትመላ ጀመር ። ናታሻ ሁል ጊዜም ስትመጣ ደክሟትና በር ዷት ሲሆን ፣ ሁልጊዜም ደግሞ ደስተኛ ሁና ትታይ ነበር ። የፓቬል እናት ለናታሻ የእግር ሹራቦች ሠር ታላት ፤ እርሷው ራሷ እግሯ ውስጥ አጠለቀችላት ። ናታሻ ሳቀች ። ይሁን እንጂ ድንገት በዝምታ ተውጣ ታስብ ጀመር ።

ከዚያም ዝግ ባለ የቀስታ አነጋገር የሚከተለውን ተናገረች ፡ —

«አንድ ጊዜ ልክ እንደርስዎ ደግ የነበረች አሳዳ ጊ ሞግዚት ነበረችኝ! ይገርማልኮ ፣ ፔላጌያ ኒሎቭና ፣ አዩ ፣ የሠርቶ-አደሮች አኗኗር ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ ከፍተኛ ችግር የተመላበት አኗኗር ነው ። ያም ሆኖ ግን ከነዚያ ከሌሎቹ ሰዎች ይበልጥ ደጎች ናቸው» በማለት «እነዚያ ሰዎች» ያለቻቸውን ለማሳየት በሩቅ-በ ሩቅ አመለከተች ።



«ይቼውልዎት እንግዲህ ፣ ከወላጆችዎ ተነጥለው እንዲህ ብቻዎን ነው ያሉት ማለት ነው...» ካለች በኋላ እናት ንግግሯን መጨረስ አቅቷት ነበር ፤ ይሁ ን እንጂ የናታሻን ፊት በምትመለከትበት ጊዜ አንድ ምክንያቱ ላልገባት ነገር ምሥጋና ለናታሻ ለማቅረብ ከጀላት ። ወለሉ ላይ ከናታሻ ፊት ለፊት ቁጭ አለች ። ናታሻም ፈገግ በማለት ከአንገቷ ጎንበስ ብላለች ።

«ሀ! ከወላጆችሽ ተነጥለሽ አሉኝ?» በማለት ናታሻ የእናትን አነጋገር ደግማ አነሳች ። ከዚያም ፡ — «ይኼ ንን ከምንም አልቆጥረውም ። አባቴ ክፉ ሰው ነው ። ወንድሜም እንደርሱ ክፉ ነው ። ጠጪም ጭምር ነው ። ታላቅ እህቴ በኑሮዋ ደስተኛ አይደለችም ። ከእርሷ በዕድሜ ብዙ ዓመት የሚበልጣትን ነው ያገባችው ። ባሏ ሀብታም ቢሆንም በጣም ቆንቋና ስስታም ነው ። እናቴ ግን ፣ በጣም ታሳዝነኛለች ። ልክ እንደርስዎ ቅን ሴት ነች ። እንደጥንቸል ትንሽ ነች ። ልክ እንደጥንቸል ፈጣን ስትሆን ፣ ያየችውን ሁሉ ትፈራለች ። እንዲህ እንዳይመስልዎት ፣ አንዳንድ ጊዜ እርሷን ለማየት እን ዴት መሰለዎት የምጓጓው!» አለች ።

«አይ የኔ ምስኪን!» አለች እናት ራሷን በሀዘን ስሜት በማወዛወዝ ።

ናታሻም ወዲያው ፈጥና ራሷን ቀና አደረገች ። አንዳች ነገርን ወገድ ከዚህ ብላ እንደምትገፋ ዓይ ነት እጅዋን አንቀሳቀሰችና የሚከተለውን ተናገረች ፡ —

«አይደለም ፣ አይደለም ። አንዳንዴ በጣም እደሰታለ ሁኝ — እጅግ በጣም እደሰታለሁኝ!» አለች ።

ፊቷ ፍም መሰለ ፣ ሰማያዊ ዐይኖቿም ቦግ-ቦግ አሉ ። እጆቿን በእናት ትከሻዎች ላይ አሳርፋ የሚከ ተለውን በዝግታ እና ስሜት በሚቀሰቅስ አባባል ተናገረች ፡ —

«እንደምን ያለ ታላቅ ተግባር በማከናወን ላይ

መሆናችንን የሚያውቁ ቢሆኑ ኖሮ ፣ የተገነዘቡ ቢሆኑ ኖሮ ይኸንን ባላሉም ነበር!» አለች ።

ቅናት ነው ሊባል ምንም ያልቀረው ዓይነት ስሜት በፔላጌያ ቭላሶቫ ልብ ውስጥ አደረ ። ከወለሉ ላይ እየተነሳችም በትካዜ ስሜት የሚከተለውን ተናገረች ።

«እኔማ ለማወቁም ለመገንዘቡም አሮጊት ነኝ ። ወዲህም ደግሞ ያልተማርኩ መሀይሚት ...» አለች ።

አሁን ረዘም ላለ ጊዜ እና በሞቀ ክርክር ብዙውን ንግግር የሚያሰማው ፓቬል ነው ። ከጊዜ ጊዜም እየከሳ በመሄድ ላይ ነው ። ናታሻን ሲመለከትና ከርሷ ጋርም ሲነጋገር አተኩረው በኩስታራነት ተመልካች የሆኑት ዐይኖቹ ረገብ ይላሉ ፣ ድምፁም ይበልጥ ዝቅ ይላል ፣ ጠባዩም የረጋ ይሆናል ።

«አይ ፣ ፈጣሪዬ በዚሁ እንዲቀጥል አድርግልኝ!» ብላ እናት በልቧ አሰበች ። ፈገግም አለች ።

በስብሰባቸው ላይ የሚያደርጉት ክርክር እጅግ የተሟሟቀ እና ጩኸቱም የበረታ በሆነ ቁጥር ፣ ኾኾል ከተቀመጠበት ብድግ በማለት እንደደወል ምላስ ከወዲያ-ወዲህ በመወዛወዝ ግልጽ እና በጎ የሆኑ ጥቂት ቃላቶችን ጣል ያደርጋል ። ይኸ ንግግሩም በክፍሉ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም በመረጋጋት ቀዝቀዝ እንዲሉ እና በጥሞና እንዲያተኩሩ ያደርጋቸዋል ። ቅፍፍ ያለው የሚመስለው ቬሶቭሺኮቭ ሁልጊዜም ሌሎችን አንድ ነገር እንዲያደርጉ ይጠይቃል ። ክርክሮቹን ሁሉ የጀመሩት እርሱ እና ሳሞይሎቭ የተሰኘው ባለቀዩ ፀጉር ናቸው ። ራሰ ሞላላ የሆነውና በአሻቦ ጨው የታጠበ የሚመስለው ኢቫን ቡኪንም የነርሱን ሃሣብ ደጋፊ ነው ። ለስላሳ እና ንጹህ የሆነው ያኮቭ ሶሞቭ የተናገረው ትንሽ ሲሆን ፣ ንግግሩ ግን ኮስተር ባለ ድምፅና በቁም-ነገር የተመላ ነው ። እርሱ



እና ግንባረ-ረጃጅሙ ፌዎዶር ማዚን ሁልጊዜም ፓቬልን እና ኾኾልን ይደግፋሉ ።

አንዳንድ ጊዜ በናታሻ ምትክ ኒኮላይ ኢቫኖቪች የተሰኘው ፤ የዐይን መነጽር የሚያደርግና አነስ ያለ ነጭ ጢም ያጤመው ሰው ለስብሰባው ይመጣል ። የትውልድ ቦታው ራቅ ካለ ጠቅላይ ግዛት ሲሆን ፣ ባነጋገር ሥልታቸው ደግሞ የሚናገሯቸውን ቃላቶች «ኦ» በሚል ፊደል በመደምደማቸው የታወቁ ሕዝቦች ከሚኖሩበት ጠቅላይ ግዛት ነው ። እንደው በጠቅላላ «የዳር አገር ሰው» ነበር ። የሚያቀርባቸው ንግግሮች ሁሉ የተመሠረቱት ሰዎች የዕለት-በዕለት ኑሮዋቸውን ለመኖር በሚያስፈልጓቸው ተራ በሆኑ ነገሮች ላይ ነበር — ስለቤተሰብ አኗኗር ሁኔታ ፣ ስለሕፃናት ፣ ስለንግድ ፣ ስለፖሊሶች ፣ ስለ ዳቦ እና ሥጋ ዋጋ እነዚህን በመሳሰሉ ነገሮች ላይ ነበር ። ይኸንን ገለጻ በማድረጉም ፣ ትክክለኛ ያልሆነውን ፣ ጅላ-ጅል እና አስቂኝ የሆነውን ሁሉ ፣ ነገር ግን ደግሞ ሰፊውን ሕዝብ ጎጂ የሆነውን ሁሉ ይናገር ነበር ። ሰው ሁሉ ደምበኛ እና ሀቀኛ የሆነ አኗኗር ከሚኖርበት ሩቅ ከሆነ ቦታ የመጣ ሰው መሆን አለበት በማለት እናት ገምታለች ። እዚህ አሁን የሚገኝበት አካባቢ ያለው አኗኗር ሁሌ ግራ ያጋባው ከመሆኑም በስተቀር ሊለምደው የማይችለው እና ከቶውንም የማይቀበለው ዓይነት አኗኗር ሁኖበታል ። የአኗኗሩን ዓይነት ጠልቶታል ። ይኸ ጥላቻውም የረጋ እና አንድ የፀና መንፈስን ያሳደረበት ሲሆን ይኸውም ሁኔታዎችን ለርሱ በሚስማማ ዓይነት ለመለወጥ የመሻቱ መንፈስ ነው ። ፊቱ ቢጫማ ነው ። ከዐይኖቹ በላይም ቀጫጭን መሥመሮች ተጋድመውበታል ። ድምፁ ለስላሳ ሲሆን እጆቹ ደግሞ ሁልጊዜም ሞቃት ናቸው ። ፔላጌያ ቭላሶቫን ሲጨብጣት ሁልጊዜም እጅዋን ሙሉ-በሙሉ ግጥም አድርጎ በመጨበጥ

ሲሆን ፣ ይኸንን ከመሰለ የእጅ ለእጅ መጨባበጥ በኋላም እናት ልጧ ረግቶ ትዝናናለች ።

በእነዚህ ስብሰባዎች ላይ ሌሎችም ሰዎች ከከተማ ይመጣሉ ። ከእነዚህ ሰዎች መካከል አዘውትራ ትመጣ የነበረችውም አንዷት ረዥም እና ሸንቃጣ የሆነች ፍም የመሰለ መልክ ጎላ-ጎላ ያሉ ዐይኖች ያሏት ልጃገረድ ነበረች ። ስሟም ሳሻ ይባላል ። አረማመዷ እና እንቅስቃሴዋ ልክ እንደወንድ ነው ። ስትናገር በመኮሳተር መልክ ሁለቱንም ቅንድቦቿን ወደላይ በልጠጥ አድርጋ ትሸበሸባቸዋለች ። እንደስንደዶ ቀጥ ብሎ በርዝመት የወረደው የቀዳዶች አፍንጫዋ ጠባብ ቀዳዶች በምትነጋገርበት ጊዜ ይርገበገባሉ ።

«እኛ ሶሻሊስቶች ነን» በማለት ለመጀመሪያ ጊዜ ጉልህ እና ግልጽ በሆነ ንግግር ያስታወቀችው እርሷ ነበረች ።

እናት ይኸንን አባባል ስትሰማ በዝምታ እና በመደነቅ ስሜት ልጃገረዷቱን ተመለከተቻት ። ከዚህ ቀደም ዛርን* የገደሉ ሶሻሊስቶች መሆናቸውን እናት በወጣትነቷ ሰምታለች ። ዛሩ ፣ ገባሮችን ከመሬት መኳንንት የበላይ ገዢነት አላቅቆ ነፃ ስላወጣቸው ፣ ይኸንን ቁጭታቸውን በዛሩ ላይ እስኪልተበቀሉ ድረስ ፀጉራቸውን ላይቆርጡ እርስ-በእርሳቸው ተማምለው ነበር የሚባል ወሬ በዚያን ጊዜ ተወርቶ ነበር ። ሶሻሊስቶች የተባሉትም በዚህ ምክንያት ነበር ። አሁን ደግሞ ልጅዋና ጓደኞቹ ራሳቸውን ሶሻሊስት ብለው ለምን እንደሚጠሩ እናት ግራ ገብቷታል ።

ሰዎቹ በሙሉ ከሄዱ በኋላ ፓቬልን እንደሚከተለው ጠየቀችው ፡ —

* ዛር ፡ — የሩሲያ ንጉሠ ነገሥታት መጠርያ ነው ። (ተርጓሚው)



«ፓሻ ! አንተ ሶሻሊስት ነህ እንዴ?»

እንደወትሮው ፊት-ለፊቷ ቀጥ ብሎ እና ጠንከር ብሎ በመቆም ፡ —

«አዎን ፣ ነኝ ። ምነው?» አላት ።

እናቱም በረዥሙ ተነፈሰችና ዐይኖቿን ከርሱ ላይ መለስ አድርጋ የሚከተለውን ጠየቀችው ፡ —

«ፓቬል ፣ ዕውነትክን ነው እንዴ? ሶሻሊስቶች እኮ ዛሩን የሚቃወሙ ናቸው ። እንደውም ከዚህ ቀደም አንድ ዛር ገድለዋል» አለችው ።

ፓቬልም አገጩን በእጁ እያሻሸ የነበሩበትን ክፍል በመንጎራደድ እና አጠር ያለ ሳቅ እየሳቀ የሚከተለውን መለሰላት ፡ —

«እኛ እንደዚህ ያሉ ነገሮችን ማድረግ አንሻም!» አላት ።

ከዚያም መራራ በሆነ እና ረጋ ባለ ድምፅ ረዘም ላለ ጊዜ አወራላት ። እርሷም ፊት-ፊቱን እየተመለከተች በሃሣቧ የሚከተለውን አሰበች ፡ —

«እንዲህ ያለ አንዳችም ስህተት አይፈጽምም ። እረ አያደርገውም!» በማለት አሰበች ።

ከዚያ በኋላ ይኸ አስፈሪ የሆነ «ሶሻሊስት» የተሰኘ ቃል በቤታቸው እስኪሰለች ድረስ በተደጋጋሚ ይሰማ የነበረ ሲሆን ፣ እንደሌሎቹ እንግዳ እንደነበሩት ቃላት ስለለመደችው በቃሉ አጠራር አትደነግጥበትም ። ይሁን እንጂ ሳሻን አልወደደቻትም ። እርሷ ስትኖርም መንፈሷ ከመረበሹም በስተቀር ቅር ይላታልም ።

ባለመደሰት መንፈስ ከንፈሮቿን ግጥም ካደረገች በኋላ ስለ ሳሻ ያላትን አስተያየት አንድ ቀን ለኾኾል ነገረችው ፡ —

«ሳሸንካ* በሃሣበ ጽኑነት ግትር ነች! ሁሉንም ታዝ

* ሳሸንካ ፡ — ሳሻ የሚለው መጠርያ ተቆላምጦ ሲጠራ ነው ። (ተርጓሚው)

ዛለች ። ይኸን አድርጉ! ያን አታድርጉ! ትላለች» አለችው ።
ኾኾል ልቡ ተነክቶ በመንከትከት ሳቀ ። ከዚያም ፡—
«እምዬ ፣ እርስዎ እንደው የዝምብ ጠንጋራም ቢሆን ለይተው ያውቃሉ ማለት ነው! አይደለም እንዴ ፣ ፓቬል?» በማለት ፓቬልን ከጠየቀ በኋላ ፣ ዐይኖቹን ብልጭ-ድርግም በማድረግም ቀጠል አድርጎ «ይኸ የ እርስዎ ክቡርነት ነው!» በማለት እናትን ተናገረ ።
ፓቬልም ድርቅ ባለ አነጋገር ፡—
«ጥሩ ልጅ ነች» አለ ።
ኾኾልም የፓቬልን አባባል እንደገና በማረጋገጥ የሚከተለውን ተናገረ ፡—
«እርግጥ ነው ጥሩ ልጅ ነች ። ነገር ግን አንድ ነገር እርሷ አትገነዘብም ። ይኸውም እርሷ አንድን ነገር ማድረግ 'አለብኝ' ባይነች ። እኛ ደግሞ ያንኑ ነገር መደረግ 'ይቻላል' ፣ ልናደርገውም 'እንችላለን' ነው የምንለው!» በማለት መለሰ ።
ከዚያም እናት በማወቅ ልትደርስበት በማትችለው ሁኔታ ስለአንድ ጉዳይ መከራከር ጀመሩ ።
ሳሻ በፓቬል ላይ ይበልጥ ግትርና ጠንካራ እንደ ሆነች እናት ተገንዝባለች ። እንደውም አንዳንድ ጊዜ በቁጣ ትጮህበታለች ። በዚህን ጊዜም ፓቬል ምንም አይልም ። በናታሻ ላይ እንደሚያደርገው ሁሉ ለስለስ ባለ አመለካከት እየተመለከታት ብቻ ይስቃል ። እናት ደግሞ ይኸን የልጃገረዲቱን ሁኔታ አልወደደችም ።
አንዳንድ ጊዜ እክፍሉ ውስጥ የተሰበሰቡት በሙሉ ፣ ድንገት በደስታ ማዕበል ተውጠው ሲታዩ እናት ሁኔታውን እያየች ትደነቃለች ። ብዙውን ጊዜ ይኸንን ዓይነቱ ሁኔታ የሚደርሰው የውጭ ሀገር ወዝ-አደሮችን እንቅስቃሴ ስለሚመለከቱ ጉዳዮች ጋዜጣዎችን ማታ-ማታ በሚያነቡበት ጊዜ ነው ። ከዚያም ዐይኖቻ



ቸው በደስታ ፈክቶ ግልፅ እና ጉልህ የሆነ ሳቃቸውን በመሳቅ እርስ-በርሳቸው በፍቅር ስሜት ትከሻ ለትከሻ እየተጓሸሙ ልክ እንደሕፃን ልጅ አኳኋን በደስታ ፍንድቅድቅ ይላሉ ።
ደስታውን እንደመጠጥ ጠጥቶት የሠከረ ያሕል ከመካከላቸው አንዱ ፡—
«እንዲህ ነው ፣ የጀርመን ጓዶች!» በማለት ይጮሃል ።
«የኢጣልያን ወዝ-አደሮች ለዘለዓለም ይኑሩ!» በማለት ደግሞ በሌላ ቀን ይጮሃሉ ።
እንደዚህ የመሳሰሉ የደስታ መግለጫ መልካም ምኞቶቻቸውን ከእነርሱ ብዙ ርቀው ለሚገኙት እና ማንነታቸውንም ለማያውቋቸው ቋንቋቸውንም ለማይገባቸው ወዝ-አደሮች ደስታ በተመላበት ጩኸት ሲያስተላልፉ እነዚህ የማያውቋቸው የሌላ ሀገር ወዝ-አደሮች የሰሙዋቸው እና ደስታቸውንም የተካፈሉዋቸው ያህል እየገመቱ ነበር ።
ኾኾል ዐይኖቹ በደስታ ፍልቅልቅ ብለው የሚከተለውን ተናገረ ፡—
«ለእነርሱ ደብዳቤ መጻፍ ጥሩ ሃሣብ አይደለምን? ሩሲያ ውስጥም እንደእነርሱው በተመሳሳይ ሥራ ላይ የተሠማሩ ወዝ-አደር ጓዶች መኖራቸውን እና ተመሳሳይ የሆነ ዕምነትንም የሚያሠራጩ መሆናቸውን ፣ ተመሳሳይ ለሆነ ዓላማ የሚኖሩ እና ተመሳሳይ የሆነ ድልን ለመቀዳጀት የሚሹ ጓዶች መኖራቸውን እንዲያውቁት ማድረግ ጥሩ ሃሣብ አይደለምን?» አለ ።
ለፈረንሳይ ፣ ለእንግሊዝ ፣ ለስዊድን ወዝ-አደሮችም እንደ ጓደኞቻቸው ፣ የቅርብ እና የልብ ወዳጅ እንደሆኑ ዓይነት ፣ ደስታቸውን እና ሀዘናቸውን አብረው እንደሚካፈሉ አድርገው ተመሳሳይ በሆነ የደስታ መንፈስ ተውጠው ይናገራሉ ።
በዚች ጠባብ በሆነች ትንሽ ክፍል ውስጥ ከመላ

ው ዓለም ወዝ-አደሮች ጋር በወንድማማችነት የመተሳሰብ ስሜት ተፈጥሮባት ነበር ። ይህ ስሜት እናትነ ጨምሮ ሁሉንም የነካ ስሜት ሲሆን ፣ ምንም እንኳን እናት የዚህን ስሜት ምንነት አውጠንጥና መገንዘብ ባትችልም ኃያልነቱን ተረድታው ነበር — ማለትም ይህ ስሜት እጅግ ወጣት የሆነ ፣ ደስታው እንደመጠጥ የሚያሰክር እና የወደፊቱን ብሩኅ ተስፋም የተጎናጸፈ ኃያል ስሜት ነው ።

አንድ ጊዜ ኾኾልን እንደሚከተለው ተናገረችው ፡ —

«ኧረ እንዴት የተባረካችሁ ናችሁ! አይሁዶች ፣ አርመኖች ፣ ኦስትርያኖች ፣ ሕዝቦች ሁሉ ጓዶቻችሁ ናቸው ። ለሁሉም ታዝናላችሁም ትደሰታላችሁም!» አለችው ።

ኾኾልም እንደሚከተለው መለሰላት ፡ —

«የኔ እምዬ! እንዴታ ለሁሉም እንጂ ፣ ለሁሉም! እኛ ከጎሣ ጎሣ እና ከዘር ዘር አንለይም ። እኛ የምንለየው ጓዶችን እና ጠላቶችን ብቻ ነው ። በዓለም የሚገኙ ወዝ-አደሮች ሁሉ ጓዶቻችን ናቸው ። የዓለም ሃብታሞች ፣ የዓለም መንግሥታት ሁሉ ጠላቶቻችን ናቸው ። በዚች ዓለም ላይ ዐይናችንን ገለጥ አድርገን እኛ ወዝ-አደሮች ምን ያህል ብዙ እንደሆንን ስንመለከት ፣ ምን ያህል ጠንካሮች እንደሆንንም ስንገነዘብ ለደስታችን ማብቂያ የለውም ። ልባችንም በታላቅ የበዓል ስሜት ይረካል! አዩ እምዬ ፣ የፈረንሳዩም ሆነ የጀርመኑ ወዝ-አደር ሁኔታዎችን የሚመለከታቸው ልክ እኛ እንደምናደርገው ባለ ሁኔታ ነው ። የጣሊያኑም ቢሆን ፣ ሁሉም ቢሆኑ ። ሁላችንም የአንዲት እናት ልጆች ነን ። ሁላችንም በመላው ዓለም የሚገኙ የሠርቶ-አደሮች ወንድማማችነት የማይናወጹ የጋለ የስሜት ማዕበል ውስጥ ተውጠን እንገኛለን ። ይህ ስሜት ልባችንን በደስታ ያሞቀዋል ። ፍትሕ በሰፈነበት ሁኔታ በሰማዩ ላይ ብርሃኗን እንደምትፈነጥቅ ፀሐይ ማለት ነው ። ያ ሰማይ ደግሞ የወዝ-አደሩ ልብ ነው ። ማንም ሆነ ማን ፣ የፈለገውን ዓይነት መጠርያ ስም ቢኖረው ፣ ትላንትናም ሆነ ዛሬ ፣ ለወደፊቱም ቢሆን እስከዘለዓለመ-ዓለም ድረስ ሶሻሊስት የሆነ ሁሉ የመንፈስ ወንድማችን ነው!» በማለት ተናገረ ።

ይህ የልጅ ስሜት የሚመስል ፣ ነገር ግን እጅግ ጠንካራ የሆነ ስሜት ፣ ልዩ ልዩ በሆኑ መንገዶች ወደማይበገር ኃያልነት በመዳበር ከጊዜ ወደጊዜ በመደጋገም በሁኔታዎቻቸው ላይ ይከሠት ነበር ። እናትም ይኸንን ስትመለከት ፣ ዕውነትም በዓለም ላይ ልክ በዐይኖቿ እንደምታየው እንደ ፀሐይ ታላቅ እና በጎ የሆነ ነገር የተፈጠረ መሆኑ እንዲሁ በስሜት ታወቃት ።

ብዙውን ጊዜ ያዜማሉ ። ማንም የሚያውቃቸውን የዘፈን ዜማዎች ጉልህ እና አስደሳች በሆነ ድምፅ ያዜማሉ ። አንዳንድ ጊዜ ግን ቁም ነገር ያለው መልዕክት የያዙ አዳዲስ መዝሙሮችን ደስ በሚያሰኝ እና ከዚህ ቀደም ባልተሰማ የዜማ ምት ያሰማሉ ። እነዚህን የመሳሰሉትን መዝሙሮች የሚያዜሙት ልክ በዝግታ እንደሚዜም የቤተ-ክርስቲያን ዜማ ዓይነት ቀስ ባለ የለሆሳስ ድምፅ ነው ። የአዚያሚዎቹ ፊቶች በስሜት ፍም የሚመስሉ ሲሆኑ ከአንደበታቸው የሚወረወሩት ቃላትም አዚያሚዎቹ በመንፈሳቸው ታላቅ ኃይል ያበጁ መሆናቸውን ያመለክታሉ ።

እናት እነዚህን ከመሳሰሉት መዝሙሮች መካከል በአንዱ መዝሙር በተለይ ተመስጣለች ። ይህ መዝሙር በተጠራጣሪነት እና ሙሉ-በሙሉ እርግጠኛ ባለመሆን መንፈስ መውጫ መግቢያው ከማይታወቅ ቦታ የምትገኝ የተጎሳቆለች ነፍስ የምታሰማውን ዓይነት ድምፅ የሚያሰማ ዜማ አልነበረም ። ወይንም ደግ

ሞ በእጦት የተጎሳቆሉ ፣ በፍርሃት አዘቅት የተዋጡ ፣
ማንነታቸው እና ሰብአዊ ክብራቸው የተረገጠባቸው
ሰዎች የሚያቀርቡትን እሮሮ የሚያንጸባርቅ አልነበረ
ም ። የጭፍን የዳሰሳ አየርን ለመጨበጥ በሃዘንና በትካ
ዜ ሁኖ እህህ በሚል እንጉርጉሮ አንድ ኃይል እንደ
ሚያሰማው ዜማ ዓይነትም አልነበረም ። አንዱን ከሌ
ላው ሳይለይ በበጎውም በክፉውም ጉዳይ ላይ ተወር
ውሮ ጉብ ሊልበት የሚሻ የአጓጉል ደፋርነት ምል
ክትም አልነበረም ። በቂም በቀል መንፈስ ተነሳስቶ
ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ የነበረውን ለማፈራረስ እንጂ
መልሶ ለመገንባት የማይቻለው መሆኑን የሚያሳይ
ስሜት በመዝሙሩ ውስጥ አይገኝበትም ። በዚህ መ
ዝሙር ውስጥ የቀድሞው የባርነት ዓለም መንፈስ ፡ አ
ይገኝበትም ።

መዝሙሩ በውስጡ የያዛቸውን ኃይለ-ቃላት እና
ኮስታራ ጣዕመ-ዜማ እናት ያልወደደችው ቢሆንም
ቃላቱን እና ጣዕመ-ዜማውን ሸፍኖ ሰውን በሃሣብ
ማዕበል የሚያጥለቀልቅ አንድ ስሜትን ቀስቃሽ የሆ
ነ አንዳች ኃይል በውስጡ ይዞ ነበር ። ይኸንን
አንዳች ኃይል በክፍሉ ውስጥ በነበሩት ወጣቶች
ዐይኖች እና ፊቶቻቸው ላይ ተመልክታለች ።
ይህ አንዳች ኃይል በእነርሱ ውስጥ ሰርጾ የሚገኝ
መሆኑን ከመገንዘቧም በስተቀር ፣ ከቃላቶቹ እና ከጣዕ
መ-ዜማው ባሻገር ከሚገኘው ከዚህ መዝሙር አንዳ
ች ኃይል ሥር ራሷን በማዋል ከማንኛውም መዝ
ሙር ይልቅ ይኸንን መዝሙር በታላቅ ጥሞና እና
በከፍተኛ የስሜት መቀስቀስ እናት ታዳምጠዋለች ።

ይህንን መዝሙር የሚዘምሩት ዝግ ባለ ድምፅ
ቢሆንም ፣ የመዝሙሩ ጣዕመ-ቃና ጎልቶ የሚሰማ ነው ።
የመዝሙሩን ዘማሪዎችም እንደ ጸደይ አየር በአንድ
ነት አዋህዶ የድምጻቸውን ላህይ ያስማማዋል ።



«ይህንን መዝሙር አደባባይ ወጥተን ማዜም አ
ለብን!» በማለት መዝሙሩ በተዘመረ ቁጥር ቬሶቭ
ሺኮቭ ፊቱን አኮሳትሮ ይናገራል ።

አባቱ አሁንም እንደገና በሌብነት ተይዞ እሥር
ቤት በገባ ጊዜ ልጁ ቬሶቭሺኮቭ የሚከተለውን ለጓ
ዶቹ ነገራቸው ፡ —

«ከእንግዲህ እኔ ቤት መሰብሰብ እንችላለን...»

ብዙውን ጊዜ ከሥራ በኋላ ምሽቱ ላይ ከፓቬል
ጓደኞች መካከል አንደኛቸው እቤት በመምጣት ለ
መታጠብ እንኳን ጊዜ አጥተውና ተቻኩለው መጻሕ
ፍትን የሚያነብቡ ከመሆናቸውም በስተቀር የሚያነብ
ቡትንም ምንባብ በጽሁፍ ያሠፍራሉ ። ራታቸውን ሲ
በሉና ሻይም ሲጠጡ መጻሕፍቶችን በእጆቻቸው ይዘ
ው ሲሆን ፣ ስለሚወያዩት ጉዳይ ምንነት ለመረዳትም
ከጊዜ ጊዜ ለእናት እየከበደባት ይሄድ ጀመር ።

«እያተምን የምናወጣው የራሳችን ጋዜጣ ያስፈል
ገናል!» በማለት ፓቬል አዘውትሮ ይናገራል ።

ህይወታቸው ፋታ በማጣት የተጣደፈ እና የተጋጋ
ለ በመሆን ከመገስገሱም በስተቀር ፣ ንቦች ከአንድ
አበባ ወደሌላ አበባ በመዘዋወር ማር እንደሚቀስሙ
ሁሉ ፣ እነርሱም ከአንዱ መጽሐፍ ወደሌላው ፣ ከዚያም
ወደሌላው-ወደሌላው እያሉ ዕውቀትን ይቀስማሉ ።

«ስለእኛ እያወሩ ናቸው ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ይይ
ዙናል!» በማለት ቬሶቭሺኮቭ አንድ ቀን ተናገረ ።

«አሣ የተፈጠረው ወጥመዱ ከሆነው መረብ ው
ስጥ ገብቶ ሊያዝ ነው!» በማለት ኾኾል መለሰ ።

እናት ኾኾልን ከጊዜ ጊዜ ይበልጥ ትወደው ጀ
መር ። ኾኾል «እምዬ» ብሎ በሚጠራት ጊዜ የኅፃን
ለስላሳ እጆች ጉንጯን የሚዳብሷት ያህል ይሰማታ
ል ። ፓቬል እሁድ እሁድ ሌላ ሥራ ላይ ከሆነ ፣
ኾኾል ለእናት እንጨት ይፈልጥላታል። አንድ ቀን

ኾኾል በትክሻው የጣውላ እንጨት ተሸክሞ መጣ ። 
ከዚያም በመጥረቢያ በሚገባ አስተካክለውና በረንዳ
ው ላይ የነበሩትን የበሰበሱ መረማመጃ የእንጨት
ደረጃዎች ነቃቅሎ ይህንን ያመጣውን ጣውላ በምትኩ
ሠራው ። ሌላ ጊዜ ደግሞ አዘንብሎ ሊወድቅ ምንም
ያልቀረውን አጥራቸውን አቅንቶ በደንብ አቆመው ።
እነዚህን የመሳሰሉ ሥራዎችን በሚሠራበት ጊዜ ደስ
የሚያሰኝና ሀዘን የተቀላቀለው የዜማ እንጉርጉሮ በፉ
ጨት ያሰማል ።

«ኾኾልን ከእኛ ጋር አዳብለን ለምን አናኖረው
ም? እርስ-በርሳችሁ ከቤት-ቤት በመፈላለግ ከምትሯሯ
ጡ ለሁለታችሁም ይበጃችኋል» በማለት እናት አንድ
ቀን ልጅዋን ጠየቀችው ።

«ለምን በችግር ላይ ችግር እንዲደራረብብሽ ትፈ
ልጊያለሽ?» በማለት ፓቬል ትከሻውን ነቅንቆ አድርጎ
መለሰላት ።

«የማትረባ ። ከዚህ ቀደም የኖርኩት ኑሮ በሙሉ
ፋይዳ-ቢስ የሆነ ኑሮ ነበር ። እርሱን ለመሰለ ጥሩ
ሰው ብችገር ምናለበት?» በማለት መለሰችለት ።

«እሺ ፥ እንዳልሽ ይሁን ። በበኩሌ ከእኛ ጋር ቢኖ
ር እጅግ ደስ ይለኛል!» አለ ።

ኾኾልም ከእነርሱ ጋር ተዳብሎ መኖር ጀመረ ።

8

ከሠፈሩ ዳርቻ ላይ የሚገኘው ይኸ ትንሽ ቤት
የሰዎችን ዐይን መሳብ ጀመረ ። አያሌ ሰዎች በአጥሩ
በኩል ስግግ እያሉ በጉጉት ለመመልከት ማሾለቅ
ጀመሩ ። ወሬው ከወዲያ ወዲህ ይነፍስ ጀመር ። ፈን
ጠር-ፈንጠር እያሉ ከበስተዳርቻው በኩል በመቆም



ከቶውንም ምን የተደበቀ ምሥጢር እንደሚካሄድ አ
ድፍጦ ለማየት ይሞክራሉ ። በምሽት ደግሞ ሰዎቹ
ወደቤቱ ቮከክ ብለው በመጠጋት በመስኮት ጭላ
ንጭል ውስጡን ለማየት ያሾልቃሉ ። ከመካከላቸው
አንዱ አንድ ቀን የመስኮቱን መስተዋት አንኳኩቶ
ነበር ። ይሁን እንጂ ሁሉም በፍርሃት በረሩ ።

የወይን-ጠጅ ቀለም ያለው ወፍራም ሰደርያ ሁል
ጊዜ የሚለብሰው እና ሰለክላካ በሆነ ደም-መሳይ
አንገቱ ላይም ጥቁር የሀር መንዲል የሚያሥረው የ
ደስ-ደስ ያለው ቤጉንጾቭ የተሰኘ ሽማግሌ የመሸታ-
ቤት ባለቤት ፔላጌያን መንገድ ስትሄድ ድንገት አ
ግኝቶ አቆማት ። ሰልከክ ብሎ በወረደው አፍንጫው
ላይ ፍሬሙ ከኤሊ አጥንት የተሠራ የዐይን መነጽር
ጉብ ብሎበታል ። በዚህ ምክንያትም «ባለአጥንቱ ዐይ
ን» እያለ ሰው ሁሉ በቅጽል ስም ይጠራዋል ።

ሽማግሌው እናትን መንገድ ላይ አግኝቶ እንዳ
ቆማት ፋታ ሳይኖረው እና ከእርሷም አንዳችም ም
ላሽ ሳይጠብቅ የሚከተሉትን ቃላቶች በአንድ ትንፋ
ሽ እያከታተለ ይደረድርላት ጀመር ፡ —

«ጤና ይስጥልኝ ፥ ፔላጌያ ኒሎቭና ፥ እጅጉን እንደ
ምነዎት ፤ ደህናም አይደሉን? ልጅዎስ እንደምንድነው ፤
ደህናም አይደለምን? አሁንም ልጅዎ ሚስት ለማግባት
ገና አላሰበም እንዴ? እንደሚመስለኝ እርሱ በአሁኑ
ጊዜ ለጋብቻ የደረሰ ያሸተ ፍሬ ነው ። ልጆች ቶሎ
ከተዳሩ ለወላጅም ይቀላል ። እንጉዳይን ከኾምጣጤ
ጋር አዋህደው ሲያቀርቡት ልክ ሁኖ ጣዕሙ ተጣ
ጥሞ እንደሚስማማ ሁሉ ፥ ሰውም ጎጆ ወጥቶ ቤተሰ
ብ ሲመሠርት ሥጋው እና ነፍሱ በመጣጣም ይስማ
ሙለታል ። እኔ እርስዎን ብሆን እድረው ነበር ። ይሄ
አሁን የምንኖርበት ዘመን ፥ አንድ ሰው ጊዜውን እን
ዴት እንደሚያሳልፍ በዐይነ-ቁራኛ ሊቆጣጠሩት የሚ

ገባ ዘመን ነው ። በዚህ በጊዜያችን ሰዎች እንዳሻቸው
መኖር ጀምረዋል ። በዛሬው ጊዜ ሰዎች የሚያስቡት
እና የሚፈጽሙት ነገር ሁሉ መላ-ቅጡ የጠፋ ነው ።
ሰዉ እንደሆን ወደ ቤተእግዚአብሔር መሄዱን ትቶ
ታል ። ሰዎች ከሚሰበሰቡባቸው ቦታዎች ራስን በማግለ
ል እና በየስርቻው ሥር በመሽጎጥ እየተንሾኳሾከ
ሁሉም ምሥጢሩን ይመሳጠራል ። እኔ እኮ ግራ ግብ
ት የሚለኝ ፣ ይሄ ሁሉ ምሥጢር መመሣጠር ከቶ
ለምኑ ነው? እያልኩኝ ነው ። ሰው ከሰዉስ ለምን
ይገለላል ። ከቶ ሰዉ ከሰዎች ፊት በይፋ መናገርን
የሚፈራው ምኑን ነው? አሁን ለምሳሌ ከመሸታ-ቤት
ሁኖ በግልጽ ማውራት ምን ነውር አለበት? ወይ ምሥ
ጢር! የምሥጢር ቦታው ቤተእግዚአብሔር ብቻ ነው ።
በየሥርቻው የተወሳ ምሥጢር አዕምሮ በስሕተት የ
ሚፈጽመው ምሥጢር ነው ። ፔላጌያ ኒሎቭና ፣ በሉ
ጤና ይስጥልኝ ፣ በደህና ይዋሉ!» አላት ።

ሽማግሌው ቤጉንጾቭ ንግግሩን ካሰማት በኋላ ባር
ኔጣውን ከራሱ ላይ አንስቶ እናትን እጅ ነስቷትና
ሃሣብ ላይም ጥሏት መንገዱን ሄደ ።

ሌላ ጊዜ ደግሞ የቭላሶቭ ቤተሰቦች ጎረቤት የሆ
ነች ፣ ባሏ ቀጥቃጭ የነበረ የሙት ሚስት ፣ ከፋብሪካ
ው በራፍ ላይ ምግቦችን በመሸጥ ኑሮዋን የምትገ
ፋ ማርያ ኮርሱኖቫ የተሰኘች ሴት ፔላጌያን ገበያ
አገኘቻት እና የሚከተለውን ነገረቻት ፡ —

«ፔላጌያ ፣ ልጅዎን ነቅተው ይጠብቁ!»

«ምነው ፣ ለምን?» በማለት እናት ጠየቀቻት ።

ማሪያ ቀስ ብላ በምስጢር በማሾክሾክ ለእናት
የሚከተለውን ነገረቻት ፡ —

«ወሬው በየቦታው ይነፍሳል ። የኔ እናት ፣ ደስ የማ
ይል ወሬ ነው የሚነፍሰው ። ልጅዎ አንድ የምሥጢ



ር ቡድን ወገን ለይቶ እያቋቋመ ነው ይባላል ። ይኸ
ንን በመሰለው ቡድንም እርስ በእርሳቸው ሊገራረፉ
ነው ይባላል ...» አለች ።

እናትም የሚከተለውን መለሰችላት ፡ —

«አይ ፣ ማርያ ፣ እንደው የሰው ወሬ ነውኮ እባክሽ!»
አለቻት ።

«መቼስ እኔማ እሳት ከሌለ ጭስ አይጨስም ብ
ዬ ነዋ!» በማለት ምግብ ሻጯ ተናገረች ።

እናት እነዚህን ሁሉ ንግግሮች ለልጅዋ ነገረችው ።
ልጅዋ ፓቬል ግን ትከሻውን ብቻ ሲያነቃንቅ ፣ ኾኾል
በቀስታ እና በጥልቀት ሳቀ ። እናትም የሚከተለውን
በማከል ተናገረች ፡ —

«ልጃገረዶቹም ቢሆኑ እኮ በእናንተ ምክንያት ጉ
ዳት ደርሶባቸዋል ። ለማንኛዋም ልጃገረድ ቢሆን የምት
ስማሙና ሳንክ የማይወጣላችሁ ጉብሎች ናችሁ ። ታታ
ሪ ሠራተኞች ከመሆናችሁም በስተቀር ጠጪዎችም
አይደላችሁም ። ነገር ግን ልጃገረዶችን ሁሉ ዞር ብላ
ችሁም አታስተውሏቸውም ። አጓጉል የሆኑ ባለጌ ልጃገ
ረዶች ከከተማ እየመጡ ይገናኟችኋል የሚባል ወሬ
ም ይወራል » አለች ።

«ኧረ ምነው ፣ እባክሽ!» በማለት በማኩረፍ መልክ
ተኮሳትሮ ፓቬል ተናገረ ። ከዚያም ኾኾል በረዥሙ
እየተነፈሰ የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«ኩሬ ውስጥ ያለ ነገር ሁሉ ይከረፋል ። እምዬ ፣
ትዳር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለእነዚህ ለትንን
ሽ ጅሎች እርስዎ በሚገባ ሊያስረዱዋቸው ይችላሉ ።
ከዚያም በኋላ አንገታቸውን ወጥመድ ውስጥ ለመክ
ተት እንደዚህ አይቸኩሉም...» አለ ። እናትም ቀጠል
አድርጋ ፡ —

«አይ የኔ ሸጋ! ኧረ እነርሱ ሁሉንም ነገር ደህና

አርገው ያስተውላሉ ፣ ያውቃሉ ፣ ከጋብቻ ሌላ ታድያ ምን ያድርጉ እንጂ?» አለችው ።

«የሚያስተውሉ-የሚያውቁ ከሆነ ፣ ከዚህ ሌላ የሚያ ደርጉት ነገር አለ!» በማለት ፓቬል መለሰ ።

እናቱም ኮስተር ያለ ፊቱን እየተመለከተች ፣ —

«ለምን አታስተምሯቸውም? ብልህ-ብልሆቹ እዚህ እናንተ ዘንድ እንዲመጡ ጠይቋቸው» አለች ።

«እርባና የለውም» አለ ልጅዋ ድርቅ ባለ አነጋገር ።

«ግን እኮ ፣ ዕውነትም ለምን አንሞክርም?» በማለት ኾኾል ጠየቀ ።

ለዚህ ጥያቄ መልስ ከመስጠቱ በፊት ፓቬል ጥ ቂት ዝም ብሎ ነበር ። ከዚያም ፣ —

«ፍቅረኛ ወዳጅ በማበጀት ጥንድ-ጥንድ እየሆኑ ሽርሽር መውጣት ይጀምራሉ ። ከዚያም ከመካከላቸው ገሚሶቹ ይጋባሉ ። ከእኛ ጋር ያላቸው ግንኙነትም ከዚ ሁ ላይ ያበቃል!» አለ ።

እናት በሃሣብ ተዋጠች ። እንዲህ ጠንካራ የሆነ የመናኝ ባሕታዊ ስሜቱ አሳሰባት ። ሁሉም ቢሆኑ ፣ በዕድሜ ከእርሱ ትላልቅ የሆኑት እንደ ኾኾል የ መሳሰሉት ጓዶች ሳይቀሩ የሚያቀርበውን ምክር ሳያ ስተሁቅሩ እንደሚቀበሉ ታያለች ። ግን ደግሞ የሚፈሩ ት መሰላት ። ጠንካራ በሆነ መንፈሱ ምክንያትም ማና ቸውም ቢሆኑ የማይወዱት መሰላት ።

አንድ ምሽት እናት አልጋዋ ላይ ተኝታ ሳለና ልጅዋ እና ኾኾልም ገና ያነብቡ በነበረበት ወቅት ፣ ድምፅ በሚያሰማው የመኝታ ቤት ክፍሏ አካፋይ በኩል ጎላ ባለ ድምፅ ሲነጋገሩ ሰማች ።

«ይቺን ናታሻን እወዳታለሁኝ» በማለት ኾኾል ድንገት ተናገረ ።

«እንደምትወዳት አውቃለሁኝ!» በማለት ፓቬል ት ንሽ ቆየት ብሎ መለሰለት ።



ኾኾል ከተቀመጠበት ቀስ ብሎ በመነሳት በባዶ እግሩ ወለሉ ላይ በረዥም እግሩ ሲራመድ እናት ሰማች ። ከዚያም በቀስታና በትካዜ ያፏጭ ጀመር ። ከዚያም እንደገና ቀስ ባለ አነጋገር የሚከተለውን መናገር ቀጠለ ፣ —

«እንደምወዳት ተገንዝባ እንደሆነ መቸም እንጃ!» አለ ።

ፓቬል ምንም መልስ አልመለሰም ።

«ምን ይመስልሃል?» በማለት በጣም ቀስ ብሎ ፓ ቬልን ኾኾል ጠየቀው ።

«ተገንዝባዋለች ። እዚህ መምጣቷንም የተወችው በዚህ ምክንያት ነው…» በማለት ፓቬል መለሰ ።

ኾኾል ወለሉን በእግሩ ጫን አድርጎ በመርገጥ እንደገና በቀስታ የሚያፏጨው ፉጨት ቤቱ ውስጥ ይሰማ ጀመር ። በኋላም እንዲህ አለ ፣ —

«ብነግራት ምናለበት?»

«ምኑን ብትነግራት?» አለው ፓቬል ።

«እኔ እርሷን ፣ እኔ …» በማለት ቀስ ብሎ ኾኾል ንግግሩን ጀመረ ።

«ለምን ትነግራታለህ?» በማለት ፓቬል ንግግሩን አቋረጠው ።

ኾኾል ወለሉ ላይ ከወዲያ ወዲህ መራመዱን ማቆሙን እናት ሰማች ። በመሳቅ ላይ ያለ መስሎም ተሰማት ።

«አንዲት ልጃገረድን ብትወዳት ፣ መውደድህን ለእ ርሷ መንገር ያለብህ ይመስለኛል ። አለበለዚያ ምንም ዋጋ የለውም!» አለ ኾኾል ።

ፓቬል የሚያነበውን መጽሐፍ አጠፈው ። ከዚያም ፣ —

«ታዲያ ስለነገርካት ምን እንዲሆን ትፈልጋለህ?» አለው ።

«እንዴት?» በማለት ኾኾል ጠየቀው ።

ከዚያም ፓቬል ቀስ ባለ አነጋገር የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«አንድሬይ ፡ ስለምትፈልገው ነገር ግልጽ ያለ አስ ተሳሰብ እንዲኖርህ ያስፈልጋል ። ለምሳሌ እኔ እንኳ ን ነው ብዬ አላምንበትም ፡ ብቻ ቢሆንም እርሷም ትወድሀለች እንበል ፡ ከዚያም ትጋባላችሁ ። እንዴት ያለ የተስማማ ጋብቻ ነው! እርሷ የተማረች ምህርት ነች ። አንተም ሠርቶ-አደር ነህ ። ልጆች ይወለዳሉ ። አ ንተ ብቻ እንደባርያ ብዙ ብዙ መሥራት አለብህ ። ኑሮአችሁ የዕለት እንጀራ ለማግኘት እና የቤት ኪ ራይ ለመክፈል ሲባል የምታሳልፉት የስቃይ ኑሮ ይሆናል ። ለቆምንለት ዓላማ የምታውሉት አንዳችም ጊዜ አይኖራችሁም ። ሁለታችሁም አንዳችም ጊዜ አይ ኖራችሁም!» በማለት ተናገረ ።

ፀጥታ ሰፈነ ። ከዚያም ፓቬል አሁንም እንደገና መናገር ጀመረ ። ድምፁም በጣም ለስለስ ብሎአል ።

«አንድሬይ ፡ እንዲህ ዓይነቱን ሃሣብ ብትተው ይ ሻላል ። ለእርሷ ሸክም አትፍጠርባት ።»

ፀጥታ ። የግርግዳው ሰዓት መቂናጥ ከወዲያ ወዲህ እየተወዛወዘ ሰኮንዱን ሲቆጥር ቋ-ቋ-ቋ የሚል ቀጭ ን ድምፅ ያሰማል ።

«ግማሹ ልቤ ያፈቅራል ፡ ግማሹ ደግሞ ይጠላል ። አሁን ይኸንንም ልብ ነው ትለዋለህ?» በማለት ኾኾ ል ተናገረ ።

የመጽሐፉ ገጾች መንኰሻኰሽ ጀመሩ ። ፓቬል ንባ ቡን ቀጥሏል ማለት ነው ። እናቱ መተንፈስ እንኳን ፈርታ ዐይኖቿን በመጨፈን ተጋድማለች ። በኾኾል ከልቧ አዘነችበት ። ከርሱ የበለጠ ደግሞ በልጅዋ አዘ ነችበት ።

«የኔ ምስኪን ልጅ!» በማለት አሰበች ።

«ስለዚህ ፤ አንዳችም ነገር ለርሷ መንገር የለብኝ ም ብለህ ነው የምታስበው?» በማለት ኾኾል ፓቬል ን ጠየቀው ።

«አዎን መንገር የለብህም» ብሎ ፓቬል በዝግታ መለሰለት ።

«ጥሩ ፤ እንግዳው አልነግራትም» አለ ኾኾል ። ከጥቂ ት ሰኮንዶች በኋላም ለስለስ ባለና ቅሬታ በተቀላቀ ለው አነጋገር ኾኾል ቀጠል አድርጎ የሚከተለውን ተናገረ ፡ — «ፓቬል ፡ አንተም ልክ እንደኔው ሲደርስብ ህ ትቸገራለህ» አለው ። ፓቬልም ፡ —

«አሁንም እየተቸገርኩ ነው...» አለው ።

የቤታቸውን ግድግዳ ነፋሱ ይወለውለዋል ። ግድግ ዳው ላይ የተሰቀለው ሰዓት መቂናጥ የጊዜውን ሂ ደት ሳያቋርጥ በመንቀሳቀስ ያመለክታል ።

«ቀልዴን እኮ አይደለም የምልህ!» አለው ኾኾል ዝግ ባለ አነጋገር ።

እናት ጭንቅላቷን ትራሱ ውስጥ ደብቃ ድምፅ ሳታሰማ በለቅሶ ትንሰቀሰቃለች ።

ጧት አንድሬይን ከቁመቱ አጠር ብሎና ይበልጥ ም ተወዳጅ ሁኖ ያገኘችው መሰላት ። ልጅዋ ግን ያው እንደዱሮው በቁመቱ ግትር ፤ በአካሉ ቅጥን ፤ እና በአ ኳኋኑም ፀጥ እንዳለ ነበር ። እናት ከዚህ ቀደም ኾኾ ልን ስትጠራው በሙሉ ስሙ በአክብሮት አንድሬይ ኦኒሲሞቪች ብላ ስሙን ከነአባቱ በመጥራት ነበር ። አሁን ግን ሳይታወቃት ስሙን ብቻ በማቆላመጥ በመጥራት የሚከተለውን ተናገረችው ፡ —

«አንድርዬ ፡ መጫሚያህን በጊዜ ብታስጠግነው ይሻ ልሃል ። አለበለዚያ ብርድ በእግርህ ገብቶ ጉንፋን ይይዝሃል!» አለችው ።

«በሚቀጥለው ደሞዝ ላይ ሌላ መጫምያ እገዛለ ሁኝ» አለ እየሳቀ ። ከዚያም ረዥም ክንዱን እናት ትከ ሻ ላይ ድንገት አሳረፈና የሚከተለውን ተናገራት ፡ —

«ምናልባትም እርስዎ ወላጅ እናቴ ሊሆኑ ይችላሉ ። መልከ-መልካም ስላልሆንኩኝ ልጄ ነው ብለው መቀበል ሳይፈልጉ ቀርተው ይሆናል ። አይደለም እንዴ?» አላት ።

መልስ ሳትመልስለት እጁን አሻሸችው ። የምትወደው መሆኑን የሚገልጹ ብዙ ቃላት ልታሰማው ፈልጋ ነበር ። ልቧ በሀዘን ስለተነካባት ከአንደበቷ ቃላት ሊወጡላት አልቻሉም ።

9

ሶሻሊስቶች በሰማያዊ ቀለም የተጻፉ በራሪ ጋዜጣዎችን ያሠራጫሉ የሚል ወሬ በሠፈሩ አካባቢ መወራት ጀመረ ። እነዚህ ጋዜጣዎችም የፋብሪካውን አስተዳደር ክፉኛ የሚያወግዙ ሲሆኑ ፣ በፒተርቡርግ ከተማ እና በደቡባዊው ሩስያ ስለተካሄዱ የሥራ ማቆም አድማዎች ዝርዝር ዜና ያቀረቡ ከመሆናቸውም በስተቀር የፋብሪካው ወዝ-አደሮችንም የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ እንዲችሉ ኅብረታቸውን ያጠነክሩ ዘንድ ጠይቀዋል ።

ከፋብሪካው ደህና የዐበል ገቢ ያላቸው እና በመካከለኛ ዕድሜ ላይ ያሉ ሰዎች በድርጊቱ ተበሳጭተው የነበረ ከመሆኑም በስተቀር ፣ የሚከተለውን ዓይነት አባባልም ያሰሙ ጀመር ፥ —

«እነዚህ ሁከት ፈጣሪዎች! ለእንዲህ ያለ ድርጊታቸውስ ግንባር-ግንባራቸውን መከስከስ ነው» እያሉ በድብቅ የሚበተኑትን ጋዜጦች ለአለቆቻቸው እየወሰዱ ይሰጡ ጀመር ።

ወጣቶቹ ግን በታላቅ ስሜት ጋዜጦቹን ያነቡ የነበረ ሲሆን የሚከተለውን ዓይነት አባባልም ያሰሙ ጀመር ፥ —



«የተጻፈው ሁሉ እርግጥ ነው!»

በየዕለቱ የፋብሪካ ሥራ አካላቸው ድቅቅ ይል የነበሩት አብዛኛዎቹ ወዝ-አደሮች ግን ስለጋዜጣው የሚሰሙትን አስተያየት ሁሉ ባለመደገፍም ባለመቃወምም ዝም ብለው በማዳመጥ የሚከተለውን ይሉ ጀመር ፥ —

«እንደውኮ ነው ፣ ምንም ማድረግ ላይቻል! ማድረግ የሚቻል ነገር አለእንዴ?»

ይሁን እንጂ በራሪ ጋዜጦቹ ሰዎቹን ይቀሰቅሷቸው ጀመር ። ጋዜጦቹ አንድ ሳምንት ሳይታዩ ከቀሩ ፣ —

«አዬ! ጋዜጣዎቹን ማተም አቆሙ መሰለኝ!» በማለት ሰዎቹ እርስ-በርሳቸው ይነጋገራሉ ።

የሚቀጥለው ሰኞ ላይ ግን አዲስ እትሞች ተዘጋጅተው ይሠራጫሉ ። ከዚያም ወዝ-አደሮቹ እርስ-በርሳቸው እንደገና ቀስ እያሉ መንሾካሾካቸውን ይቀጥላሉ ።

በፋብሪካው ውስጥ እና በየመሸታ ቤቱ ከዚህ ቀደም ታይተው የማይታወቁ ሰዎች መታየት ጀመሩ ። አንዳንድ ሁኔታዎችን መቃኘት እና ማነፍነፍ የጀመሩ ሲሆን ጥያቄዎችንም ያቀርቡ ነበር ። ይኸ ሁኔታቸው ፣ እንደዚሁም ይበልጥ ጠንቃቃ መሆናቸውና በየሰው አያገባቸው ጉዳይ እየገቡ ጥያቄ ማቅረብን ማዘውተራቸው በአካባቢው ስለነርሱ ጥርጣሬ እንዲፈጠር አደረገ ።

በሠፈሩ የደረሰው ይኸ ሁሉ ከፍተኛ ስሜት በልጅዋ ተግባር ምክንያት መሆኑን እናት አሳምራ ታውቃለች ። ብዙ ሰዎች ወደርሱ የተሳቡ መሆናቸውን ተመልክታለች ። ይኸ በመሆኑ ለልቧ የተሰማት ኩራትም ስለርሱ ደህንነት ከምታስበው ሃሣብ ጋር ተደባልቆባታል ።

አንድ ምሽት ላይ ማሪያ ኮርሱኖቫ በመስኮት በ

ኩል አንኳኳች ። እናትም መስኮቱን እንደከፈተች የሚከተለውን ጎላ ባለ ሹክሹክታ ኮርሱኖቫ ነገረቻት ፡—

«ፔላጌያ ፣ ይጠንቀቁ! ነገሩ ሁሉ አልቆለታል! ዛሬ ማታ መጥተው ቤትዎን ይፈትሻሉ ። የእነ ማዚን እና የእነ ቬሶቭሺኮቭ ቤትም ዛሬ ማታ ሊፈተሽ ነው» አለቻት ።

ከዚያም የማሪያ ወፋፍራም ከናፍሮች ግጥም ብለው ተዘጉና ደፍጠጥ ባለ አፍንጫዋ ቁና-ያህል ከተነፈሰች በኋላ ከመንገዱ በኩል ሰው ማየት-አለማየቱን ለማረጋገጥ ዐይኖቿን ምልስ-ቅልስ በማድረግ አንዴ ግራውን አንዴም ቀኙን ከቃኘች በኋላ የሚከተለውን ለእናት እንደገና ተናረገች ፡ —

«አደራዎትን ፣ እንግዲህ ጉዳዩ በኔና በርስዎ መሀል ብቻ እንዲቀር! እኔ ምንም የማውቀው ነገር የለም ። አንዳችም የነገርኩዎት ነገር የለም ። የቀረው ቀርቶ እኔና እርስዎ ዛሬ አልተገናኘንም ነበር ማለት ነው ። አይደለም እንዴ? አዎ ፣ አደራዎትን እሺ?» አለች ።

ይኸንን ለእናት ነግራ ሄደች ።

እናት መስኮቱን ዘጋችና ቀስ ብላ ወንበሩ ላይ ኩርምት በማለት ተቀመጠች ። ልጅዋን አደጋ ላይ ሊጥለው የተቃረበው ሁኔታ ወዲያውኑ በሃሣብ አስፈንጥሮ ብድግ አደረጋትና ቆመች ። በፍጥነት ልብሷን ለበሰች ። ሻሿን አሠር አድርጋ ወደ ፌዎዶር ማዚን ዘንድ እየተፋጠነች ሄደች ። ፌዎዶር አሞት ስለነበር ወደፋብሪካው አልሄደም ነበር ። እናት ወደቤቱ ስትገባ ፌዎዶር አውራ-ጣቱ ከሌባ-ጣቱ ጋር አላግባቡ ተጣብቆ የሚገኝበትን የቀኝ እጁን እያሻሸ ከመስኮቱ ጥግ ቁጭ ብሎ መጽሐፍ ያነብባል ። ወሬውን እንደነገረችው በድንጋጤ ነጭ-አመዱ ወጣና ከተቀመጠበት ፍንጥር ብሎ ተነሳ ።

«እኪድዬ!» አለ በማጉረምረም ።



«ምን እናድርግ?» አለችው እናት በሚርበደበዱ እጆቿ ከግንባሯ ላይ ላቦቿን እየጠረገች ።

ከዚያም ፌዎዶር ፀጉሩን ወደኋላ እያሻሸ ፡ —

«ይቆዩ እስኪ ፣ አይደናገጡ» አላት ።

«ምን እደናገጣለሁኝ ፣ የተደናገጥከውማ አንተ ነህ!» አለችው ጎላ ባለ ድምፅ ። እርሱም እናት ባቀረበችው መልስ መደናገጡ ለራሱ ስለተሰማው ፊቱ ቀልቶ እና ፈገግም እያለ ፡ —

«ማን ፣ እኔ? ኧረ ይተው ። ሀ-ሀ ... ይልቁንስ ፓቬል እንዲያውቀው ማድረግ አለብን ። ወደርሱ ዘንድ ሰው እልካለሁኝ ። እርስዎ ግን ወደቤት ተመልሰው ይሂዱ ። አያስቡ ። አይደበድቡንም ። ይደበድቡናል እንዴ?» አላት ።

እቤት እንደደረሰችም መጻሕፍቶቹን ሁሉ ሰብስባ በደረቷ ላይ አስደግፋ በመሸከም አንዴ ወደ እሳት ማንደጃው በመሄድ ፣ ከዚያም ጎንበስ ብላ ከእሳት ማንደጃው ውስጥ ለመደበቅ ይቻል እንደሆነ በመመልከት ፤ አንዴ ደግሞ ውሃ ማከማቻው በርሚል እንኳን ሳይቀር በመመልከት ክፍሉ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ ትንቆራጠጥ ጀመር ። ፓቬል ከፋብሪካው ወዲያውኑ ይመጣል ብላ ገምታ ነበር ። አልመጣም ። ከዚያም መንቆራጠጡ ድክም ስላላት ማዕድ ማዘጋጃው ክፍል በመሄድ ፓቬል እና ኾኾል እስኪመጡ መንቀሳቀስን እንኳን ፈርታ መጻሕፍቶቹን ከሥሯ ወለሉ ላይ አስቀመጠችና አግዳሚው ወንበር ላይ ተቀመጠች ። እነርሱ እንደመጡም ፡ —

«ሰማችሁ እንዴ?» አለቻቸው ከተቀመጠችበት ሳትነሳ ። ከዚያም ፓቬል ፈገግ እያለ ፡ —

«አዎን ሰማን ። ምነው ፈራሽ እንዴ?» አላት ።

«በጣም ነው የፈራሁት!...» አለችው ። ኾኾልም ፡ —

«መፍራት የለብዎትም! መፍራት ምንም አይጠቅምም» አላት ። ፓቬልም ቀጠል አደረገና ፡ —

«ሳሞቫሩን እንኳን ለሻዩ አላያያዝሺውም» አላት ። እናትም ሻይ ባለማፍላቷ ቅሬታ ለራሷ ተሰምቷት ከተቀመጠችበት ቦታ ብድግ አለችና ፡ —

«ምን ላድርግ ብለህ ነው ፣ እነዚህን ሰብስቤ ተቀምጨ እኮ ነው» በማለት መጻሕፍቶቹን እያሳየች መለሰችለት ።

ልጅዋና ኾኾል ለካ ቁጭ ብላ የነበረው መጽሐፍቶቹን ከምራ በመደበቅ መሆኑን በማየታቸው በሳቅ ተንከተከቱ ። ይኸ ሁኔታም ድንጋጤዋን መለስ አደረገላት ። ፓቬል ከመጻሕፍቶቹ መካከል ጥቂቱን መረጠና ውጪ ለመደበቅ ወጣ አለ ። ኾኾልም ሻይ ለማፍላት ሳሞቫሩን እያቀጣጠለ የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«እምዬ ፣ ምንም የሚያስፈራዎት ነገር የለም ። የሚያሳዝነው ፣ ሰይፋቸውን በወገባቸው ላይ የታጠቁ ፣ የሚጋልቡትን ፈረስ መኮርኮሪያ እንዲሆን መጫሚያቸው ላይ የብረት ጉጥ የለጠፉ እና በዕድሜ ትልልቅ የሆኑ ጉብሎች ይኸንን በመሰለ የእንከፍ ድርጊት ጊዜያቸውን የሚያባክኑ መሆኑ ነው ። እዚህ ይመጡና አንዳችም ነገር ሳይቀራቸው ያለ-የሌለውን በማመሳቀል ይበረብራሉ — አልጋው ሥር ገብተው ይፈትሻሉ ። እሳት ማንደጃው ሥር ይፈትሻሉ ። ምድር ቤቱ ውስጥ ወርደው ይፈትሻሉ ። ጣራው ሥር ያለውን ቦታ ሳይቀር ይፈትሻሉ ። ከወዲያ-ወዲህ እየተሯሯጡ ሲበረብሩ ፊታቸውን የሸረሪት ድር ያደራበታል ፣ ከዚያም በመከፋት ተውጠው ይደነፋሉ ። ይነጫነጫሉ ። ሃፍረትም ስለሚይዛቸው ፣ አስፈሪዎች እና ቁጡዎች ለመምሰል ይጥራሉ ። ሥራቸው የአራዊት ሥራ መሆኑን ራሳቸውም ያውቁታል! አንድ ጊዜ በድርጊታቸው በጣም ተከፍተው ስለነበረ ያለኝን ሁሉ አግበስብሰው ይዘውት ሄዱ ። ሌላ ጊዜ ደግሞ እኔንም ጭምር ይዘውኝ



ሄዱ ። ከዚያም እሥር ቤት ወርውረውኝ አራት ወራት ያህል እዚያው አቆዩኝ ። እሥር ቤት ምንም የሚደረግ ነገር የለም ። ቁጭ ብሎ መጠባበቅ ብቻ ነው ። ከዚያም ይጠሩና ወታደሮች አጅበው በመንገዱ በኩል ወደአለቃቸው ዘንድ ይወስዱዎታል ። ከፍተኛ ሹማምንቶቻቸውም ጥያቄዎች ያቀርቡልዎታል ። እነዚህ ሹማምንቶቻቸውም ብልሆች አይደሉም ። ብዙ ይለፈልፋሉ ። ከዚያም ወታደሮቹ እንደገና ወደእሥር ቤት እንዲወስዱዎት ያደርጋሉ ። በዚህ ዐይነት ሁኔታ ከወዲያ-ወዲህ ያመላልሱዎታል ። ምናለ ፣ ለሚከፈላቸው ደሞዝ ትንሽም ቢሆን መሥራት አለባቸው አይደል! ከዚያም የኋላ-ኋላ ይለቁዎታል ። ይኸው ነው እንግዲህ ጉዳዩ!» በማለት ተናገረ ።

«አንድርዬ ፣ የአነጋገርህ ሁኔታ ሁል ጊዜም እንዴት ግሩም ነው!» በማለት እናት ተናገረች ።

ሳሞቫሩን ለማቀጣጠል በርከክ ብሎ ከነበረበት ቦታ የቀላ ፊቱን ቀና አደረገና ሪዙን በማሻሸት የሚከተለውን ጠየቀ ፡ —

«እንዴት ዓይነት የአነጋገር ሁኔታ ነው ያለኝ?» አለ ።

«ማንም ምንም ጉዳት እንዳላደረሰብህ አድርገህ ነው የምትናገር» አለችው ።

ከዚያም በርከክ ካለበት ቦታ ብድግ ብሎ በመቆም እና ጭንቅላቱንም በመነቅነቅ ፡ —

«ለመሆኑ በዚች ዓለም ላይ ያልተበደለች ነፍስ ትገኛለችን? እነርሱ እኔን ከፉኛ የበደሉኝ በደል እጅግ የከፋ በመሆኑ ምክንያት ዳግመኛ አላስታውሰውም ። ሰዎች ይኸንን ዓይነት እስከሆኑ ድረስ ምን ማድረግ ይችላሉ? የደረሰብዎትን በደል የሚያስታውሱት ከሆነ በሥራዎ መሀል ትውስቱ ጣልቃ እየገባ ያውክዎታል ። ከዚህም በስተቀር ልብዎን በሀዘን ማስቱ

ከዝ ጊዜ ማባከን ነው ። ኑሮ እንደሆን ልክ እንደዚህ
ነው! እኔም በሰዎች ድርጊት እበሳጭ ነበር ። በኋላ
ሳስተውለው ግን ፋይዳ የለውም ። ሁሉም ሰው ጎረ
ቤቱ ዘርጥጦ ጥሎ ሊደበድበኝ ነው ብሎ ስለሚፈራ
ሳልቀደም — ልቅደም በሚል መንፈስ ቀድሞ ሌላውን
ይወግረዋል ። የኔ እምዬ ፣ ይኸውልዎት እንግዲህ ሕይወ
ት ማለት ይቺው ነች!» አላት ።

እነዚህ ቃላት ከአንደበቱ የሚወጡት ያለመጨነ
ቅ ወዲያው-ወዲያው ስለነበረ የሚበረበሩ በመሆናቸ
ው አድሮባት የነበረውን ሥጋት አጠፋላት ። ትክል
ብለው የሚያስተውሉት ዐይኖቹ የመሳቅ ስሜት ያላ
ቸው ይመስላሉ ። ቅልጥፍጥፍ ያለ ባይሆንም እንኳን
ንቁ መሆኑን ተገነዘበች ።

እናት በረዥሙ ተነፈሰች ። ከዚያም ልብ በሚነካ
ሁኔታ ፤ —

«አንድርዬ ፣ እግዚአብሔር ደስታን ያጎናጽፍህ!»
አለችው ።

ኾኾልም ወደሳሞቫሩ መለስ ብሎ በመነካካት ፤ —

«ትንሽ ደስታን ብጎናጸፍ ቅር አይለኝም ። ይሁን
እንጂ እባካችሁ ደስታ አጎናጽፉኝ እያልኩ አልለም
ንም!» አለ ።

ፓቬል ከውጭ መጣ ። ከዚያም ፤ —

«ሲበረብሩ ቢውሉ አያገኟቸውም!» በማለት በሙ
ሉ ልብ እየተናገረ እጆቹን ይታጠብ ጀመር ። ከዚያም
እጆቹን እያደረቀ ወደ እናት ዞር አለና ፤ —

«መደናገጥሽን ከሁኔታሽ ላይ ከተመለከቱ ፣ እንዲህ
የሚያርበተብታት እዚህ ቤት ውስጥ አንድ የተደበ
ቀ ነገር ቢኖር ነው ብለው ይገምታሉ ። እኛ አንዳ
ችም ስህተት እንደማናደርግ ታውቂያለሽ ። ፍትህ
ከእኛ ጋር ነች ። መላ ሕይወታችንን የምንሠ
ራውም ለዚችው ለፍትሕ ስንል ነው ። ጥፋተኞች



የምንባልበት ምክንያት ይኸ ብቻ ነው ። ስለዚህ ፣ ምን
የሚያስፈራን ነገር አለ?» አላት ።

«ፓሻ ፣ ያለአንዳች ፍርሃት በብርታት እቆያለሁኝ»
በማለት ቃል ገባችለት ። በሚቀጥለው አነጋገርዋ ደግ
ሞ በመረበሽ አነጋገር ፤ —

«አንዴ ብቻ ወደዚያ የሚፈትሹትን ቶሎ ፈታት
ሸው በሄዱልኝ እንጂ!» አለች ።

በዚያን ምሽት ይመጣሉ የተባሉት አልመጡም ።
ጧት ሲነጋም ፣ እንዳትረበሽ በማለት ልጆቹ የቀለዱባ
ትን ቀልድ እርሷ የመጀመርያ ሁና በማሰማት ፤ —

«እነዚያ አስፈራሪዎች ገና ሳይመጡ እኔ ግን
ፈርቼ ነበር!» አለች ።

## 10

ያ አስጊ የነበረው ምሽት ካለፈ አንድ ወሩን
ሊይዝ በተቃረበበት ጊዜ ፖሊሶቹ መጡ ። ፓቬልን
እና አንድሬይን ለመጠየቅ ኒኮላይ ቬሶቭሺኮቭ መጥቶ
ስለነበረ ፣ ሦስቱም ስለጋዜጣቸው ጉዳይ ይወያዩ ነበር ።
በጣም መሽቶ ነበር — ዕኩለ-ሌሊቱ ተቃርቧል ።
እናት ወደ መኝታዋ ሂዳ ጋደም በማለት እንቅልፍ
ሊወስዳት ሸለብ እያደረገ ይሞካክራታል ። ያም ሆኖ
ግን ረጋ ያለ እና በሃሣብ የተመሰጠ ድምፃቸውን
ትሰማለች ። ከዚያም አንድሬይ ቀስ ብሎ ወደ ማዕድ
ክፍል ድምፅ ሳያሰማ ሄደና የማዕድ ክፍሉን በር ከ
በስተኋላው ዘጋው ። የባልዲ ድምፅ ሲንኳኳ ይሰማ ነ
በር ። በሩ ተበርግዶ ተከፈተ ። አንድሬይም ከማዕዱ ክ
ፍል ብቅ አለና ጎላ ባለ ድምፅ ፤ —

«አስበርጋጊዎቹ መጥተዋል!» አለ ።

እናት ከአልጋዋ ላይ እመር ብላ በመነሳት በሚ

ንቀጠቀጡት እጆቿ ልብሷን አፈፍ አድርጋ መልበስ
ስትጀምር ፓቬል መጣና ከመኝታ ክፍሏ በር ላይ
ቆሞ ረጋ ባለ ሁኔታ የሚከተለውን ተናገራት ፦ —
«አንቺ ወደአልጋሽ ተመለሺና ያመመሽ ሁነሽ
ተኚ!» አላት ።
ከበስተውጪ በኩል ኮሽኮሽታ ይሰማል ። ፓቬልም
ወደ በሩ ሄደና ፦ —
«ማነህ አንተ?» በማለት በሩን ከፈተው ።
ወዲያውኑም አንድ አመድማ መልክ ያለው ረዥ
ም ሰው ሌሎች ሁለት ሰዎች አስከትሎ ብቅ ሲል ፥
ሁለት ዣንዳርሞች ደግሞ ፓቬልን ወደቤት ውስጥ
ገፉትና እርሱን በመጠበቅ ሁኔታ ከግራና ቀኙ ቆሙ ።
ከዚያም ጎላ ባለ ድምፅና በፌዝ አባባል ፦ —
«ስትጠባበቃቸው የነበሩት ሰዎችህ አይደለንም ።
እውን?» በማለት አንዱ ተናገረ ።
ይኸንን የተናገረው ሪዝ ያቀመቀመው ረዥሙና
ቀጭኑ መኰንን ነበር ። ፌዲያኪን የተሰኘው የሠፈሩ
የፖሊስ መኰንን ወደ እናት የመኝታ ክፍል ሄደ ።
ከዚያም በአንድ እጁ መለዮውን እየነካካና በሌላ
እጁ ደግሞ ወደ ፔላጌያ እየተመለከተ ፦ —
«ክቡር ሆይ ፥ እናቲቱ ይህቺ ናት» ካለ በኋላ እጁ
ን ወደ ፓቬል በማመልከት ደግሞ ፦—«ልጅዋ ደግሞ
ይሄ ነው» አለ ። መኰንኑም ዐይኖቹን ጠበብ በማድረ
ግ ሁኔታ ፓቬልን አትኩሮ እየተመለከተ ፦ —
«ፓቬል ቭላሶቭ አንተ ነህ?» በማለት ጠየቀው ።
ፓቬልም በንግግር ሳይሆን ራሱን በመነቅነቅ ፥ አዎ
ነኝ የሚል ምልክት አሳየ ። ከዚያም መኰንኑ ሪዙን
እያሻሸ ፦ — «ቤታችሁን ልፈትሽ ነኝ ። ማነው እዚያ
ያለው? ሴትዮ ይነሱ!» በማለት ወደክፍሏ እየተመለከተ
ገባ ። ከዚያም ፦ —
«ስማችሁ ማን ይባላል?» በማለት ጠየቀ ።



ሁለት እማኞችም መጡ ። አንደኛው ቀድሞ ብረት
ቀጥቃጭ የነበረ ትቬርያኮቭ የተሰኘ ሽማግሌ ሲሆን ፥
ሌላው ደግሞ ትቬርያኮቭ ከሚኖርበት ቤት አንድ
ክፍል በደባልነት ተከራይቶ የሚኖር ግዙፍ የሆነ
እና የጠቆረ መልክ ያለው ሪቢን የተሰኘ ሰው ነው ።
«እንደምን አመሹ ፥ ኒሎቭና!» በማለት ባልተገራ ወ
ፍራም ድምፅ ተናገረ ።
እናት ልብሷን እየለበሰች ከራሷ ጋር የሚከተለው
ን በማነብነብ ብርታት እንዲኖራት ጣረች ፦ —
«ኤጭ ፥ እንዲህ ያለ ሰምቼም አላውቅ! እንዲህ በዕ
ኩለ-ሌሊት ሰው ቤት ይኬዳል እንዴ! ሰው አልጋው
ላይ ከተኛ በኋላ ምን ዘው ብለው ይገባሉ!» አለች ።
ክፍሉ በሰዎች ተሞልቶአል ። ቤቱ የጫማ ቀለ
ም — የጫማ ቀለም መሽተቱ አለምክንያት አልነበረ
ም ። ሁለት ዣንዳርሞች እና የሠፈሩ የፖሊስ
አዛዥ አንድነት ሁነው በአጓጉል ሁኔታ መጻሕፍቶ
ችን ከመጽሀፍ መደርደሪያው ላይ እያነሱ መኰንኑ
ፊት ጠረጴዛ ላይ ከመሯቸው ። ሌሎቹ ሁለቱ ደግሞ
በቡጢ ግድግዳዎቹን መታ-መታ በማድረግና ወንበሮ
ቹ ሥርም በመመልከት ይበረብራሉ ። ከመካከላቸው
አንደኛው የእሳት ማንደጃው ምድጃ ላይ ሳይቀር
ወጥቶ ይበረብራል ። ኾኾልና ቬሶቭሺኮቭ ክፍሉ ው
ስጥ ካንዱ ጥግ በኩል ተጠጋግተው ቆመዋል ። ፈንጣ
ጣ የጠቀጠቀው የኒኮላይ ፊት ጉብርብር ብሎ ቀልቶ
አል ። ትንንሽ የሆኑ አመድማ ዐይኖቹንም ከመኰንኑ
ላይ ሳይነቅል በመጣል አተኩሮ ይመለከታል ። ኾኾል
ሪዙን እያሻሸ ቆሞአል ። እናት ወደ ክፍሉ ውስጥ
ስትገባ ለአፍታ ያህል ሳቅ ካለ በኋላ በማበረታታት
ዓይነት መልክ ራሱን ነቅነቅ አደረገላት ።
ፍርሀቷን ለማስወገድ በማለት አቋቋሟ እንደቀድሞ
ው አቋቋሟ የጎድን ዘንበል ያለ ሳይሆን ደረቷን

ወደፊት ነፍታ ቀጥ ያለ አቋቋም እንዲኖራት በማድረግ ሲሆን ፥ ይኸውም አኳኋኗ ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ ጀነን ያለች እንድትሆን አድርጓታል ። ወለሉን ስትረግጥ እግሮቿ ኳ-ኳ እያሉ የሚሰሙ ሲሆኑ ፥ የዐይኖቿ ሽፋሽፍቶችም ይርገበገባሉ ።

መኮንኑም አመድ በሚመስል እጁ ላይ ባሉት ቀጫጭን እጣቶቹ መጻሕፍቶቹን ምንጭቅ-ምንጭቅ እያደረገ በማንሳት ገልበጥ-ገልበጥ አድርጎ ከተመለከታቸው በኋላ ወዲያውኑ ወረወራቸው ። ግማሾቹ መጻሕፍት ወለሉ ላይ ወደቁ ። ማንም ምንም አልተናገረም ። ላብ ያላባቸው ዣንዳርሞች በትልቁ እየተነፈሱ እና በየቦታው እየበረበሩ ፡ —

«እዚያ ዘንድስ ፈትሸሃል?» እየተባባሉ ይነጋገራሉ ።

እናት ጀርባዋን ለግድግዳው ሰጥታ እና እጆቿንም እንደልጅዋ አጣጥፋ ከፓቬል ጎን ቆማ ዐይኖቿ መኮንኑን ይከተላሉ ። ጉልበቷን ብርክ-ብርክ ያላት ሲሆን ፥ ዐይኖቿም እንባ አቅርረዋል ።

ሁሉም ሰው በፀጥታ ጭጭ-ምጭጭ ብሎ ይገኝ ከነበረበት ሁኔታ ድንገት ጎርነን ባለ ድምፅ ኒኮላይ ፡ —

«መጻሕፍቶቹን ወለሉ ላይ መወርወር ምን ያስፈልጋል?» በማለት ተናገረ ።

እናት ደነገጠች ። አንድ ሌላ ሰው የገፋው ይመስል ትቬርያኮቭ ጭንቅላቱን ድንገት ዞር አደረገ ። ሪቢን በማጉረምረም ኒኮላይን አተኩሮ ይመለከተው ነበር ።

መኮንኑ ዐይኖቹን ዘጋ በማድረግ ሁኔታ እንደ በድን የተገተረውንና ፈንጣጣ የጠቀጠቀውን የኒኮላይን ፊት በዐይኖቹ ገረፍ በማድረግ ተመለከተው ፤ ከዚያም ፈጠን-ፈጠን እያለ የመጻሕፍቶቹን ገጾች ያገላብጥ ጀመር ። አንዳንድ ጊዜ ፥ ሊቋቋመው ባልቻለው የሕመም ሥቃይ ተወጥሮ ግቢ-ነፍስ ውጪ-ነፍስ የሆነበት ይመስል ለጮኸት እንደተቃረበ በሽተኛ አመድማ ዐይኖቹን ብልጥጥ አድርጎ ይበረግዳቸዋል ።

«ስማ ፥ ወታደር የተወረወሩትን መጻሕፍት ከወለሉ ላይ አንሳቸው!» በማለት ቬሶቭሺኮቭ እንደገና ተናገረ ።

ከዚያም ዣንዳርሞቹ በሙሉ ዞር ብለው ቬሶቭሺኮቭን በግልምጫ ከተመለከቱት በኋላ መኮንኑን ተመለከቱ ። መኮንኑም ጭንቅላቱን ቀና አድርጎ የኒኮላይን ግዙፍ ሰውነት በግልምጫ አመለካከት ከተመለከተ በኋላ በአፍንጫው አየር ደህና አድርጎ በመሳብ ተነፈሰና ፡ —

«ኡ-ሆ-ሆ-ሆ! አንሷቸው?» በማለት ወለሉ ላይ የወደቁት መጻሕፍት እንዲነሱ ፖሊሱን አዘዘ ።

ከዚያም ከዣንዳርሞቹ መካከል አንዱ ተበታትነው የወደቁትን መጻሕፍት እየሰበሰበ ማንሳት ጀመረ ።

«ይሄ ኒኮላይ ዝም ቢል ይሻለዋል!» በማለት እናት ቀስ ብላ ለፓቬል ነገረችው ።

ፓቬልም ትከሻውን ነቅነቅ አደረገ ። ኾኾል ጭንቅላቱን ዘቅዘቅ አድርጎ ነበር ።

«መጽሐፍ ቅዱስ የሚያነበው ደግሞ ማነው?» አለ መኮንኑ ።

«እኔ ነኝ!» አለ ፓቬል ።

«እነዚህ ሁሉ መጻሕፍት የማን ናቸው?»

«የኔ ናቸው!» አለ ፓቬል ።

«እ-ሀ! መልካም ነው!» አለ መኮንኑ ወንበሩ ላይ ለጠጥ ብሎ በመቀመጥ ። ከዚያም የቀጫጭን እጆቹን ጣቶች እያንቋቋ እና እግሮቹንም ጠረጴዛው ሥር ዘርግቶ ፥ ሪዙንም እያሻሸ ኒኮላይን ፡ —

«አንድሬይ ናኾድካ ማለት አንተ ነህ?» ብሎ ጠየቀው ። ኒኮላይም ፡ —

«አዎን ፤ እኔ ነኝ» በማለት ወደ መኮንኑ ተጠጋ ።

በዚህን ጊዜ ኾኾል ኒኮላይን ከትከሻው ላይ ያዝ
አድርጎ ወደ ኋላ በማስቀረት ፡ —

«የለም ፣ እርሱ አይደለም ። አንድሬይ ማለት እኔ
ነኝ!...» አለ ።

መኮንኑ እጁን ከፍ አድርጎ እጣቶቹን ቬሶቨሺኮ
ቭ ላይ በዛቻ በማወዛወዝ ፡ —

«አንተ ሰው ፣ ብትጠነቀቅ ይሻልሃል!» አለው ።

ከዚያም መኮንኑ ወረቀቶቹን ያገላብጥ ጀመር ። የ
ጨረቃ ብርሃን ያረበበት ምሽት ከመንገዱ በኩል
ፍዝዝ-ድብዝዝ ብሎ በመስኮቱ ውስጥ ይታያል ። በቤ
ቱ አጠገብ ቀስ ብሎ ያልፍ የነበረውን ሰው ኮቴ
በረዶው ሿ-ሿ እያደረገ ያሰማል ።

«አንተ ማነህ ፣ ናኾድካ! ከአሁን በፊት በፖለቲካ
ጉዳይ ወንጀል ፈጽመህ ነበር ። አይደለም?» በማለት
መኮንኑ ጠየቀው ።

«አዎን ። አንድ ጊዜ ሮስቶቭ ከተማ ፣ ሌላ ጊዜ ደ
ግሞ ሳራቶቭ ከተማ ውስጥ ፈጽሜአለሁኝ ። እዚያ
ያሉት ዡንዳርሞች ግን ይበልጥ የተሻሉ ትሁቶች
ናቸው» በማለት መለሰ ።

መኮንኑ የቀኝ ዐይኑን ዘጋ አድርጎ ማሻሸት ጀመ
ረ ። ከዚያም ትንንሽ ጥርሶቹን ብልጭ እያደረገ ፡ —

«ስማ ፣ ናኾድካ ፣ ወንጀለኛ የሆኑ ጽሁፎችን በፋብሪ
ካው ውስጥ የሚበትኑት ልክስክስ ሰዎች እነማን
እንደሆኑ አታውቅምን?» በማለት ጠየቀው ።

ኾኾል ፈገግ በማለትና ከተረከዙም ከፍ በማለት
መልስ ሊሰጥ ሲል ኒኮላይ እንደገና ፡ —

«ልክስክሶችን ማየት ስንጀምር ይኸው ይኼ የመጀ
መርያ ጊዜያችን መሆኑ ነው» በማለት ተናገረ ።

በክፍሉ ውስጥ ፀጥታ ሰፈነ ። ለጥቂት ሰኮንዶች
ሁሉም ጭጭ-ምጭጭ አሉ ።

እናት ጠባሳዋ ከነበረበት ቦታ ወደላይ ከፍ አለ ።



የቀኝ ቅንድቧም ብርግድ ብሎ ተበለጠጠ ። የሪቢን ጥ
ቁር ጢም በሚያስደንቅ ሁኔታ ይንቀጠቀጣል ። ጢሙን
በእጣቶቹ እያሻሸ ዐይኖቹን ወደመሬት ተክሎአል ።

«ይኼንን እንስሳ ከዚህ አስወጡልኝ!» በማለት መ
ኮንኑ በጩኸት ድምፅ ተናገረ ።

ሁለት ዡንዳርሞች ኒኮላይን በእጃቸው ጨምድደ
ው በመያዝ እያንገላቱ ወደ ማዕድ ክፍል ሲወስዱት
እግሩን ከወለሉ ጋር ቀርቅቦ በመትከል ከመራመድ
ካቆማቸው በኋላ ፡ —

«አንዴ ልቀቁኝ! ካፖርቴን ልልበስ!» በማለት ተና
ገረ ።

የፖሊሱ አዛዥ ከቤቱ ግቢ ከሚገኘው የአትክል
ት ሥፍራ ተመልሶ ከመጣ በኋላ ፡ —

«ውጪ ምንም አላገኘንም ። ሁሉንም ቦታ ፈተሽ
ን!» በማለት ተናገረ ። መኮንኑም ትከሻውን ነቅነቅ በ
ማድረግ ፡ —

«እንዴ ፣ ነው እንጂ! እንዴት አድርጎ ይገኛል! በጉዳ
ዩ የሠለጠኑበት ሰዎች ዘንድ እኮ ነው ያለነው!»
በማለት ተናገረ ።

እናት የዚህን ሰው ስልምልም እና ስብርብር ያለ
ድምፅ እያዳመጠች እና ወደቢጫነት የተለወጠ አስፈ
ሪ ፊቱንም እየተመለከተች በተራ ሰዎች ላይ ቂም
በቀሉን ለመወጣት አሰፍስፎ የሚጠባበቅ ምህረት-የለ
ሽ ጨካኝ ፍጡር እንደሆነ ተገነዘበች ። እንደነዚህ
ዓይነት ሰዎችን አልፎ-አልፎ ብቻ የምትገናኝ ስትሆ
ን እስከመኖራቸውም ጭምር እርግፍ አድርጋ ዘንግታ
ቸው ነበር ።

«እ-ህ! በሚበተኑ ወረቀቶች የሚሸበሩት እነዚህ
ናቸው ማለት ነዋ!» በማለት እናት ከራስዋ ጋር ተወ
ያየች ።

«አንተ ሚስተር አንድሬይ አኒሲሞቭ ናኾድካ የተሰኘህና ከሕጋዊ ጋብቻ ውጪ የተወለድክ ዲቃላ ፥ ወደ እሥር ቤት እንድትሄድ በቁጥጥር ሥር ውለሃል!» በማለት መኮንኑ ኾኾልን ተናገረው ። ኾኾልም ፦

«ምን ስላደረግሁኝ?» በማለት በረጋ ሁኔታ ጠየቀ ።

«ግዴለም ፥ ያደረከውን በኋላ እነግርሃለሁ!» በማለት መኮንኑ ከመለሰለት በኋላ ፦ «አንቺ ትምህርት የተማርሽ ነሽ?» በማለት ፔላጌያን ጠየቃት ።

«የለም ፥ አልተማሩም!» በማለት ፓቬል መለሰ ። ከዚያም ፦

«አንተን የጠየቀህ የለም!» በማለት መኮንኑ ቆጣ ብሎ ለፓቬል መለሰ ። ከዚያም ፦

«ሴትዮ ፥ ተናገሪ እንጂ!» በማለት መኮንኑ እናትን ጠየቀ ።

እናት ይኸንን ሰው ክፉኛ ጠልታው ነበር ። ቀዝቃዛ ውሀ ውስጥ የተነከረች ይመስል ድንገት መንቀጥቀጥ ጀመረች ። ቀና ብላ በመቆም ጠባሳዋ በጉልህ እየታየና ቅንድቦቿም እየተርገበገቡ እጣቶቿን ወደ መኮንኑ ጠቁማ በማመልከት ፦

«ይኸንን ያህል መጮህ አያስፈልግዎትም! እርስዎ ገና ወጣት ነዎት ። መከራ ምን እንደሆነ አልቀመሱም...» አለችው ።

ፓቬልም ንግግሯን እንድታቆም በመሞከር ፦

«ተይው ዝም በይ እማማ!» በማለት ተናገረ ።

«ተው እስኪ ቆይ ፥ ፓቬል!» በማለት እናት መኮንኑ ወደሚገኝበት ጠረጴዛ በመገስገስ ተጠግታ ፦ «እነዚህን ሰዎች የሚይዟቸው ለምንድነው?» በማለት ጠየቀችው ።

«ኢሄ አንቺን የሚመለከት ጉዳይ አይደለም! ዝም በይ!» በማለት በቁጣ ድምፅ እየጮኸ መኮንኑ ከተቀመጠበት ተነሳ ። ከዚያም ፦



«በቁጥጥር ሥር የዋለውን ቬሶቭሺኮቭንም ወደዚህ አምጡልኝ!» በማለት አዘዘ ።

ይዞት የነበረውን ወረቀት አፍንጫው ሥር አስጠግቶ ማንበብ ጀመረ ።

ኒኮላይ ከነበረበት እንዲመጣ ተደረገ ። መኮንኑም ጀምሮ የነበረውን ንባብ በማቋረጥ ፦

«አውልቅ ይሄንን ቆብህን!» በማለት ጮኸ ።

ሪቢን ወደ ፔላጌያ ጠጋ አለ ። ከዚያም አይዞሽ እንዳትደነግጪ በሚል አኳኋን በትከሻው ነካ አደረጋትና ፦

«እናት ፥ አይደናገጡ!» በማለት ነገራት ። ከዚያም በቁጥጥር ሥር የዋሉበት ማዘዣ መነበቡ ሲቀጥል ኒኮላይ በማቋረጥ ፦

«ሁለቱም እጆቼ ተጠፍረው ተይዘዋል ። ለመሆኑ ቆቤን የማወልቀው እንዴት አድርጌ ነው?» በማለት ጠየቀ ።

«ና ፈርም እዚህ ላይ!» በማለት ወረቀቱን ጠረጴዛው ላይ እየወረወረ በቁጣ ድምፅ መኮንኑ ተናገረ ።

ወረቀቱ ላይ ፊርማቸውን ሲያኖሩ እናት ትመለከት በነበረበት ጊዜ ብስጭቷ በረታ ፥ ልቧ በሀዘን በትር ተመታ ፥ በጉዳት እና በረዳት-አልባነትም ዐይኖቿ በእንባ ተመሉ ። በትዳር ላይ በነበረችባቸው ሃያ ዓመታት ውስጥ እነዚህን መሳይ እንባዎች አንብታለች ። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ግን አቃጣይ የነበሩትን የእንባዎቿን ግንፋሎት እስከመዘንጋቱም ተዳርሳ ነበር ። መኮንኑ እርሷን ተመለከተና በሁኔታዋ ደስ ባልተሰኘ አመለካከት ፊቱን ኮስተር አድርጎ ፦

«ሴትዮ ፥ ይኸንን እንባ ቆጠብ አድርጊ! አለበለዚያ ለወደፊቱ ሀዘን ምንም እንባ አይተርፍሽም!» አላት ።

እንደገና ሌላ የቁጣ ብስጭት አካሏን ወረራት ።

«እናት ምንግዜም ቢሆን ፣ ለማንኛውም ነገር ፣ ለማንኛውም ነገር በቂ እንባ አላት! እርስዎም እናት ካለዎት ፣ እናትዎ ይኸንን በሚገባ ያውቁታል!» አለችው ።

ከዚያም መኮንኑ የሚያንጸባርቁ ቁልፎች ባሉት በአዲስ የወረቀት መያዣ ቦርሳ ውስጥ ወረቀቶቹን ከተታቸውና ፡ —

«ቅደሙ ወደፊት!» በማለት በቁጥጥር ሥር ያዋላቸውን አዘዛቸው ። ፓቬልም በጋለ ስሜት ለመሰናበት እየጨበጣቸው ፡ —

«አንድሬይ ፣ በል ደህና ሁን! ኒኮላይ ፣ በል ደህና ሁን!» በማለት ተሰናበታቸው ። ከዚያም መኮንኑ ትንሽ ሳቅ ካለ በኋላ ፡ —

«አይዞህ አታስብ ፣ በቅርቡ አንድላይ ትቀላቀሉ ይሆናል!» በማለት ፓቬልን ተናገረው ።

ቬሶቭሺኮቭ በረዥሙ ተነፈሰ ። ወፍራም በሆነው አንገቱ ላይ ያሉት ሥሮቹ በደም አገሽበዋል ። ዐይኖቹም በቁጣ ተመልተዋል ። ኾኾል ፈገግታ አሳየና ደህና ሁኑ በሚል ሁኔታ ራሱን ነቅንቅ ካደረገ በኋላ ለእናት አንድ ነገር በጆሮዋ ነገራት ። እናትም አማተበች ። ከዚያም ፡ —

«ትክክለኛው ማን እንደሆነ ፈጣሪ ያያል...» አለች ።

በመጨረሻም ግራጫ የመለዮ ልብስ የለበሱት እነዚህ ሰዎች ወደበረንዳው እየወጡ በመኮልኮል በመጫምያቸው ላይ የተለጠፉትን ብረቶች ሲራመዱ እያንኳኩ መንገዳቸውን ሄዱ ። ከቤት በመጨረሻ የወጣው ሪቢን ነበር ። ፓቬልን በቀይታ ከተመለከተው በኋላ የገዛ ራሱን ጢም በመነካካት ሳሉን እየሳለ እና በማሰብ መንፈስ ተውጦ ፡ —

«በል እንግዲህ ደህና ዋል!» አለው ።

ፓቬልም እጆቹን ወደ ኋላው አድርጎ በዝግታ



ክፍሉ ውስጥ በመራመድ ወደ ተበታተኑት መጻሕፍትና ልብሶች ጠጋ ብሎ እየተመለከተ ፡ —

«አየሽ? እንዲህ ነው የሚያመሳቅሉት!» በማለት እናትን ተናገራት ።

እናትም ምስቅልቅላቸው የወጡትን መጻሕፍት በመገረም እያስተዋለች ፡ —

«ኒኮላይ ምነው እንዲህ ተዳፈረ?» በማለት በመፀፀት መልክ ተናገረች ።

«ፈርቶ ስለነበረ ሳይሆን አይቀርም» በማለት ፓቬል መለሰላት ።

«ወይ ጉድ! ድንገት መጡና ዘው ብለው ገቡ ። እያንጠለጠሉ ዝም ብለው ይዘዋቸው ይሂዱ!» በማለት ራሷን እየነቀነቀች አጉረምርማ ተናገረች ።

ልጅዋ ያልተያዘ ስለነበር የልቧ ትርታ ቀነስ ብሎ ላታል ። ይሁን እንጂ ፣ የተመለከተችውን ድርጊት በመቃወም ሁኔታ እያሰላሰለች በሃሣብ ተውጣ ነበር ።

«ያ ፊተ-ቢጫ በላያችን ላይ አናፋ እኮ! ሊያስፈራራንም ከጀለው እኮ!..» እያለች ስትናገር ፓቬል ድንገት በረጋ መንፈስ አቋረጣትና ፡ —

«በቃሽ እንግዲህ ፣ የኔ እናት ። ይልቁንስ እነዚህን የተበታተኑትን እንሰበሳስባቸው» በማለት ተናገረ ።

አንቱ ሳይሆን አንቺ በሚል አጠራር የኔ እናት አላት ። ይኸንን አጠራሩን የሚጠቀምበት በጣም ቅርብ በሆነ የመቅረብ መንፈስ በሚያነጋግራት ጊዜ ብቻ ነበር ። ወደርሱ ጠጋ ብላ ፊት-ፊቱን እየተመለከተች ፡ —

«ጎዳህ እንዴ?» በማለት ቀስ ብላ ጠየቀችው ።

«አዎን ጎድተውኛል ። በጣም ከባድ ሁኔታ ነው ። ከሌሎቹ ጋር አንድነት በወሰዱኝ ኖሮ ይሻለኝ ነበር...» አላት ።

ዐይኖቹ እንባ አቅርረው የተመለከተች መሰላት ።

ከዚያም በረዥሙ በመተንፈስና እንዲጽናና ለማድረግ በመሞከር ፡ —

«ትንሽ ጊዜ ጠብቃቸው ፣ አንተንም ይወስዱሃል!» አለችው ።

«እንደሚወስዱኝ አውቃለሁኝ!» በማለት መለሰላት ።

ለጥቂት ጊዜ ዝም አለች ። ከዚያም ፡ —

«ፓቬል ፣ እንዴት እንዲህ ጠንካራ ሆንክ ልጄ! ትንሽም እንኳን አታጽናናኝም እንዴ! እኔ ሊናገሩት የማይገባ አንድ አጉል ቃል ስናገር አንተ ደግሞ በላዩ ላይ ከዚያ የባሰ ትጨምርበታለህ!» አለችው ።

እርሷን-እርሷን ተመለከተና ወደርሷው ጠጋ በማለት የሚከተለውን በዝግታ ተናገረ ፡—

«እማማ ፣ እንዴት እንደሚቻል እኔ እንጃ! ይሁን እንጂ ፣ እንዲህ የመሰለውን ሁኔታ መላመድ አለብሽ» አላት ።

በረዥሙ ተነፈሰችና ድምጿ ስልቱን እንዳይስት እየሞከረች የሚከተለውን ጥያቄ አቀረበችለት ፡ —

«ለመሆኑ የሚይዟቸውን ሰዎች ያሰቃዩ ይሆን? ገላቸውን ይተለትሉት ይሆን? አጥንታቸውን ይሠባብሩት ይሆን? ስለዚህ ጉዳይ ባሰብኩኝ ቁጥር ይዘገንነኛል!..» አለችው ።

«ልብሽን ይቦጫጭቁታል ። በቆሻሻ እጃቸው ልብሽን ሲያነድፉት ፣ ሕመሙ ከሁሉም ይበልጥ የከፋ ሁኖ ይሰማሻል!» አላት ።

## 11

ቡኪን ፣ ሳሞይሎቭ ፣ ሶሞቭ እና ሌሎች አምስት ሰዎችም መያዛቸው በማግሥቱ ሊታወቅ ቻለ ። ምሽቱ ላይ ፌዎዶር ማዚን እናት ቤት መጣ ። የእርሱም ቤ



ት ተፈትሾ ነበር ። ይኸም በመሆኑ እጅግ ተደስቶ የነበረ ሲሆን የጀግንነት ስሜትም ተሰምቶታል ።

«ፈርተህ ነበርን ፌዎዶር?» በማለት እናት ጠየቀችው ።

ደም መሰለ ። ሰውነቱን ሰገግ አድርጎ በማቆም አፍንጫው ይንቀጠቀጥ ጀመር ። ከዚያም ፡ —

«መኰንኑ ያላጋኛል ብዬ ፈርቼ ነበር ። ጥቁር ጢም ፊቱ ላይ ያጤመ ፣ እጣቶቹ በጠጉር የተወረሩ እና ዕውር ይመስልም ጥቁር መነጽር ያደረገ ወፍራም ሰው ነው ። እየጮኸ እግሮቹን ከወለሉ ጋር ያጋጭ ነበር ። 'ወደ እሥር ቤት ነው የምወረውርህ!' እያለ ይጮህ ነበር ። በሕይወቴ ማንም ሰው ደብድቦኝ አያውቅም ። እናት እና አባቴ እንኳን ደብድበውኝ አያውቁም ። አንድ ብቻ ልጃቸው እኔ ስለሆንኩኝ ይወዱኝ ነበር» በማለት ተናገረ ።

ለአፍታ ያህል ዐይኖቹን ዘጋና በሁለቱም እጆቹ ፀጉሩን ቶሎ-ቶሎ ወደኋላ እያሻሸ ከንፈሮቹን ግጥም አድርጎ ያዛቸው ። ከዚያም ደም በለበሱ ዐይኖቹ ፓቬልን እየተመለከተ ፡ —

«እኔን አንዱም ለመንካት ቢሞክር እንደጩቤ እላዩ ላይ ተወርውሬ ነው የምተክልበት ። በጥርሶቼ እቦጫጭቀዋለሁኝ ። ለምን እዛው አይገድሉኝም ፣ አልለቃቸውም!» በማለት ተናገረ ።

«እንዴት አድርገህ ትደባደባለህ ፣ አንተ ለራስህ ኩስስ ያልክ ከሲታ ነህ» አለችው እናት ።

«የፈለገው ይሁን እደባደባለሁኝ!» አለ ።

ፌዎዶር ከሄደ በኋላ እናት ፓቬልን እንዲህ በማለት ተናገረችው ፡ —

«ከሁሉም ቀድሞ በጠላት የሚፈታው ፌዎዶር ነው!» አለች ።

ፓቬል አንዳችም መልስ አልመለሰም ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የማዕዱ ክፍል በር ቀስ ብሎ ተከፈተና ሪቢን መጣ። በጥቂቱ ፈገግ በማለ ትም ፦

«እንደምንድናችሁ! ይኸው እንደገና መጣሁኝ ። ትላ ንትና ማታ አስገደዱኝ፥ ዛሬ ራሴ መጣሁኝ!» አለ ። የፓ ቬልን እጅ ስሜት በተሞላበት ሁኔታ አወዛውዞ ከጨ በጠ በኋላ የፔላጌያን ትከሻም በእጁ ነካ-ነካ አደረገ ።

«አንድ ብርጭቆ ሻይ ብጠጣ እንዴት ደስ ባለኝ ነበር!» በማለት ተናገረ ።

ፓቬልም በጢም የተወረረውን የሪቢንን ሰፋ ያለ ፊት እና ጥቋቁር ዐይኖቹን በጥሞና እየተመለከተ ያጤናል ። በእንዲህ ያለ አመለካከቱ አንድ ነገር ለመረ ዳት የፈለገው ነበር ።

እናት ሳሞቫሩን ለማያያዝ ወደ ማዕድ ቤት ሄደ ች ። ሪቢን ክርኖቹን ጠረጴዛ ላይ አስደግፎ ተቀም ጦአል ። ከዚያም ፓቬልን እየተመለከተ ቀደም ሲል ከጀመረው ንግግር የተቋረጠ ይመስል ፦

«እና ይኸውልህ፥ ከአንተ ጋር በግልጽ መወያየት እሻለሁኝ ። ሁኔታህን ለጥቂት ጊዜያት እየተከታተልኩ ኝ ነበር ። የምኖረውም ያው ከቤትህ ጎን የማለት ያህ ል ነው ። ብዙ ሰዎች ወደቤትህ የሚመጡ መሆናቸ ውን፥ ይሁን እንጂ የማይሰክሩ ወይንም የማይራበሹ መሆናቸውን ተገንዝቤአለሁኝ ። ይኼ አንዱ ጉዳይ ነው ። ደህና-ደህና ሰዎችን ወዲያውኑ ለይቶ ማወቅ ይቻላል ። እንዲህ መሆናቸው ለምንድነው ብለህ ትደነቃለህ ። እ ኔም ራሴ ብሆን ከሁሉም ነገር ተጠንቅቄ የምኖር ሰው ነኝ» በማለት ተናገረ ።

አነጋገሩ ጎተት ያለ ቢሆንም አንደበቱ ሳይገታ ቃላቶቹን ይሰነዝራል ። ጢሙን ጠቆር ባለ እጁ እያሻ ሸ የፓቬልን መልክ አተኩሮ ይመለከታል ። ከዚያም ቀጠል አደረገና ፦



«ሰዎች ስለአንተ ወሬ ማውራት ጀምረዋል ። ከእነ ዚህ ስለአንተ ከሚያወሩት ሰዎች መካከል አንዱ እ ኔ የምኖርበት ቤት ባለቤት ነው ። ቤተክርስቲያን የማ ትሄድ በመሆንህ ምክንያት መናፍቅ ነህ ይልሀል ። እኔም ራሴ ብሆን ቤተክርስቲያን አልሔድም ። ከዚያ ም እነዚያ ወረቀቶች መበተን ጀመሩ ። አንተ ነህ እንዴ ይኸን አስበህ ያደረግህ?» በማለት ጠየቀው ።

«አዎን እኔ ነኝ!» በማለት ፓቬል መለሰ ።

«ምን ይላል ኢሄ!» አለች እናት ጠንቀቅ ባለ ሁኔታ ድምጿን ከፍ አድርጋና ከማዕዱ ቤት በራፍ ላይ አንገቷን ብቅ አድርጋ በመናገር ። ከዚያም ፦ — «ይኼ አንተ ብቻህን ያደረግኸው ሥራ አይደለም!» በማለት ቀጠለች ።

ፓቬል ሳቀ ። ሪቢንም ሳቀ ።

«እሺ!» አለ ሪቢን ።

አነጋገሯን ከምንም ባለመቁጠራቸው ምክንያት ገልመጥ አድርጋቸው እያጉረመረመች ወደማዕዱ ቤት ተመለሰች ።

«እነዚያን በምሥጢር የሚበተኑ በራሪ ወረቀቶች ማዘጋጀት ግሩም ሃሣብ ነው ። ሕዝቡን ያነቃሉ ። እስከ አሁን አሥራ ዘጠኝ እትሞች ተሠራጭተዋል ። አይደለ ም እንዴ?» በማለት ሪቢን ጠየቀ ።

«አዎን!» በማለት ፓቬል መለሰ ።

«ይህም ማለት ሁሉንም የተበተኑትን ወረቀቶች በሙሉ አንብቤአቸዋለሁኝ ማለት ነው ። በላያቸው ከሠፈሩት ጽሁፎች መካከል ገሚሶቹ ግልጽነት የሮ አቸው የተብራሩ አይደሉም ። ገሚሶቹ ደግሞ አስፈላ ጊ አይደሉም ። ይሁን እንጂ አንድ ሰው እጅግ ብዙ ሃሣቦችን ማቅረብ በሚኖርበት ጊዜ አስፈላጊ ያልሆኑ አንድ-ሁለት በረፍት-ነገሮችን መጨመሩ አይቀርም» አለ ።

ሪቢን ነጭ ጥርሶቹን ብልጭ አድርጎ ሳቀ ። ከዚያም ፡ —

«ከዚያም ፍተሻው ቀጠለ ። ይበልጥ የተደነቅሁት በዚህን ጊዜ ነበር ። አንተ እና ኾኾል እንደዚሁም ኒኮላይ ሁላችሁም ተገኝታችሁ ነበር...» አለ ።

ይህንን ከተናገረ በኋላ ተስማሚ የሆኑ ትክክለኛ ቃላት ለመፈለግ ንግግሩን ጋብ አድርጎ ጠረጴዛውን በእጣቶቹ ቋ-ቋ-ቋ እያደረገ በመስኮቱ ውስጥ ውጪውን አሻግሮ ያስተውል ጀመር ።

«የያዛችሁትን አቋም አሳይታችኋል ። 'ክቡር ሆይ እርስዎም በመሰለዎ መንገድ ይጓዙ ። እኛም በመሰለን እንጓዛለን ።' እንደማለት ያለ ነው ። ኾኾልም ጥሩ ሰው ነው ። አንዳንድ ጊዜ ፋብሪካ ውስጥ ሲነጋገር ስሰማው ፡ 'ይኸንን ሰው አንዳችም ነገር ድል አይነሳውም ። ሞት ብቻ ነው የሚገላግለው ። እንደብረት የጠነከረ ሰው ነው ።' በማለት ለራሴ አስባለሁኝ ። ታምነኛለህን ፓቬል?» በማለት ጠየቀ ።

«አዎን አምንሃለሁኝ!» በማለት ፓቬል ራሱን በአዎንታ እየነቀነቀ መለሰ ።

«ጥሩ! እኔን ተመልከተኝ ። አርባ ዓመቴ ነው ። ከአንተ ሁለት ጊዜ ሽማግሌ ስሆን ከአንተ የበለጠ ሃያ ዓመት ኖሬአለሁኝ ። ከሦስት ዓመት በላይ በወታደርነት አገልግዬአለሁኝ ። ሁለት ጊዜ አግብቻለሁኝ — የመጀመርያ ሚስቴ ሞተች ። ሁለተኛይቱን ፈታኋት ። ካውካሰስ በተሰኘው ክፍለ-ሀገር ኖሬ የነበር ሲሆን እዚያም ዱኾቦርትጽ* የተሰኙትን ተመልክቻለሁኝ ። ከህይወት ጋር እኩል መራመድ የሚችሉ አይደሉም ። ወንድሜ ፡ በፍጹም አይደሉም!» በማለት መለሰ።

* ዱኾቦርትጽ ፡ — የየራሳቸውን የሃይማኖት ዕምነት ተከታዮች ። (ተርጓሚው)



እናት ጠንከር ያለ አነጋገሩን በጉጉት ታዳምጣለች ። ይህ መካከለኛ ዕድሜ ያለው ሰው ከልጅዋ ጋር እንዲህ ያለ ንግግር መነጋገሩ አስደሰታት ። ይሁን እንጂ የፓቬል ጠባይ ድርቅ ያለ በመሆኑ እርሷ ይበልጥ እንግዳ ተቀባይ በመሆን ለማካካስ ሞከረች ። ስለዚህም ፡ —

«ሚኻኢሎ ኢቫኖቪች ፡ ትንሽ የሚጎረስ ብጤ ላቅርብልህ?» በማለት ሪቢንን ጠየቀችው ።

«አመሰግናለሁኝ እናት ። እራቴን አሁን ነው የበላሁት» በማለት ለእናት መልስ ከሰጠ በኋላ «እና ታዲያ ፡ ፓቬል ፡ ሕይወት እንደዚህ መሆን የለበትም ብለህ ነው የምታስበው?» ብሎ ፓቬልን ጠየቀ ።

ፓቬልም ከመቀመጫው በመነሳት እጆቹን ወደኋላው አድርጎ ክፍሉ ውስጥ ወዲያና-ወዲህ ይንጎራደድ ጀመር ። ከዚያም ፡ —

«ሕይወት ትክክለኛውን አቅጣጫ እየተከተለ ነው ። አንተ እኔን ግልጽ በሆነ ልቦናህ እንድትቀርበኝ ያደረገ ሕይወት አይደለምን? እኛን ሠርቶ-አደሮችን ሕይወት ቀስ-በቀስ እያስተባበረን ነው ። መላውን ሠርቶ-አደሮች በሙሉ በአንድ ላይ የሚያስተባብርበት ጊዜም ይመጣል ። ሕይወት ለእኛ ከባድ እና አድላዊ ነው ። ይሁን እንጂ ፡ መራራ የሆነ ምንነቱን በዐይናችን ፊት ጉልህ አድርጎ እያሳየን በመገኘት ላይ ሲሆን ፡ ሁኔታዎችን በፍጥነት ለማንቀሳቀስ እንዴት እንደሚቻልም ያመለክተናል» በማለት ተናገረ ።

«ልክ ነህ!» አለ ሪቢን ። ከዚያም ፡ — «ሰውን ተሃድሶ እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል ። አንድ ሰው ሰነፍ ከሆነ ገላ መታጠቢያ ቤት ወስደኸው ደህና አድርጎ ገላውን እንዲታጠብ ካደረግህ በኋላ ንጹህ ልብስ እንዲለብስ አድርገው ። ከዚያ በኋላ በተገቢ ሁኔታው ላይ እንደገና ሊገኝ ይችላል ። የአንድን ሰው ልብ ግን

እንደምን አድርጎ ማጠብ ይቻላል? ችግሩ ያለው እዚህ ላይ ነው!» በማለት ተናገረ ።

ፓቬል ስለ ፋብሪካው እና ስለ ፋብሪካው አለቆች ሁኔታ ፤ እንደዚሁም ወዝ-አደሮቹ ለመብታቸው እንደምን እንደሚታገሉ በስሜት ተውጦ ተናገረ ። ፓቬል በሚናገርበት ጊዜ ሪቢን የፓቬልን ዐረፍተ-ነገሮች በአራት ነጥቦች ይደመድማቸው ይመስል አልፎ-አልፎ ጠረጴዛውን በእጣቱ ቋ-ቋ ያደርጋል ። ብዙ ጊዜም በፓቬል ንግግር ጣልቃ እየገባ ፡ —

«እሺ! ወይ ጉድ!» ይላል ።

አንድ ጊዜ ደግሞ ሳቅ ካለ በኋላ የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«አንተ ገና ወጣት ነህ! ስለሰው ብዙ አታውቅም!» አለው ። ፓቬልም ሪቢን አጠገብ በመሄድ ኮስተር ብሎ የሚከተለውን መለሰለት ፡ —

«እከሌ ወጣት ነው ወይንም ሽማግሌ ነው በማለት አናውራ ። መገንዘብ ያለብን ትክክሉ አስተያየት የማን አስተያየት እንደሆነ ነው ።»

«እና ፤ ስለ እግዚአብሔር ምንነት ጭምርም ሲያሞኙን ነበር ብለህ ትገምታለህ ማለት ነዋ? ሀ! እኔም ሃይማኖታችን ፋይዳ-ቢስ ነው ብዬ አስባለሁኝ ።» አለ ።

እዚህ ላይ እናት ተሸበረች ። ፈጣሪን በሚመለከት ጉዳይ ላይ እና የተወደደ እና የተቀደሰ አድርጋ የምትቆጥረውን ፈጣሪ አምላኳን በሚመለከት ረገድ የምትከተለውን ዕምነቷን አንስቶ ባወሳ ቁጥር አላማኒ በሆነ አስተሳሰብ የልብ ቁስል እንዳይተክልባት ዐይኖቿን ከዐይኖቹ ጋር ተክላ ትመለከተዋለች ። ይሁን እንጂ ፤ ከእርሱ አላማኒነት በስተጀርባ በእርሱ ላይ አንድ ዓይነት ዕምነት ይሰማታል ። ይኸ ዕምነትም ያጽናናታል ።



«አስተሳሰቦቹን ልረዳ የምችለው ከቶውኑ እንዴት ይሆን?» በማለት ትደነቃለች ።

ይኸ በመካከለኛ የዕድሜ ዘመኑ ላይ የሚገኝ ሪቢንም በልጅዋ አነጋገር ቅር ይሰኝ ይሆናል ብላ ታስባለች ። ይሁን እንጂ ፤ ሪቢን ረጋ ብሎ ለፓቬል ይኸንን መሳዩን ጥያቄ ባቀረበለት ጊዜ ልትታገስ ካለመቻሏም በስተቀር በአጭሩ እና መረር ባለ አነጋገር የሚቀጥለውን ተናገረች ፡ —

«ፈጣሪ አምላክን በሚመለከት ረገድ ፤ የምትናገራቸውን ቃላት ዝግ ብለህ ብታስተውል ይሻላል! ያሻህን ሁሉ መመራመር ትችላለህ ። ከእኔ አሮጊት ከሆንኩቷ ሴት ላይ ግን ፈጣሪ አምላኬን ከገፈፍክብኝ ከሀዘኔ እና ከትካዜዬ የሚያጽናናኝ አላገኝም!» አለችው ።

ሳሕኖቹን በምታጥብበት ጊዜ ዐይኖቿ በዕንባ ተመሉ ። እጣቶቿም ይንቀጠቀጣሉ ።

«እናቴ! እኛን ልትገነዘቢን አልቻልሽም!» በማለት ፓቬል አክብሮት ባልጎደለው ሁኔታ ተናገረ ።

«እናት! ይቅርታ አድርጊልን!» በማለት ጎላ እና ረጋ ባለ ድምፅ ሪቢን ተናገረ ።

በጥቂቱ ፈገግ ካለ በኋላ ፓቬልን መልከት አደረገው ። ከዚያም ፡ —

«ይህንን አስተሳሰብ ልትረጂው እንደማትችይ ዘንግቼው ነበር!» በማለት ተናገረ ።

«እኔ የተናገርኩት ደግ እና መሀሪ ስለሆነው ስለዚያ ስለምታምኝበት አምላክ አልነበረም ። እኔ የተናገርኩት መማቻ ዱላ ይመስል እኛን ለማስፈራራት ካህናት መጠቀሚያቸው ስለሚያደርጉት አምላክ ነው ። እፍኝ የማይሞሉ ሰዎች ለሚፈጽሟቸው ክፉ ምግባሮች ሕዝቦች በሙሉ እንዲሰግዱ ለማድረግ ስለሚጠቀሙበት አምላክ ነው» በማለት ፓቬል ተናገረ ። ሪቢንም ጠረጴዛውን በመደብደብ ፡ —

«ይኸውልህ! የሀሰት አምላክ ፈጥረውብናል! አጠገባቸው ያገኙትን ነገር ሁሉ እያነሱ ሊቀጠቅጡን ይሻሉ! እናት ፣ እስኪ ይኸንን ጉዳይ ዝግ ብለሽ አስተውይው ፡ — እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ ፈጠረው ። ይህም ማለት ሰው ፈጣሪውን የሚመስል ከሆነ ፣ ፈጣሪ አምላክም ሰውን ይመስላል ማለት ነው ። እኛ ግን ፈጣሪን የምንመስል ሳንሆን እንደዱር አራዊቶች ነን ። አብያተ-ክርስትያናት በእኛ ላይ የማስፈራሪያ ቁራዎች ያስጮሁብናል ። አየሽ እናት ፣ ይኸንን ዓይነቱን አምላክ መለወጥ ያሻል ። ማጽዳትም ያሻል! ፈጣሪን የቅጥፈት እና የዘለፋ ልብስ አጎናጽፈውታል ። ነፍሳችንን ለማውጣት ሲሉ ካህናት የፈጣሪን መልክ ተልትለውታል!» በማለት ተናገረ ።

ይናገር የነበረው ረጋ ብሎ ነው ። ይሁን እንጂ ከአንደበቱ የሚወጡት እየአንዳንዳቸው ቃሎች እናትን አስደንግጠዋታል ። በጥቁር ጢም የተከበበውና ረጅም የሆነውን አስከሬን መሳይ ፊቱን ስታይ ትፈራዋለች ። ልቧን በድንጋጤ ድው-ድው የሚያደርጉትን የዐይኖቹን ጽልመታዊ አበራር አተኩራ መመልከት አልቻለችም ።

«ከዚህ ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ልሒድ ። እንዲህ ያለ ንግግር ማዳመጥ ለእኔ ከአቅሜ በላይ ነው!» በማለት ጭንቅላቷን እያወዛወዘች ተናገረች ።

ከዚያም ወዲያውኑ ወደማዕዱ ክፍል ሄደች ።

«አየህ ፓቬል ፣ የነገሮች ሁሉ መገኛ ማዕከል ጭንቅላት ሳይሆን ፣ ልብ ነው ። ልብ በሰው ነፍስ ውስጥ ይዞት የሚገኘው ቦታ እጅግ ልዩ የሆነ ቦታ ነው ። በዚያ ቦታ ውስጥም ሌላ የሚበቅል አንዳችም ነገር የለም» በማለት ሪቢን ተናገረ ።

«የሰውን ልጅ ነፃ የሚያወጣው የአዕምሮ ምርምር ብቻ ነው!» በማለት ፓቬል ጠንከር አድርጎ ተናገረ ።

«የአዕምሮ ምርምር ለሰው ልጅ ብርታትን የሚሰጥ አይደለም ። ብርታትን የሚሰጠው ልቡ እንጂ አዕምሮው አይደለም!» በማለት ሪቢን ድምፁን ከፍ አድርጎ መለሰለት ።

እናት ልብሶቿን አወላልቃ የምሽት ፀሎቷን ሳታደርስ ተኛች ። በርዷት የነበረ ከመሆኑም በስተቀር ደስ አልተሰኘችም ። ቀደም ሲል ብልህ ሰው መስሏት የነበረው እና ደስ አሰኝቷትም የነበረው ሪቢን አሁን እንድትጠላው አደረጋት ። ሪቢን በተናገረ ቁጥር ፣ እናት ፡ —

«ኧረ ጉድ በሉ ይሄን ከሃዲ! ኧረ ጉድ በሉ ይኸን አመጸኛ! እዚህ ምን ሊያረግ ይመጣል?» በማለት ከራሷ ጋር ትነጋገራለች ።

እርሱ ግን በተረጋጋ ሁኔታ እንደሚቀጥለው መነጋገሩን አላቋረጠም ፡ —

«ቅዱሱ ቦታ ባዶ መሆን የለበትም ። አምላክ ልብ ውስጥ የሚይዘው ቦታ እጅግ ገር የሆነ ቦታ ነው ። ያንን ቦታ ቆርጠህ ብታወጣው በምትኩ ትልቅ ቁስል ይቀራል ። ፓቬል ፣ አዲስ ዕምነት ማሰላሰል አለብህ ። ለሰው ጓደኛ የሚሆን አምላክን መፍጠር ያስፈልጋል!» አለ ሪቢን ።

«ክርስቶስ እኮ ነበር!» በማለት ፓቬል መለሰ ።

«ክርስቶስ ደካማ ነበር ። 'ይኸ ጽዋ ይለፈኝ' በማለት ተናገረ ። ቄሳርንም አወቀ ። በፈጠራቸው ፍጡሮቹ ላይ ሰው የበላይነት ሥልጣን እንዲኖረው ፈጣሪ እንዴት ይፈቅዳል? እርሱ ራሱ ሁለንታዊ ሥልጣን እኮ ነው! ከዚህ መለስ የፈጣሪ ነው ፣ ከዚህ መለስ ደግሞ የሰው ነው በማለት ፈጣሪ ነፍሱን ከሁለት ቦታ አ

ይከፍልም ። ፈጣሪ ግን ንግድን አልተቃወመም ። ጋብቻንም አልተቃወመም ። የበለስን ዛፍ መርገሙም ትክክል አልነበረም ። የበለስ ዛፍ ፍሬ ስላላፈራ ሊወቀስ ይገባዋልን? የሰው ልጅ ደግነትን የማያስገኝ እስከሆነ ድረስ ሊወቀስ እንደማይችል ሁሉ ይኸንን መሳይ ክፋት ነፍሴ ውስጥ ያለመለምኩት እኔ ራሴ ነኝን?»

የሁለቱ ሰዎች ድምፅ በከፍተኛ ስሜት በተዋጠ ክርክር በክፍሉ ውስጥ በተፈራራቂ ይሰማል ። ፓቬል በክፍሉ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ ሲንጎራደድ ወለሉ ሲጥ-ሲጥ የሚል ድምፅ ያሰማል ። ፓቬል በሚናገርበት ጊዜ ሁሉም ነገር ፀጥ በማለት አንዳችም ድምፅ አይሰማም ። ሪቢን ግን ዝግተኛ በሆነ እና ረጋ ባለ ድምፁ በሚናገርበት ጊዜ የግድግዳው ሰዓት መቂናጥ ከወዲያ ወዲህ ቋ-ቋ-ቋ የሚል ድምፅ ሲያሰማ እና በረዶ የተቀላቀለው ነፋስም የቤቱን ግድግዳ ታክኮ ሲነፍስ ንግግሩን ትሰማለች ።

«በእኔው በራሴ አባባል ፤ ማለትም በብረት አቅላጭ አባባል ሃሣቤን ላቅርብ — እግዚአብሔር የእሣት ነበልባል ነው ። እርሱም በሰዎች ልብ ውስጥ ያድራል ። 'አስቀድሞ ቃል ነበረ ። ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ።' ተብሎአል ። እና ስለዚህም ፤ ይህ ቃል መንፈስ ነው…»

«ቃል አዕምሮ ነው!» በማለት ፓቬል አጠንክሮ ተናገረ ።

«እሺ ይሁን ። እንደዚህም ከሆነ ፤ እንግዲህ የእግዚአብሔር መገኛ በልቦና እና በአዕምሮ ውስጥ ነው እንጂ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አይደለም ማለት ነው ። ቤተ-ክርስቲያን የፈጣሪ መካነ-መቃብር ነው ።»

እናት ተኝታ ስለነበረ ሪቢን ሲሄድ አልሰማችም ።

ከዚህም በኋላ ሪቢን አዘውትሮ መጪ ሆነ ። ሪቢን በሚመጣበት ጊዜ ከፓቬል ጓዶች መካከል አንደኞቸው ቢኖሩ ፤ ሪቢን ከአንድ ጥግ ቦታውን ይዞ ከመቀመጥ በስተቀርና አልፎ-አልፎ ብቻ «እንዴታ ነው እንጂ!» ከማለት በስተቀር ሌላ ነገር አይናገርም ።

አንድ ቀን ከተቀመጠበት ጥግ ቦታ ሁኖ በቤቱ ውስጥ ያሉትን ሁሉ አተኩሮ እየቃኛቸው ጨፍገግ ባለው ሁኔታ ሪቢን የሚከተለውን ተናገረ ፡ —

«ስለማናቸውም ጉዳዮች በሚወሳበት ጊዜ ጉዳዮቹ በሚገኙበት ሁኔታ ላይ ተመሥርቶ ማውሳት እንጂ ወደፊት ምን እንደሚሆኑ ገምቶ ማውሳት አያስፈልግም ። እነዚህ ጉዳዮች ወደፊት ምን እንደሚሆኑ ማን ያውቃል? ሕዝቦች አንዴ ነፃ ከወጡ ለራሳቸው የሚበጃቸውን ራሳቸው ይወስናሉ ። ምን እንደሚፈልጉ ሳይጠየቁ በጫንቃቸው ላይ እስከዛሬ በተደራራቢ ከባድ መርግ ድንጋይ ተጭኖባቸዋል ። ሕዝቦች የሚሹትን ያስቡ ይመራመሩ ዘንድ ከእንግዲህ ጊዜው ነው ። ምናልባትም እኮ ማናቸውንም ነገር ፤ ማለትም ኑሮንም ፤ ምርምርንም ይቃወሙ ይሆናል ። ምናልባትም እንደቤተ-ክርስቲያን አምላክ ሁሉንም ነገር ጠላታቸው አድርገው ይመለከቱት ይሆናል ። መጻሕፍቶቹን በሙሉ ስጧቸው ። ከዚያም እነርሱ ራሳቸው ያሻቸውን ይምረጡ ። ዋናው ነገር ይኸ ነው!»

ሪቢን እና ፓቬል ብቻቸውን ሲሆኑ ክርክራቸው ማብቂያ በሌለው ሁኔታ የሚቀጥል ሲሆን በሚከራከሩበት ጊዜም በመማረር እርስ-በርሳቸው አይናቆሩም ። እናት እነርሱ የሚለዋወጧቸውን እየአንዳንዳቸውን ቃላት በማዳመጥ ፍሬ-ሃሣቡን ለመገንዘብ በጥሞና ትጥራለች ። አንዳንድ ጊዜ ባለ ሰፊ-ትከሻው እና ጢም-ጥቁሩ ሪቢን ፤ እንደዚሁም ጠንካራው እና ረጅሙ ልጅዋ የታወሩ ይመስላታል ። የመውጫቸውን ቦታ በመፈለግ አንዴ ወዲህ አንዴም ወዲያ በመዳበስ ፤ ዐይን-አልባ በሆኑት ጠንካራ ጣቶቻቸው ያገኙትን

ሁሉ በመነካካት ፤ ከወዲያ ወዲህ በመንቆራጠጥ ዕቃ ዎችን በመጣል በእግራቸው ይሰባብራሉ ። ያመኑበት ን ሳይለቁና ተስፋቸውንም ሳይቆርጡ በተመስጦ ተው ጠው ዕቃዎችን በመነካካትና በማተረማመስ ያመሰቃ ቅላሉ ።

ሃቀኛነትን እና ቆራጥነትን የሚያረጋግጡ መግለ ጫዎች የሆኑትን አስደንጋጭ ቃላትን እናት ለማዳ መጥ እንድትችል ያበቋት ሲሆኑ ፤ እነዚህን የመሳሰ ሉት ቃላት ቀደም ሲል ያሳድሩባት የነበሩትን ዓይ ነት ኃይለ-ሥሜቶች አሁን ተላምዳቸዋለች ። እንዴት እንደምትቋቋማቸው ተገንዝባለች ። አንዳንድ ጊዜ ፈጣ ሪ-አምላክን ስለመካድ በሚገለጹት ቃላት ውስጥ ለፈ ጣሪ-አምላክ ያላትን የማይናወጽ ዕምነት ትገነዘባለች ። ከዚያም መለስተኛ በሆነ በይቅር-ባይነት ፈገግታ ፈገ ግ ትላለች ። እና ደግሞ ፤ ምንም እንኳን ሪቢንን የማት ፈቅደው ቢሆንም ፤ ባየችው ቁጥር ለርሱ ያላት ትልቅ ጥላቻ መቀስቀሱ አብቅቷል ።

በየሳምንቱ ለኾኾል መጻሕፍቶችን እና የታጠቡ ልብሶችን ወህኒ ቤት ትወስዳለች ። አንድ ጊዜ ከኾ ኾል ጋር ተገናኝታ እንድትነጋገር ተፈቅዶላት ነበር ። አነጋግራው ከተመለሰች በኋላም ስለርሱ ሁኔታ ስት ናገር ፡ —

«ቅንጣት ታህል አልተለወጠም ። ለሰው ሁሉ የሚ ያሳየው የተለመደ ደግነቱ እንዳለ ነው ። ሰው ሁሉ ከርሱ ጋር ይቀልዳል ። ያለበት ሁኔታ ለርሱ ከባድ ነው ። በጣም ከባድ ነው ። ያም ሁኖ ግን መከፋቱን አያሳይም…» በማለት ለርሱ ባላት የመውደድ ሁኔታ ተናገረች ። ሪቢንም በበኩሉ አስተያየቱን ሲሰጥ ፡ —

«ነው እንጂ! እንዲህ መሆን አለበት ። ሀዘን መሸሸ ጊያ ነው ። እኛም በውስጡ ተሸሽገን እንገኛለን ። ይኸ ንን መሳዩን የመሸሸጊያ ልብስ መልበስ ተላምደናል ።



የሚያስኩራ ነገር የለበትም ። ሰው ሁሉ ዐይኖቹ እንዳ ያዩ ይሁነኝ ተብሎ በተጋረደበት ግርዶሽ የተከለለ አይደለም ። አንዳንድ ሰዎች እንደው ዝም ብለው ዐይ ኖቻቸውን ይጨፍናሉ ። ስለዚህም እንከፎች ከሆንን እየሳቅን መከራችንን መቀበል ብቻ ነው!» በማለት ተናገረ ።

## 12

በአካባቢው የሚገኘው ነዋሪ ግራጫማ ቀለም ወዳለ ው ወደእነሸላሶቭ ትንሽ ቤት ከጊዜ ጊዜ ዐይኖቹን ማማተር ቀጠለ ። ይኸ የማተኩሩ ዝንባሌ ሊደርስ የ ቻለበት ምክንያት በጥርጣሬ እና ከውስጥ ተደብቆ በሚገኝ የጠላትነት ስሜት ሲሆን ፤ ዕምነት በተጣለ በት የመወደድ ስሜት ላይም የተመረኮዘ ነበር ። አንዳ ንድ ጊዜ ፓቬልን አንዱ የማያውቀው ሰው ከመንገ ድ ላይ አግኝቶት ያቆመውና የሚከተለውን ይጠይቀ ዋል ፡ —

«ሰማኸኝ ወይ ወንድሜ ፤ አንተ መጻሕፍቶችን የምታነብ ሰው ስለሆንክ ሕጉን የምታውቅ ነህ ። ከ ዚህ ቀጥሎ በምገልጽልህ ጉዳይ ላይ ያለህን አስተያ የት አትነግረኝምን?…»

ይኸንን በመሳሰለ ጥየቃ ፖሊስ ወይንም የፋብሪ ካ አስተዳዳሪ ያደረሱባቸውን በደሎች ለፓቬል ዘር ዝረው ያስረዱታል ። ፓቬል ጉዳዩን ፡ ውስብስብ ሁኖ ሲያገኘው ለባለ ጉዳዩ ማስታወሻ ጽፎ በመስጠት በከተማው ውስጥ ከሚገኘው እና ከሚያውቀው ጠበቃ ዘንድ ባለጉዳዩ ሂዶ ጉዳዩን እንዲያስረዳ ያደርጋል ። እ ርሱ ራሱ ሊያስረዳ የሚችለው ጉዳይ ሲሆን ደግሞ ጉዳዩን ለባለ ጉዳዩ ያብራራለታል ።